# ከመስከረም ፩፡ ርእሰ-ዐውደ-ዓመት፡ እስከኅዳር ፳፩ ቀን፡ ተዝካረ-ማርያም ድረስ ስላሉ በዓላትና አጽዋማት፡ መልእክታዊ ማብራሪያ።

## የእግዝእተብሔር እም፡ ድንግል ማርያም በዓለ ልደት፡፡

[በግእዙ፡ "እግዝእትነ"፡ "እግዝእተብሔራችን" እንጂ፡ *"እመቤታችን"* ማለት አይደለም፤
"እግዚእነ"፡ "እግዚአብሔራችን" እንጂ፡ *"ጌታችን"* ማለትም አይደለም።
Lord፡ "ጌታ"፥ Lady፡ "እመቤት" ተብሎ፡ እንደፈረንጆቹ ቋንቋ ሊተረጐም አይገባም።]

ከመስከረም ፩ ቀን፡ የርእሰ ዐውደ-ዓመት በዓል ጋር፡ ዐብሮ ስለሚታሰበው፡ ስለእግዝእተብሔር እም፡ ድንግል ማርያም፡ የልደቷ በዓል፡ እዚህ ላይ፡ ሊታወስ የሚገባው ቍም-ነገር አለ። ያንንም፡ እንደሚከተለው ገላልጠን አቅርበንላችኋል፡-

አዎን! የእርሷ፡ የእግዝእተብሔር እም፡ ድንግል ማርያም ልደት፡ እንደልጇ ወዳጇ እግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ መሲሕ ልደት ዅሉ፡ በውጪ፡ በሊባኖስ ተራራ ላይ፡ በዛፍ ሥር መኾኑ፡ በልጇ ልደት፡ ኋላ፡ በበረት የተከሠተውን፡ ታላቁን የመለኮት ምስጢር፡ ቀደም ብሎ፡ በእርሷ ልደት፡ ፍንጩን አሳይቷል፡፡ ይህም የኾነው፡ በጠቅላላ፡ ስለኢየሱስ መሲሕ፥ በተለይም፡ ቅድሚያ ስላለው፡ ስለትስብእቱና ስለልደቱ የተነገረውን ትንቢት ዅሉ፡ ለመጨረሻው ፍጻሜ እንዲበቃ ለማድረግ ያስቻለውን መሠረት ለመጣል ነበረ፡፡

ይኸውም፡ የድንግል ማርያም ወላጆች፥ አያቶች እና ቅድመ አያቶች፥ ምዝላቶችም፡ የዚችው ልጃቸው፡ ቀዳሚት አርአያና ጥላ የኾነችውን፡ የንግሥተ ሳባን ፈለግ በመከተልና ከኖኅ ጀምሮ፡ በኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት ዘንድ፡ ሲወርድ ሲዋረድ የተለመደውን ሃይማኖታዊ ጉዞ፡ የትውልድ ግንዳቸው፡ መልከ ጼዴቅ ወደቈረቈራት፡ ቅድስት ሀገር፡ ወደኢየሩሳሌም በማድረግ ያረጋገጡት ነው፡፡

ቅድስት ድንግል ማርያም፡ ገና፡ በእናቷ፡ በሐና ማሕፀን ውስጥ ተፀንሳ ሣለች፡ ሕሙማንን በመፈወስ፡ ብዙ ተአምር ታደርግ ስለነበረ፡ ያን ዅሉ ተአምራት የተመለከቱ አይሁድ፡ ለምቀኝነት አያርፉምና፡ የኢትዮጵያ ልጆች በኾኑት፡ ኢያቄምና ሐና ላይ፡ ታላቅ ቅንዓት አደረባቸው፤ *"ቀድሞ፡ ከእነዚህ ወገን የሚኾኑ፡ 'ዳዊት፥ ሰሎሞን'፡ አርባ አርባ ዘመን፡ እንደሰም አቅልጠው፥ እንደገል ቀጥቅጠው ገዙን፤ ደግሞ፡ ከዚህች የተወለደ፡ እንደምን ያደርገን ይኾን?"* ብለው፡ በጠላትነት ተነሡባቸው፡፡

በዚህ ጊዜ፡ የእግዚአብሔር መልአክ፡ ኢያቄምን፡ "ወደሊባኖስ ተራራዎች፡ ይዘሃት ኺድ!" ብሎት፡ ወደዚያ ኼደው፡ እግዝእተብሔር እም የተዋሓደቻትን ድንግል ማርያምን፡ ሐና፡ በዚያ የተራራ ዛፎች ሥር ወልዳታለች!

በዚህም: "እምሊባኖስ: ትወፅእ መርዓት!": ማለትም: "ሙሽሪት: ከሊባኖስ ትወጣለች!" የሚለው ትንቢት ተፈጸመ::

የእርሷ ልደት: በሊባኖስ ተራራ: በዛፍ ሥር፥ የልጇ የኢየሱስ መሲሕም ልደት: በቤተ ልሔም: በከብቶች በረት፥ እንዲሁም: በጻድቁ ኢትዮጵያዊ ጃንደረባ: በዮሴፍ የተጠበቀው ምድራዊ መጠለያቸው: በናዝሬት ዋሻ መኾኑ: ለዚያ ሃይማኖታዊ ጉዟቸውና ለመጻተኛ ኑሮአቸው እውነተኛነት: በቂ ማስረጃ ኾኖ ይመሰክራል:: "ዮሴፍ" የሚለው ስም: በግብፅ ስደተኛ ኾኖ ከኖረው: ከመጀመሪያው ዮሴፍ ወዲህ: ለስደተኛ ግለሰብ የሚሰጥ ስያሜ በመኾኑ: ያም የኢትዮጵያዊው ዮሴፍ ስደተኛነት፡ እዚህ ላይ ሊጤን ይገባዋል::

በዚህ መልክ: በመስከረም ፩ ቀን የጀመርነውን: የምሕረቱን ዓመት: ሥጋዊ እና ነፍሳዊ፥ መንፈሳዊ እና ኹለንተናዊ ጉዞ: ወደፊት: በየመልካቸው እንደምናስተናግዳቸው፡ እንደሌሎቹ ምግባሮቻችን ኹሉ: በእውነት እና በመንፈስ ቅዱስ አምልኮታችን አካኺደን፡ ለፍጻሜ የምናበቃው ሊኾን ይገባል:: ይህም ማለት: "በዚህ ጉዞ: እግዚአብሔር: ይህን ዓለም ሲፈጥር: ለሰው ልጆች ሥጋዊ ሕይወት: አስፈላጊ የኾኑትን: ከፀሓይ እንሥቶ: እስከነፋስ፥ ውኃና መሬት ድረስ ያሉትን መሠረታውያን ንጥረ-ነገሮች፥ ከእነዚህ የሚገኙትንም: የሚንቀሳቀሱትንና የማይንቀሳ ቀሱትን፡ ረቂቃንና ግዙፋን ፍጥረታት: አትረፍርፎ መስጠቱ ይታሰብበታል!" ማለት ነው።

ይህ ብቻ አይደለም፤ ከዚህ ጋር ደግሞ: "እኒሁ የሰው ልጆች: በመንፈሳዊ ሕይወታቸው ረገድ: የሚያስፈልጋቸውን ኹሉ: እንዲሁ: ምንም ሳይቀረው: ያሟላላቸው መኾኑ ብቻ ሳይኾን: በጠቅላላ: ለሥጋዊውና ለመንፈሳዊው መልካም ህልውናቸው: ጠንቅ የኾኑትን: የክፋትን ኃይላት፥ ኃጢአትንና ሞትን: በመጨረሻው ዘመን: በኢየሱስ መሲሕ ሰው መኾን አስወግዶላቸው: የዘለዓለም ድል አድራጊነትን ጸጋ ያስገኘላቸው መኾኑን በመገንዘብና በማስታወስ ጭምር ሊኾን ይገባል!" ማለት ነው::

እንግዴህ: እያንዳንዱ በዓል: እውነተኛ ኾኖ: ለእየራሳችን፡ እርካታን የምናተርፍበት፥ በፈጣሪያችንም ፊት ሞገስን የምናገኝበት: በዚህ መልክ ስናከብረው መኾኑን: በብርቱ ልንገነዘበው ይገባናል::

## ስለእግዝእተብሔር እም፡ ቅድስት ድንግል ማርያም የልደት ቀን ሓተታ።

የቅድስት ድንግል ማርያም: የልደቷ በዓል የሚውለው: *"በግንቦት ፩ ቀን ነው!"* ተብሎ: እስከዛሬ: በዚህ ቀን ሲከበር የቆየውን: አኹን: "የለም! ይህ ትክክል አይደለም፤ የእርሷም የልደት ቀን የሚውለው: በ'መስከረም ፩ ቀን ነው!'" ከተባለ: እንዲህ ሊኾን የቻለበትን ምክንያት: ከዚህ ጋር አያይዞ መግለጽ አግባብ ይኾናል:: ምክንያቶቹን: በማስተዋል እንድትመለከቷቸው: ባጭር ቃል እናቀርብላችሁ:-

አንደኛ:- በግብፅ ኦርቶዶክሳውያን ጳጳሳት: የውግዘት ቃል: በኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት ላይ: ጸንቶ እየሠራ ያለው የተአምረ ማርያም መጽሓፍ: የቅድስት ድንግል ማርያም: የልደት በዓል: "ግንቦት ፩ ቀን ይውላል" ብሎ: በዚሁ ወርና ቀን እንዲከበር አድርጓል::

"ቦ፡ እለ ይቤሉ፡ 'አመ ዐሡሩ ለመስከረም ልደታ!' የቅድስት ድንግል ማርያም፡ የልደቷ ቀን፡ 'በመስከረም ዐሥር ነው!' የሚሉም አሉ፤" ተብሎ፡ በዚሁ መጽሓፍ ውስጥ ተጽፎ ዘወትር የሚነበብ፡ ሌላ ተቃራኒ ቃል አለ።

ከዚህ ጋር፡ ከእነርሱው፡ ከግብፅ ኦርቶዶክሳውያኑ መነኮሳት፡ ባገኘነው፡ "ስንክሳር" በተባለው መጽሓፋቸው፡ በመስከረም ፲ ቀን ምንባብ ውስጥ፡ **"ወበዛቲ ዕለት [አመ ፲ ለመስከረም]፡ ቦ፡ እለ ይብሉ፡ ኮነ ልደታ፡ ለእግዝእትነ ቅድስት ድንግል ማርያም፡ ወላዲተ አምላክ፤ ወዝንቱ ጽሑፍ፡ ውስተ መጽሓፈ ግጻዌ፡ ዘቅዱስ አባ መቃርስ፡ ዘገዳመ አስቄጥስ፤ ወከማሁ፡ ካዕበ ጽሑፍ፡ ውስተ መጽሓፈ ግጻዌ፡ ዘላዕላይ ግብፅ፡ ከመ አመ ፲ወ፯ ለወርኀ ታኅሣሥ፡ ፀንሰታ፡ ለእግዝእትነ፡ ቅድስት ድንግል፡ ብፅዕት ሐና፤ ወወለደታ፡ አመ ፲ ለመስከረም፤** በዚችም፡ በመስከረም ፲ ቀን፡ 'አምላክን የወለደች፡ እግዝእተብሔራችን፡ ቅድስት ድንግል ማርያም፡ የተወለደችበት ነው!' የሚሉ አሉ፤ ይህም፡ የአስቄጥሱ ገዳም፡ ቅዱስ አባ መቃርስ፡ ባዘጋጀው፡ መጽሓፈ ግጻዌ ውስጥ ተመዝግቧል፤ እንዲሁም ደግሞ፡ በላዕላይ ግብፅ በሚገኝ፡ መጽሓፈ ግጻዌ ውስጥ፡ 'ቅድስት ድንግል እግዝእተብሔራችንን፡ ቅድስት ሐና፡ በታኅሣሥ ወር፡ በ፲፯ኛው ቀን፡ እንደፀነሰቻትና በመስከረም ፲ ቀን እንደወለደቻት የሚያመለክት ቃል አለ፤" ተብሎ፡ ተመዝግቦ ይገኛል፡፡

"ቦ፡ እለ ይቤሉ!" ማለትም፡ እንዲህ፡ "የሚሉ አሉ!" የተባልን፡ እኛው የኢትዮጵያ ልጆች ነን፤ ሌላ፡ ማን ሊኾን ይችላል? የኢትዮጵያ አምላክ፡ ይህ እውነታ፡ በዚሁ፡ በእነርሱው የተአምረ ማርያምና የስንክሳር መጻሕፍት ውስጥ ሳይቀር፡ በጽሑፍ ሠፍሮ፡ በግድ እንዲነበብ ያደረገው፡ ያለምክንያት አይደለም። ከጥንት ጀምሮ፡ ኢትዮጵያንና ልጆቿን በሚመለከት፡ በነቢያቱ ያናገራቸው መለኮታውያት ቃላቱ፡ ዓለም በተቀበለው መጽሓፍ ቅዱስ ውስጥ ተጽፈው እንዲገኙ እንዳደረገ ኹሉ፡ አኹን ደግሞ፡ በእነዚህ፡ በግብፃውያን መጻሕፍት ውስጥ፡ ይህንኑ ድንቅ ሥራውን መድገሙ መኾኑን አስተውሉት!

ይኸውም፡ ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት፡ "የቅድስት ድንግል ማርያም፡ የፅንሰቷ ወር፡ 'ታኅሣሥ'፥ የልደቷም፡ 'መስከረም' ነው!" ብለው አምነው፡ ሲያከብሩትና ሲሠሩበት የኖሩት፥ ዛሬም፡ እኛ፡ የቅዱሱ ቃል ኪዳን ልጆቿ ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት፡ እያከበርነውና እየሠራንበት ያለነው፡ ይህ ሥርዓታቸው፡ እውነተኛውና ትክክለኛው፡ የእግዚአብሔሩ መኾኑን፡ በእነርሱው መጽሓፋዊ ማስረጃ ሳይቀር፡ አረጋግጦ በማሳወቁ ነው፡፡

ከዚህ የተነሣ፡ እውነተኛው ሕያው ቅርስ ሳይደመሰስ፥ ደብዛውም ሳይጠፋ፡ እነሆ፡ ለምስክርነት ተርፎ፡ ዛሬ፡ ከእኛም ዘመን እንዲደርስ፥ አኹን፡ በዚህ መልእክት ቀርቦ እንደሚታየውም፡ እነሆ፡ እውነታው ተፈጽሞ፡ እንዲታወቅ ኾነ! ለዚህ ድንቅ ሥራው፡ እያቀረብንለት ያለነውን ምስጋናችንን፡ እግዚአብሔር፡ የሚቀበለው ይኹን! (የተአምረ ማርያም መቅድምና መጽሓፈ ስንክሳር፥ ከመስከረም እስከየካቲት፥ በትንሣኤ ማሳተሚያ ድርጅት፥ አዲስ አበባ፤ ፲፱፻፺፩ ዓ. ም.፤ ገጽ ፵፱፡፡)

ኹለተኛ፡- ቅድስት ሓና፡ ልጇን፡ ቅድስት ድንግል ማርያምን፡ በታኅሣሥ ወር፡ በ፲፯ኛው ቀን እንደፀነሰቻትና በመስከረም ፲ ቀን እንደወለደቻት የሚያመለክተውን፡ የግብፃውያኑን የመጽሓፍ ቃል፥ ፅንሰቷ፡ በታኅሣሥ ፯፥ ልደቷም፡ በመስከረም ፩ ቀን መኾኑን የሚያረጋግጠውን፡ መለኮታዊ እውነት እንዲጸና ካደረገው፡ ከእኛው፡ ከኢትዮጵያኑ ሥርዓት ጋር፡ እንዴት ሊታረቅ እንደሚችል፡ ከዚህ የሚከተለው ሓተታ ያስረዳል፡፡

የዲያብሎስ ሓሰት፡ በንስሓ፡ ወደእግዚአብሔር እውነት ተመልሶ እንዲታረቅ ከማድረግ በቀር፡ በእግዚአብሔር እውነትና በዲያብሎስ ሓሰት መካከል እንዴት ዕርቅ ሊኖር ይችላል? አይችልም። በተነሣንበት ጉዳይ ላይ፡ ዕርቅ ሊኖር የሚችለውም፡ የሰው የኾነው፡ የእነርሱ፡ የግብፅ ኦርቶዶክሳውያኑ፡የሓሰትና የጥፋት ሥራ፡ የእግዚአብሔር ወደኾነው፡ ወደእኛው፡ ወደኢትዮጵያኑ የእውነትና የልማት ሥራ ሲመለስ ብቻ ነው። ይህን መንፈሳዊ ጭንጫ መሠረት በማድረግ፡ ለዚህ እውነታ ማብራሪያ የኾነውን ሓተታ፡ እንደሚከተለው፡ በሦስት ቁም ነገሮች አጠቃልለን አቅርበነዋል፡-

<u>በመጀመሪያ፡-</u> በኹለቱም፡ ማለትም፡ በመስከረምና በታኅሣሥ ወሮች ላይ፡ <u>፲ (ዐሥር) ያህል ቀኖችን የጨመሩት፡</u> እነርሱው፡ መኾናቸውን፡ የራሳቸው ሥራ፡ ዛሬም ይመሰክርባቸዋል፤ ይኸውም፡ እግዚአብሔር፡ በሥነ ፍጥረቱ አከናውኖ ያበጀውንና የኢትዮጵያም ልጆች፡ እስካኹን ጠብቀውት፡ እየሠሩበት የሚገኘውን፡ የቀን አቈጣጠር፡ እነርሱ፡ ምዕራባውያኑ፡ በሰብአዊ ዕውቀታቸውና በሥጋዊው ፍልስፍናቸው ለዋውጠው፡ በዚሁ አቈጣጠራቸው መሠረት፡ በዓመቱ ውስጥ ባሉት ወራት ላይ፡ ከ፮-፲፩ (ከስድስት እስከአሥራ አንድ) ቀኖችን እያከሉ ሲጠቀሙበት በመቀጠላቸው መኾኑ፡ በግልጽ ይታያል።

ይህ፡ የተምታታ ግብራቸው፡ በዚሁ፡ የ"ስንክሳር" መጽሓፋቸው ውስጥ፡ እንደገና፡ በሌላ ማስረጃ ተጋልጠና ተረጋግጦ ስለምናገኘው፡ የኢትዮጵያ የቃል ኪዳን አምላክ፡ የፈጸመልንን የቸርነትና የጥበብ ሥራውን እናደንቃለን። ይኸውም፡ በታኅሣሥ ፲፫ **ቀን ስለሚውሉት በዓላት ሲዘረዝሩ፡ "ወበዛቲ ዕለት፡ ቦ፡ እለ ይቤሉ፡ 'ጸንሰታ ቅድስት ሓና፡ ለእግዝእትነ ቅድስት ድንግል ማርያም፤'** በዚች ቀን፡ 'ቅድስት ሓና፡ ቅድስት ድንግል ማርያምን ጸነሰቻት፤' የሚሉ አሉ፤" ብለው፡ በአጭር ዐረፍተ ነገር ወስነው የገለጹት ቃል ነው። (መጽሓፈ ስንክሳር፥ ከመስከረም እስከየካቲት፥ በትንሣኤ ማሳተሚያ ድርጅት፥ አዲስ አበባ ፲፱፻፺፬ ዓ. ም.፤ ገጽ ፬፻፷፮፤)

የሰዎች የኾነውን ሥርዓት፡ የመለኮት ከኾነው ጋር ለማስተካከል፥ ወይም፡ ለመለወጥ በመሞከር፡ እንደሌላው ድርጊታቸው ኹሉ፡ አኹንም፡ በዚህ ረገድ፡ ያለኀፍረትና ያለይሉኝታ የፈጸሙት የባሰ ጥፋትና በደል፡ በዚያው፡ የስንክሳር መጽሓፋቸው ውስጥ ባለው፡ በራሳቸው ቃል፡ እንዴት አድርጎ እንደሚመሰክርባቸው፡ በማስተዋል ተመልከቱት! ይኸውም፡ **"ወተዝካረ በዓለ ልደታሰ፡ ናሁ ጸሓፍነ፡ ምሉአ ወስፉሓ፡ አመ አሚሩ፡ ለወርኀ ግንቦት። ይደልወነ ንግበር፡ በክልኤሆን ዕለታት፡ ተዝካረ ልደታ፡ ለእግዝእትነ፤ እስመ ይእቲ ትተነብል በእንቲአነ፤** እኛ ግን፡ 'የልደቷ መታሰቢያ በዓል፡ በግንቦት ወር፥ በመጀመሪያው ቀን ነው!' ብለን፡ እነሆ፡ አልምተንና አስፍተን ጽፈናል። እግዝእተብሔራችን፡ ስለእኛ ትማልዳለችና፡ የልደቷን መታሰቢያ በዓል፡ በኹለቱም ቀኖች ልናከብር ይገባናል።" የሚለው ቃላቸው ነው።

**እዚህ ላይ በአንክሮ፥ በተዘክሮ ሊመረመርና ሊገመገም የሚገባው፡ አንድ አስገራሚ ነገር አለ፤ ይህንም፡ እንዲህ በሚል አጭር ዐረፍተ ነገር እንገልጸዋለን፡- እንኳንስ የአምላክ እናት የኾነችው፡ የቅድስት ድንግል ማርያም ይቅርና፡ የአንድ አረማዊ የልደት ቀን እንኳ፡ በዓመት ኹለት ጊዜያት፥ ያውም፡ በተለያዩ ዕለታት፡ ከቶ እንዲከበር ይደነገጋልን? አይደነገግም፤ ቀድሞውንስ፡ ይህ ነገር እንዴት ታሰባቸው? ያስገርማል።**

ይህ ግብራቸው፡ ለምን ያስገርመናል? የራሱን የፈጣሪያችንን የኢየሱስ መሲሕን የልደት ቀን፡ እንዲሁ፡ ከመስከረም ፩ ቀን፡ ወደታኅሣሥ ፳፰ ወይም ፳፱ ቀን፡ በድፍረት ወስደውት የለምን? ያውም፡ ለእግዝእተብሔራችን፡ ለድንግል ማርያም የቸሩትን ዕድል፡ ለእርሱ በመንፈግ? ለእርሷስ፡ ጽንሰቷና ልደቷ፡ በዓመት ኹለት ጊዜያት፡ በተለያዩ፡ ቀናት በተመደቡ በዓላትም ቢኾን፡ እንዲከበሩላት ፈቅደዋል።

<u>**ቀጥሎ፡-**</u> ልጇ፡ ኢየሱስ መሲሕ፡ የተስፋ ቃሉን፡ በጽኑ ታማኝነቱ ጠብቆ፥ የቀጠሮውንም ጊዜ፡ ለአንዲት ካልዕት እንኳ ሳያሳልፍ፡ በዚችው፡ ቀዳማዊው አዳም በተገኘባት፡ በመስከረም ፩ ቀን፡ ዳግማዊው አዳም ኾኖ እንደተወለደባት አምነን፡ እነሆ፡ እኛም፡ በቅዱሱ ኪዳን፡ የኢትዮጵያ ልጆች፡ በዚሁ እምነታችን፡ እየሠራንበት እንገኛለን:: እንደዚሁ ኹሉ፡ የዚያች የተስፋ ቃል፡ አማናዊት መፈጸም የኾነችው ድንግል ማርያምም፡ አርአያዋ የኾነችው፡ ቀዳማዊዋ ሔዋን በተገኘችባት፡ በመስከረም ፩ ቀን፡ ዳግማዊት ሔዋን ኾና እንደተወለደችበት መጠራጠርና ማስተባበል አይቻልም::

የእኒህ፡ የዳግማውያኑ አዳምና ሔዋን፣ ማለትም፡ የድንግል ማርያምና የኢየሱስ መሲሕ፡ በዚሁ፡ በመስከረም ፩ ቀን የመወለዳቸው ምስጢራዊ እውነታ፡ ቀዳማውያኑ አዳምና ሔዋንም፡ በ፲፰ ዓመታት የዕድሜ ልዩነት፡ በዚሁ፡ በመስከረም ፩ ቀን ለመገኘታቸው፡ ማረጋገጫ ነው:: ይኸውም፡ ጾታ-አልባ የነበረ፡ አንድ እግዚአብሔር፡ ረቂቁን እና ግዙፉን፣ ማለትም፡ መንፈሳዊዉን እና ሥጋዊዉን ፍጥረት የሚያስገኝበትን፣ ከዚያም፡ ያን ፍጥረቱን፡ የሚጠብቅበትን እና የሚያስተዳድርበትን፡ <u>**ቃሉን**</u> ለመውለድ፡ አንድ ራሱ፡ እግዚአብሔር አብ እና እግዝእተብሔር እም ኾኖ፡ የአንድነት ህላዌውን፡ በፈቃዱ፡ ወንድ እና ሴት አድርጎ፡ በኹለትነት ጾታ እንዳስገኘ ኹሉ፣ ኋላ ደግሞ፡ በዘመነ ፍጥረት፡ ልክ በዚያው አንድነት እና ጾታ-አልባነት፡ የአዳምን ሰብአዊ እና ኹለንተናዊ አካል፡ በእግዚአብሔራዊ መልክ በመፍጠር፣ **"ከእኛ ፡ ከኹለታችን፡ እንደአንዳችን፡ ወንድ እና ሴት ኾናችሁ!"** በማለት፡ አዳምን፡ የ፴ (ሠላሳ) ዓመት ጐልማሳ፣ ሔዋንንም፡ የ፲፰ ዓመት ቆንጆ አድርጎ በማስገኘቱ እውነታ ታውቋል።

<u>**በመጨረሻ፡-**</u> መነሻው፡ መስከረም ፩ ቀን የኾነውን፡ "ዓመተ ምሕረት" ላስገኘው፡ ለባሕረ ሓሳቡ አቀማመር፡ መሠረቱ፡ የልጇ፡ የኢየሱስ መሲሕ መወለድ እንደመኾኑ መጠን፡ ይኸው ዘለዓለማዊ ምሕረት ለተረጋገጠበት፡ ለአዲሱ ኪዳን፡ ሕያው ምልክት የኾነችው፡ እናቲቱ ድንግል ማርያምም፡ በዚሁ የምሕረት ጸጋ ውስጥ፡ በፍጹም ተዋሕዶ፡ አብራ የመገኘቷን ነገር፡ ፍጹም አስፈላጊ ያደርገዋል:: ያለእርሷ የቅድምና ልደት፡ ይህ የምሕረት ዓመት ሊኖር፥ ዘመኑም፡ "ተጀመረ!" ሊባል አይቻልምና::

ስለዚህ፡ "እግዚአብሔር፡ ይህን የምሕረት ጸጋውን፡ ለፍጥረቱ በመስጠቱ ረገድ፡ ለፈጸመው፡ ለዚህ መለኮታዊ ቸርነቱ እና ጥበባዊ ሥራው፡ ምክንያትና መሣሪያው ያደረጋትን፡ የቅድስት ድንግል ማርያምን የልደት ቀን፡ ጥንት፡ በሥነ ፍጥረቱ ልደት ጊዜ፡ የብርሃን ደጃፍን በከፈተበት፣ ኋላም፡ በፍጻሜ ዘመን፡ የዓመተ ምሕረቱ መግቢያ በኾነው፡ በዚሁ፡ በመስከረም ፩ ቀን እንዲኾን አደረገ!" ብሎ መደምደሙ ተገቢ ይኾናል::

"የሔዋን መገኘት፡ የ፴ ዓመት ጐልማሳ ኾኖ በቅድሚያ በተገኘው፣ በአዳም ላይ የተመሠረተ እንደነበረ ኹሉ፡ እግዚአብሔር ቃል፡ በኢየሱስ መሲሕ ሰውነት መገለጥ ደግሞ፡ በድንግል ማርያም ቀድሞ መወለድ ላይ ተመሥርቷል!" ማለት ነው።

በመሠረቱስ፡ "ኪዳነ ምሕረት" በማን ተገኘ? በእርሷ፡ በድንግል ማርያምና በልጇ፡ በኢየሱስ መሲሕ አንድነት አይደለምን? "ኪዳነ ምሕረት" የሚለው ስያሜስ፡ ለማን ተሰጠ? እግዚአብሔር ቃልን፡ በድንግልና ፀንሳና ወልዳ፥ አጥብታና አሳድጋ፡ በዘለዓለማዊ እናትነት ለምትኖረው፡ ለእርሷ፡ እግዝእተብሔር እም ለተዋሓደቻት፣ ለድንግል ማርያም አይደለምን? ለመኾኑ፡ የቀደመችው የብሉይ ኪዳኗ ጽላት፡ ያለታቦቷ፥ ታቦቷም፡ ያለጽላቷ፡ አንዳቸው፡ ያለአንዳቸው፡ ለየብቻቸው ሊኖሩ፡ ከቶ ይቻላቸው ነበርን? አይቻላቸውም። እንደዚሁ ኹሉ፣ የአዲስ ኪዳኗ ሕያውት ጽላት፡ ያለሕያዉ ታቦቷ፥ ሕያዉ ታቦቷም፡ ያለሕያውት ጽላቷ፡ አንዳቸው፡ ያለአንዳቸው፡ ለየብቻቸው ሊኖሩ፡ ከቶ አይቻላቸውም።

ስለዚህ፡ "ከማሕፀኗ ጀምሮ እስከዛሬ፡ በሰማያት፡ በሥጋና በነፍስ፥ በመንፈስም ያልተለያዩት፡ ኢየሱስ መሲሕ እና እናቱ ድንግል ማርያም፡ ለፍጥረተ ዓለሙ፡ ዓመተ ምሕረቱን፡ ማለትም፡ የምሕረቱን ዘመን ለማስገኘት፡ ሳይለያዩ፡ በእናትነት እና በልጅነት፣ የቅደም ተከተል ሥርዓት፡ ማለትም፣ በ፲፭ ዓመታት የዕድሜ ልዩነት፡ በዚያችው፡ በአንዲቱ፡ በመስከረም ፩ ቀን፣ በሥጋ ተወልደው እንዲገለጡ፡ የእግዚአብሔር ፈቃድ ኾኖ፣ ፈቃዱ፣ በመለኮታዊ ጥበቡ ተፈጸመ!" ብሎ መደምደም፡ የፍጹም ሃይማኖት ጣፋጭ ፍሬ ለመኾኑ ሊጠረጠር ከቶ አይቻልም።

## ኢትዮጵያዊቷ ድንግል ማርያም፡ በኢየሩሳሌምና በእስራኤል የመገኘቷ ምስጢር።

"ድንግል ማርያም፡ ከኢትዮጵያ፡ ወደእስራኤል ምድር የኼደችው፡ በትንቢቱ መሠረት፡ ኢየሱስ መሲሕን፡ የይሁዳ ክፍል በኾነችው፡ በቤተ ልሔም ልትወልደው ነው!" ስለሚለው እምነት፥ በመሠረቱም፡ ስለእርሷ ኢትዮጵያነትና እግዚአብሔር ወልድ፡ ከእርሷ፡ በኢትዮጵያዊነት ስለመወለዱ፡ ከዚህ አስቀድሞ፡ በየሓተታው ከተገለጸው ጋር፡ እዚህ ላይ፡ ተጨማሪ ማስረጃዎችን እንሰጣለን።

ለዚህ የእምነት አቋም፡ ማረጋገጫ የኾነው ሓተታ፡ ቀደም ብለው ታትመው፡ ለንባብ በበቁት፡ "ኢትዮጵያዊው፡ በማንነቱ ፍለጋ!"፥ "ኢትዮጵያ፡ የዓለሙ መፋረጃ!" እና "Ethiopia: The Classic Case"፥ እንዲሁም፡ "ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊነት፡ ፩ኛ፥ ፪ኛ እና ፫ኛ"፥ ደግሞ፣ «ምሥራች! ከእናት ኢትዮጵያ፤ ለኢትዮጵያ ልጆች፤ ስለኢትዮጵያዊነት»፥ በቅርቡም፣ "አዳም እና ሔዋን፣ በኢትዮጵያ! ፩ኛ፥ ፪ኛ እና ፫ኛ" በተባሉት፡ ንቡረ እድ ኤርምያስ ከበደ ዓባይነሽ ባዘጋጇቸው መጻሕፍት ውስጥ ይገኛል።

*ያን ሓተታ መሠረት በማድረግ፥ ከዚያ የቀሩ ቁም ነገሮች ቢኖሩ፡ እነዚያን በማከል፡ ከዚህ የሚከተለውን መጠነኛ ማብራሪያ፡ እነሆ አቅርበንላችኋል፤ በማብራሪያው ውስጥ የተጠቃለሉት እነዚህ ቊም ነገሮች፡ እግዚአብሔር፡ ሰው ኾኖ፡ ፍጥረቱን ሊያድንበት ያዘጋጀውን መለኮታዊ ሥራ፡ እውን የሚያደርገው፡ እንዴትና በምን እንደኾነ፡ ለሰው ልጆች፥ በተለይም ላመኑበት ወገኖቹ፥ ይልቁንም፡ የቃል ኪዳን ልጆቹ ለኾኑት፡ ለኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት፡ እያከታተለ የገለጣቸው፡ የቅድሚያ ዕፁብ ድንቅ ሥራዎቹ ናቸው፤ እነርሱም፡ በተራቸው፡ የተስፋው ፋናና ማጽኛ፥ መፈጽምና ማኅተም ለኾነችው፡ ለቅድስት ድንግል ማርያም፡ ጥላና ምሳሌ፥ አርአያና ምልክት ኾነው በመታየት አገልግለውታል፡-*

*፩ኛ፡ ገና በፍጥረት መጀመሪያ፡* “**ወይቤላ እግዚአብሔር፡ ለአርዌ-ምድር፡-'እስመ ገበርኪዮ ለዝንቱ ግብር፡ ...አስተፃርር ማእከሌኪ፥ ወማእከለ ብእሲት፤ ማእከለ ዘርእኪ፥ ወማእከለ ዘርአ! ውእቱ፡ ለይዕቀብ ርእሰኪ! ወአንቲኒ፡ ዕቀቢ ሰኰናሁ!** *እግዚአብሔር አምላክም፡ የምድር እባብን፡ (ዲያብሎስን) እንዲህ አላት፡- 'ይህን ሥራ ሠርተሽዋልና፡ ...በአንቺ እና በሴቲቱ (በሔዋን) መካከል፥ በዘርሽ እና በዘርዋ (ከእግዝእተብሔር እም፡ ድንግል ማርያም በሚወለደው ልጇ) መካከል፡ ጠላትነትን አፀናለሁ፤ እርሱ (እግዚአብሔር ወልድ፡ ኢየሱስ መሲሕ)፡ ራስሽን እየተከታተለ ይቀጠቅጣል፤ አንቺም፡ ሰኰናውን እየተከታተልሽ ትነድፊያለሽ።'”*

*ይህ የኾነው፡ አዳምና ሔዋን በተፈጠሩባት፥ እግዚአብሔር፡ ከሰው ልጆች ጋር ላደረጋቸው፡ ለሰባቱ ቅዱሳት ኪዳናት መሠረት የኾነው፡ የአዳምና ሔዋን የጋብቻ ቃል ኪዳን በተፈጸመባት፥ የዔዶም ገነት በምትገኝባትና ለአራት ከሚከፈለው ወንዟ፡ አንዱ የኾነው፡ “ግዮን” በከበባት፡ በዚችው፡ በኢትዮጵያ ምድር ስለኾነ፡ የሰው፡ ማንነቱ የሚታወቀው ደግሞ፡ በተወለደባት ምድር በመኾኑ፡ የድንግል ማርያም ኢትዮጵያዊነት፡ የተረጋገጠበት የመጀመሪያው ማስረጃ ይህ ነው፡፡ (ዘፍጥ. ፪፥ ፰-፲፫፤ ፫፥ ፲፬-፲፭፡፡)*

*፪ኛ፡ የእግዚአብሔር ወገኖች የኾኑት፡ ደጋጎቹ ወንዶችና ሴቶች፡ እስከጥፋት ውኃ ድረስ፡ በኢትዮጵያ ኖረው፡ በኖኅና በቤተሰቡ አማካይነት፡ ከጥፋት ውኃ የዳኑባት፥ መቅዘፊያና ሰብአዊ ቀዛፊ ሳይኖራት፡ በመለኮት ኃይል ብቻ ተጠብቃ የተመራችውን መርከብ፡ እኛ ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት፡ “ድንግል ማርያም ናት!” እንላለን፡፡*

*በመጨረሻም፡ ኖኅና ቤተሰቡ፡ በኋላ ዘመን፡ በመልከ ጼዴቅ ተቈርቊራ፡ ሰው የሚኾነው አምላክ፡ ዓለሙን ለማዳን እንዲሰቀልባት ወደተመረጠችው፡ ወደኢየሩሳሌም ከተማ፡ የመጀመሪያዋን የመርከብ ጒዞ ፈጽመውና ከሞት ተርፈው፡ ከእግዚአብሔር ጋር፡ ላደረጉት ቃል ኪዳን፡ ምልክት የኾነችው ቀስተ ደመና፡ “ድንግል ማርያም ናት!” ብለን እንናገራለን፡፡ ከዚህ የተነሣ፡ በእርሷ፡ቃል ኪዳኑን፡ ፍሬያማው አንድነታችን፥ መርከቧን፡ ቤተ መቅደሳችን/ቤተ ክርስቲያናችን፥ “የማርያም መቀነት” የምንለውንም የቀስተ ደመና ምልክት፡ ሰንደቅ ዓላማችን አድርገንና እርሷን፡ የተንዠረገገ የፈትል ጥልፍ ቀሚስን በተላበሰ የተዋበ የሴት ወገቧ ላይ አስታጥቀን፡ “እናት አገራችን፡ ኢትዮጵያ” በሚል ስሟ፡ የምናውቃት፥ የምንጠራትና የምንሥላት መኾናችን፡ ይህ፡ ኹለተኛው ማስረጃ ነው፡*

፫ኛ፡ እግዚአብሔር፡ ሙሴን፡ ወደግብፅ ልኮት፡ የእስራኤልን ልጆች፡ ከፈርዖን ባርነት፡ ነጻ ከማውጣቱ በፊት፡ በቅድሚያ፡ ወደኢትዮጵያ እንዲመጣና ኢትዮጵያዊት ሚስት አግብቶ፡ በዚያ፡ እንደእስራኤላውያን ልማድ፡ ብዙ ሚስቶችን በማግባት ሳይኾን ፤ በእግዚአብሔር ሥርዓት፡ በአንዲት ሚስት ተወስነው እንደሚኖሩት፡ እንደኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት፡ እስከመጨረሻው፡ በእርሷ፡ በአንዲት ሚስቱ ብቻ ተወስኖ እንዲኖር ለምን አደረገ?

እግዚአብሔር፡ ለዚህ፡ መለኮታዊ ምክንያት አለው፡፡ ሙሴ፡ የኢየሱስ መሲሕ፡ ቀዳሚ ምሳሌና አርአያ ሲኾን፡ የኢትዮጵያዊው ካህን፡ የዮቶር ልጅ የኾነችው ሚስቱ ሲጳራ ደግሞ፡ የድንግል ማርያም ቀዳሚት ምሳሌና አርአያ መኾኗን ጭምር ሊያሳይ በመኾኑ፡ ይህ እውነታ፡ የድንግል ማርያምን ኢትዮጵያነት ለማሳየት፡ ሦስተኛው ማስረጃ ነው፡፡

፬ኛ፡ ከአዳምና ሔዋን ጀምሮ፡ እስከ ሙሴ ዘመን ድረስ፡ በኪዳነ ልቦና ጸንቶ የቆየው፡ የዐሥሩ አምላካውያት ቃላት ሥርዓት [ትእዛዛት፣ ሕግ]፡ በኢትዮጵያውያንና በኢትዮጵያውያት የልብ ጽላት ላይ ተጽፎ እየተሠራበት ሣለ፡ በሙሴ መሪነት፡ ከግብፅ ባርነት፡ ነጻ የወጡት እስራኤላውያን ግን፡ በታላቅ ኃይሉ፡ ነጻ ያወጣቸውን፣ የዘር ግንዶቻቸውን፡ የአብርሃምን፥ የይስሓቅንና የያዕቆብን አምላክ፡ እንደኢትዮጵያ ልጆች፡ በዚያው፡ በኪዳነ ልቦና፡ በእውነትና በመንፈስ ሊያመልኩት ሳይፈልጉ ቀሩ፤ ከዚህ ይልቅ፡ በክህደትና በዓመፅ ተነሣሥተው፡ በጣዖት የማምለክ ዝንባሌን ስላሳዩ፡ እግዚአብሔር፡ ያን ሕጉን፡ እነርሱ እንደፈለጉት፡ በጣዖት መልክ፡ በኹለት የድንጋይ ጽላት (ሰሌዳዎች) ላይ፡ በጣቶቹ ጽፎና በታቦት (በሣጥን ውስጥ የሚቀመጡ) አድርጎ፡ እንደሰጣቸው ይታወቃል፡፡

ይኹን እንጂ፡ እነርሱ፡ በቃል ኪዳኑ ሕግ ውስጥ ያሉትን ትእዛዛት መፈጸም አቅቷቸው ስላፈራረሷቸው፥ ከዚህም የተነሣ፡ የኃጢኣታቸው ጽዋ ስለሞላ፡ እነርሱና አገራቸው፡ በአረማዊው ናቡከደነጾር ሠይፍ እንደሚደመሰሱ፡ በአምላካቸው ዘንድ ታወቀ፤ ያ፡ ታላቅ ጥፋት ከመድረሱም በፊት ግን፡ እግዚአብሔር፡ እነዚያን ጽላት የያዘችው፡ ያች ታቦተ ሕጉ፡ ወደኢትዮጵያ እንድትመጣ አደረገ፤ እርሷም፡ "ቃል ሥጋ ኾነ!" እንደሚለው፡ እንደባለምሥራቹ (ወንጌላዊው) ዜና፡ የአምላክ ሰው መኾን፡ በእውን እስከተፈጸመበት ጊዜ ድረስ፡ በኢትዮጵያ ኖረች፤ ይህም እውነታ እርግጥ መኾኑን፡ ማስተባበል የሚቻለው፡ ማንም የለም።

ጽላቱ፡ ሰውነትን፡ ማለትም፡ ነፍስንና ሥጋን፣ መንፈስንም፡ ከድንግል እናቱ፡ በተዋሕዶ የለበሰው የአምላካችን፡ የኢየሱስ መሲሕን ትስብእትና መለኮት፥ ጽላቱን የያዘችው ታቦት ደግሞ፡ የቅድስት እናቱ ምሳሌ በመኾናቸው፡ ኢየሱስ መሲሕን የወለደችው ድንግል ማርያም፡ ከኢትዮጵያ ምድር የተገኘች ኢትዮጵያዊት ለመኾኗ፡ ይህ፡ አራተኛው ማስረጃ ነው፡፡

፭ኛ፡- እግዚአብሔር፡ ኢትዮጵያዊቷ ንግሥት ማክዳ፡ በዚያን ጥንታዊ ዘመን፡ ብዙ ሠራዊት እና አያሌ ጓዝ የሚገኝበትን፡ ያን የሚያህል፡ አታካችና አዳጋች ረዥም ጉዞ፡ ወደኢየሩሳሌም እንድታደርግ፡ ለምን ፈቀደ? "**ወአመ ትፌጽም መዋዕሊከ፣ ወትሰክብ ምስለ አበዊከ፡ አቀውም ዘርአከ እምድኅሬከ፣ ዘይወጽዕ እምከርሥከ። ወአስተዴልዋ ለመንግሥቱ። ...ወለዓለም አቀውም መንበሮ። ወአነ እከውኖ አባሁ፤ ወውእቱ ይከውነኒ ወልድየ።**

"ዕድሜህ በተፈጸመ ጊዜ፣ እንደአባቶችህም ባንቀላፋህ ጊዜ፣ ከአብራክህ የሚወጣ ልጅህን፡ ከአንተ በኋላ አስነሣለሁ! መንግሥቱንም አዘጋጃታለሁ። ...የመንግሥቱንም ዙፋን፡ ለዘለዓለም አጸናለሁ። እኔም፡ አባት እኾነዋለሁ፤ እርሱም፡ ልጅ ይኾነኛል::" ብሎ፡ ለልበ አምላኩ ለቅዱስ ዳዊት፡ የገባለትን ቃል ኪዳን ሊፈጽም አይደለምን? አዎን! በእርግጥ ነው እንጂ።

እነሆ፡ ንግሥት ማክዳ፡ ይህ፡ መለኮታዊ የተስፋ ቃል፡ "የዳዊት ልጅ!" በተባለው፡ በኢየሱስ መሲሕ የተፈጸመበትን፡ የእግዚአብሔርን ልጅ የወለደች፡ ድንግል ማርያምን ያስገኘውን፡ የቃል ኪዳን ዘር፡ ከዳዊት ልጅ፡ ከንጉሥ ሰሎሞን ተቀብላ (ፀንሳ)፡ ወደአገርዋ፡ ወደኢትዮጵያ ተመለሰች::

እንግዴህ፡ በኢየሩሳሌም የነገሠው፡ የነቢዩ ዳዊት ልጅ፡ እስራኤላዊው ንጉሥ ሰሎሞን፡ የኢየሱስ መሲሕ ቀዳሚ ምሳሌና አርአያ ሲኾን፡ የመልከ ጼዴቅ ዘር የኾነችው፡ ኢትዮጵያዊቷ ንግሥት ማክዳ ደግሞ፡ የድንግል ማርያም ቀዳሚ ምሳሌና አርአያ ናት፤ ይህም፡ "ንግሥተ አዜብ ትትነሣእ "**ንግሥተ አዜብ ትትነሣእ፡ አመ ዕለተ ደይን፡ ምስለ ዛ ትውልድ፤ ወትትፋትሓ፥ ወታስተኃፍራ፤ እስመ መጽአት እምአጽናፈ ምድር፡ ትስማዕ ጥበቢሁ ለሰሎሞን፤ ወናሁ፡ ዘየዐቢ እምሰሎሞን፡ ሀሎ ዝየ።**

"ንግሥተ ዓዜብ፡ [ኢትዮጵያ] በፍርድ ቀን፡ ከዚህ ትውልድ ጋር ተነሥታ ትፋረደዋለች፤ ታሳፍረዋለችም፤ የሰሎሞንን ጥበብ ለመስማት፣ [እውነተኛነቱንም፡ በእንቆቅልሽ ጥበቧ ትፈትነው ዘንድ]፡ ከምድር ዳር መጥታለችና:: እነሆም፡ ከሰሎሞን የሚበልጥ፡ ከዚህ አለ!" በሚለው፡ በራሱ በጌታ ቃል ተረጋግጧል::

ስለዚህ፡ ይህ፡ የንግሥተ ሳባ ኢትዮጵያዊነትና በእርሷ የተፈጸመው፡ መለኮታዊ ዕቅድ፡ ድንግል ማርያም፡ ኢትዮጵያ ለመኾኗ፡ አምስተኛው ማስረጃ ነው:: (፪ሳሙ. ፯÷ ፲፪-፲፮፤ ማቴ. ፲፪÷ ፵፪::)

፯ኛ:- **"ኢትዮጵያ ታበጽሕ እደዊሃ ኀበ እግዚአብሔር! ኢትዮጵያ፡ እጆቿን፡ ወደእግዚአብሔር ታደርሳለች!"** ተብሎ፡ በአምላካዊ ቃል የተነገረላት ሰብአዊት ፍጡር፡ ድንግል ማርያም ካልኾነች በቀር፡ ይህ ማንነት፡ ከቶ፡ ለሌላ፡ ለማን ሊኾን ይችላል? መቼም፡ ቃሉ፡ ምድርን÷ አገርን፥ ወይም ግዑዝ አካልን የመሰለ፡ ሌላ ነገርን የሚወክል አይደለም፤ እንደቃሉ አነጋገር፡ ዘርግታ ወደእግዚአብሔር ያደረሰቻቸው እጆች ያሏት÷ ለዘለዓለምም፡ ሕያውት ኾና፡ በምድር ላይ፡ በሰብአዊት ሴት አንቀጽ፡ "ኢትዮጵያ" በሚል ስሟ ስትጠራ የምትኖር÷ እጆቿን፡ እንዲህ ወደእግዚአብሔር ዘርግታ ያደረሰች፥ መልካሙንም ዘለዓለማዊ ምላሽ፡ ከፈጣሪዋ ያገኘች፡ ሰብአዊት ፍጡር፡ ከድንግል ማርያም በቀር፡ ሌላ ፍጡር ሊኖር ከቶ አይችልም::

አዎን! በመላው የሰው ልጆች እና በፍጥረቱ ኹሉ ስም፡ እጆቿን፡ ወደእግዚአብሔር ዘርግታ፡ በፍጹም ብቅዓት ያደረሰችው መልእክት፡ ከሥሉስ ቅዱስ መንበረ ጸባዖትነቷ ቀርቦ፡ የቅዱሱ ኪዳን፡ የመጨረሻ ማኅተም የኾነውን፡ የምሕረት ቃል ኪዳን፡ ኢየሱስ መሲሕን ያስገኘችው፡ ያች "ኢትዮጵያ"፡ ድንግል ማርያም ለመኾኗ፡ ይህ፡ ስድስተኛው ማስረጃ ነው:: (መዝ. ፷፯÷ ፴፩::)

፯ኛ፡ **“'አኮ ከመ ደቂቀ ኢትዮጵያ፡ አንትሙ በኀቤየ! ደቂቀ እስራኤል።' ይቤ እግዚአብሔር፤ ዘኵሎ ይመልክ ስሙ።** 'የእስራኤል ልጆች! እናንተ፡ በእኔ ዘንድ፡ እንደኢትዮጵያ ልጆች አይደላችሁም።' ይላል፡ ስሙ፡ 'ኵሉን የሚገዛ!' የኾነ እግዚአብሔር፡፡” የሚለው፡ የነቢዩ ቃል፡ በመጀመሪያ፡ ስሙ፡ “እስራኤል” የኾነ፥ ብዙዎች ልጆችም ያሉት ሰው መኖሩን ያመለክተናል፡፡ ታዲያ፥ ይህ ሰው፡ እርሱ ማነው? ሰብአዊ ፍጡር የኾነው፡ በወንድ አንቀጽ የሚጠራው፡ የአብርሃም ልጅ የኾነው፡ የይስሓቅ ልጅና የዔሳው መንትያ፡ ያዕቆብ አይደለምን? አዎን! ነው። “እስራኤል”፡ ቀድሞ፡ የእግዚአብሔር ወልድ፥ ኋላም፡ የኢየሱስ መሲሕ ስም መኾኑ፥ ይህንንም ስም ለያዕቆብ የሰጠው፡ እርሱ ራሱ የስሙ ባለቤት መኾኑ ይታወቃል፡፡

ይኸውም፡ ቀድሞ፡ በብሉዩ ኪዳን፡ **“ወይቤሎ ኢይኩን እንከ፡ ስምከ፡ 'ያዕቆብ'! ዳዕሙ፡ ይኩን ስምከ፡ 'እስራኤል'! እስመ ክህልከ [ተጋድሎ] ምስለ እግዚአብሔር፥ ወምስለ ዕጓለ እመሕያው።** ከእንግዲህ ወዲህ፡ ስምህ፡ 'እስራኤል' ይባል እንጂ፡ ያዕቆብ አይባል! ከእግዚአብሔር፥ ከሰውም ጋር መታገል ችለሃልና!” ተብሎ የተጻፈው ቃል፥ ኋላም፡ **“እስመ ሕፃን ውእቱ እስራኤል፤ እስመ አነ አፍቀርክዎ፤ እምግብፅ ጸዋዕክዎ ለወልድየ።** እስራኤልን፡ ሕፃን በነበረ ጊዜ ወደድሁት፤ ልጄንም፡ ከግብፅ ጠራሁት።” ተብሎ፡ በሙሴ መሪነት፡ ከግብፅ ባርነት ነጻ በወጡት በእስራኤል ሕዝብ አስመስሎ፡ ነቢዩ የተናገረው ትንቢት፡ በኢየሱስ መሲሕ የተፈጸመ በመኾኑ ነው፡፡

አዎን! ፈጣሪያችን ኢየሱስ መሲሕ፡ በሕፃንነቱ፡ ከእናቱ፡ ድንግል ማርያም ጋር፡ ወደግብፅ ተሰድዶ፥ እዚያም፡ የኢትዮጵያውያንና የኢትዮጵያውያት ርስት በኾነችው፡ በቍስቋም ገዳምና በኢትዮጵያ፡ ቆይቶ፡ ከሦስት ዓመት ተኩል በኋላ ወደናዝሬት ስለመመለሱ፡ የአዲስ ኪዳኑ ባለምሥራች ሲጽፍ፡ ይህንኑ፡ **“ልጄን፡ ከግብፅ ጠራሁት!”** የሚለውን ቃል እንደጠቀሰው ይታወሳል፡፡

እንግዴህ፡ ከላይ፡ በ፯ኛው ተራ ቁጥር የተጠቀሰው፡ “ኢትዮጵያ” የሚለው ስያሜ፡ ለማን ሊሰጥ እንደሚገባ፥ ለማንስ እንደተሰጠ፡ ስለ“እስራኤል” የተነገረው፡ ይህ የእግዚአብሔር ቃል፡ ያመለክተናል፡፡ ይኸውም፡ “እስራኤል” የተባለውን ኢየሱስ መሲሕን፡ ለወለደችው፡ ለድንግል ማርያም፡ የተሰጠ መኾኑ ነው፡፡ ይህን እውነታ ለመረዳት፡ “**'የእስራኤል ልጆች ሆይ! እናንተ፡ ለእኔ፡ እንደኢትዮጵያ ልጆች አይደላችሁም።' ይላል እግዚአብሔር፡፡”** የሚለውን፡ የራሱን፡ የነቢዩን ቃል በማስተዋል መመልከቱ ይበቃል፡፡

አዎን! እግዚአብሔር፡ እርሱን፡ በአምላክነቱ ፈልገው ላመኑበትና ለወደዱት፥ ቃሉንም ለጠበቁት ወላጆቻቸው፡ ለአብርሃምና ለይስሓቅ፥ ለራሱም ለያዕቆብ የሰጣቸውን ቃል ኪዳን በማጽናት፡ ስለስሙና ስለእነርሱ ፍቅር ሲል፡ በኋላ ዘመን፡ ልጆቻቸውን፡ የእግዚአብሔር ሕዝብ ሊያደርጋቸው ስለፈለገ፡ “እስራኤል” የሚለውን ስም እንደሰጣቸው ይታመናል፤ እንደዚሁ ኹሉ፡ በቀደመው ዘመን፡ ከእነርሱ፡ ከእስራኤል ልጆች ይልቅ፡ አስቀድመው ላወቁት፥ ላመኑበትና ለወደዱት፥ ቃሉንም ጠብቀው ለኖሩት ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት ደግሞ፡ እርሱን ለመውለድ በምትበቃው እናቱ ስም፡ የእርሷ **"የኢትዮጵያ ልጆች"** ተብለው እንዲጠሩ ፈቃዱ ኾነ ማለት ነው፡፡

ስለዚህ፡ ቀደም ብሎ ከተሰጠው ማብራሪያ ጋር፡ የራሱ የነቢዩ ቃል፡ “እስራኤል” የሚለው ስም፡ ኢየሱስ መሲሕን የሚመለከት÷ “ኢትዮጵያ” የሚለው ስያሜ ደግሞ፡ ድንግል ማርያምን የሚያመለክት መኾኑን÷ እንዲሁም፡ እግዚአብሔር፡ ከእስራኤላውያን ይልቅ፡ አስቀድሞ ያወቀውና የወደደው፡ ኢትዮጵያውያንንና ኢትዮጵያውያትን መኾኑን፡ በግልጽ ስለሚያረጋግጥ፡ ድንግል ማርያም፡ “ኢትዮጵያ” ለመኾኗ፡ ይህ፡ ሰባተኛው ማስረጃ ይኾናል:: (ዘፍጥ. ፴፪÷ ፳፰፤ አሞ. ፱÷ ፯፤ ሆሴ. ፲፩÷ ፩፤ ማቴ. ፪÷ ፲፭::)

ቀደም ብለው የተጠቀሱትን ማስረጃዎች የሚያጠናክሩ፡ ሌሎች፡ የገዘፉ እውነታዎችን፡ እዚህ ላይ ማከል ይቻላል:: ከእነዚህ መካከል፡ አንዱን እንጥቀስላችሁ! ይኸውም፡ ድንግል ማርያምን፡ እንዲህ፡ በሥጋ ጭምር የምንዛመዳት ብቻ ሳትኾን፡በመኾኗ፡ "እግዝእተብሔራችንና እናታችን÷ መድኃኒታችንና ሃይማኖታችን፤ አገራችንና ንግሥታችንም ናት!” ብለን፡ በስሟ፡ አገራችን፡ “ኢትዮጵያ”÷ ምድራችን፡ ርስቷ÷ ጉልቷ÷ እኛም፡ ልጆቿ፡ “ኢትዮጵያውያን÷ ኢትዮጵያውያት” ተብለን መጠራታችን ነው።

እንደዚሁ ኹሉ፡ ልጇን ኢየሱስ መሲሕንም፡ “ፈጣሪያችንና አምላካችን÷ አባታችንና ሰላማችን÷ ብቻ ሳይኾን፡ “ካህን፡ ሊቀ ካህናታችን÷ ንጉሥ፡ ንጉሠ ነገሥታችንም ነው!” ብለን፡ የነፍሳችንና የመንፈሳችን ብቻ ሳይኾን፡ የሥጋችንም ጌታና ባለቤት መኾኑን፡ ለዓለሙ ኹሉ፡ በይፋ ያረጋገጥንበት ብሔራዊ አቋማችን ይገኛል:: ያም፡ “**ሞአ አንበሳ፡ ዘእምነገደ ይሁዳ!** ከይሁዳ ነገድ የኾነው አንበሳ፡ ድል አደረገ!” የሚለውን መለኮታዊ ዓርማ፡ ብሔራዊ ማኅተማችንና በሰንደቅ ዓላማችን ላይ አሥፍረን፡ ማእከላዊ ምልክታችን በማድረጋችን ታውቋል::

መቼም፡ በሰብአዊው የሥጋ ዝምድና ሓረግ፡ በቀጥታ ያልተሣሠረውን÷ ወይም፡ ወገኑ ያልኾነውን፡ ማንንም ሰው፡ በዚያ ሰው አስገዳጅነት እና በጦር ኃይል ካልኾነ በቀር፡ በፈቃዱ አምጥቶና ተቀብሎ፡ በራሱ ላይ የሚያነግሥ፡ ሕዝብ÷ ወይም ኅብረተሰብ፡ በምድር ላይ ስለሌለ፡ ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያትም፡ ከድንግል ማርያም እና ከልጇ፡ ከኢየሱስ መሲሕ ጋር በሥጋ ዝምድና የተሣሠሩ ባይኾኑ ኖሮ፡ እርሱን፡ "ንጉሣችን!"÷ እርሷን፡ እናቱንም፡ "ንግሥታችን!" ብለው፡ በፍጹም ሃይማኖታዊ ፈቃደኛነትና ደስታ፡ በላያቸው ሊያነግሡዋቸው÷ መንግሥታቸውንም፡ "የራሳችን ነው!" ብለው ሊተዳደሩበት ባልተቀበሉም ነበር::

ይህን እውነታ፡ በንጽጽር አቅርቦ ለማሳወቅ፡ ርቆ ኼዶ፡ ሌላ ማረጋገጫ፡ መፈለግና ማሳወቅ አያሻም፤ አረማዊው ጲላጦስ፡ ሰላማችን ኢየሱስ መሲሕን፡ በአደባባይ፡ በፊታቸው አቁሞ፡ “**ለንጉሥክሙኑ እስቅሎ?** ንጉሣችሁን ልስቀለውን?” ብሎ፡ የአይሁድን ካህናትና ሕዝቡን በጠየቃቸው ጊዜ፡ “**አልብነ ንጉሥ፡ ዘእንበለ ቄሣር!** ከቄሣር በቀር፡ ሌላ ንጉሥ የለንም!” ብለው የሰጡት ቁርጥ ምላሽ ይበቃል::

ደግሞም፡ እኒሁ አይሁድ፡ ወንጀሉ ተገልጾ እንዲጻፍበት በፈለጉበት፡ በመስቀሉ ዓናት ላይ፡ ጲላጦስ፡ “**ኢየሱስ ናዝራዊ፡ ንጉሦሙ ለአይሁድ!** የአይሁድ ንጉሥ፡ የናዝሬቱ ኢየሱስ!” የሚል ቃልን በማስጻፉ፡ “**ኢትጽሐፍ፡ ከመ ውእቱ ንጉሦሙ ለአይሁድ! አላ፡ ለሊሁ ይቤ፡- 'ንጉሦሙ ለአይሁድ አነ!'** ራሱ፡ ‹'እኔ የአይሁድ ንጉሣቸው ነኝ!' አለ፤› ብለህ ጻፍ እንጂ፡ ‹እርሱ፡ የአይሁድ ንጉሥ ነው!› ብለህ አትጻፍ!” ሲሉ፡ እንደገና ያቀረቡለት ጥያቄያቸውና እርሱም፡ ለዚሁ ጥያቄያቸው፡ “**ዘጽሐፍኩ፣ ጸሐፍኩ።** እኔ፡ የጻፍሁትን ጽፌአለሁ።” ሲል የሰጣቸው ቁርጥ መልስ፡ የእውነታውን ንጽጽር፡ የበለጠ ያጎላዋል::

አይሁድ፡ በኢየሱስ መሲሕ ላይ ያላቸው የጥላቻ ተቃውሞ፡ ይህን በመሰለ ኹኔታ ተገልጾ የታየው፡ እርሱ፡ ራሱ ፈጣሪያችን ኢየሱስ መሲሕ፡ የሞት ፍርዱን በተቀበለበት ጊዜ ብቻ አልነበረም፤ ገና፡ ቀደም ብሎ፡ በኢየሩሳሌም ቤተ መቅደሳቸው ውስጥ እያስተማረ ሣለ ጀምሮ፡ ተከሥቶ ነበር፤ ያም የጥላቻ ተቃውሞ፡ ቀዳሚ ምሳሌው የኾነው ሙሴ፡ ኢትዮጵያዊት ሚስትን አግብቶ፡ ኢትዮጵያዊ በመኾኑ፡ ከሕዝበ አይሁድ ብቻ ሳይኾን፡ ከእኅቱ፡ ከሚርያምና ከወንድሙ፡ ከአሮን ሳይቀር የደረሰበትን የጥላቻ ተቃውሞን የመሰለ ነበር፡፡

ይኸውም፡ አይሁድ፡ በኢየሱስ መሲሕ ላይ የነበራቸው የጥላቻ ተቃውሞ፡ ኢትዮጵያዊ መልኩን በማየት፡ ማንነቱን ከመናቃቸው የተነሣ እንደነበረ፡ ራሱ፡ ኢየሱስ መሲሕ፡ እንዲህ ሲል፡ በአምላካዊ አንደበቱ በተናገረው ቃሉ የመሰከረው ነው፡- "**ወእመሰ በሰንበት፡ ግዝረተ ይነሥእ ብእሲ፡ከመ ኢይሰዐር ሕጉ ለሙሴ፡ ለምንት እንከ ትግእዙኒ፡ ለእመ አሕየውክዎ ለብእሲ፡ ኵለንታሁ በሰንበት? ኢትፍትሑ በአድልዎ ለገጽ! አላ፡ ፍትሐ ጽድቅ ፍትሑ!** የሙሴ ሕግ እንዳይሻር ብላችሁ፡ ሰውን፡ በሰንበት የምትገርዙ ከኾነ፣ ሰውን፡ ኹለናንተናውን፡ በሰንበት፡ ጤናማ ስላደረግሁ፡ ለምን ትቃወሙኛላችሁ? በእውነት ፍረዱ እንጂ፡ በሰው ላይ፡ መልክ አይታችሁ፡ በአድልዎ አትፍረዱ!" ስለዚህ፡ ይህን እውነታ ማስተባበል፡ የሚቻለው ማንም የለም። (ዮሐ. ፯፥ ፳፪-፳፬፤ ፲፱፥ ፲፰-፳፪፡፡)

እዚህ ላይ፡ ከዚህ ጋር ተያያዞ ሊብራራ የሚያስፈልገው፡ ሌላ፡ የእምነት ጥያቄ አለ፤ እርሱም፡ መልአኩ፡ ቅዱስ ገብርኤል፡ ለድንግል ማርያም፡ "**ወናሁ ኤልሣቤጥኒ፡ እንተ እምአዝማድኪ፡ ይእቲኒ ፀንሰት፥ ወረከበት ወልደ፡ በልህቃቲሃ፥ ወበርስአቲሃ፤** እነሆም፡ ዘመድሽ ኤልሣቤጥ፡ እርሷ ደግሞ፡ በእርጅናዋ፡ ወንድ ልጅን፡ ፀንሳለች! አግኝታለችም።" ሲል የተናገረው ቃል፡ ድንግል ማርያም፡ ኤልሣቤጥን የመሰሉ፡ ሌሎች ሴቶችና ወንዶች ዘመዶች፡ በዚያ አገር ያሏት መኾኑን የሚያመለክተው እውነታ ነው፡፡ ይህ ከኾነ፡ ይኸው እውነታ፡ ከእርሷ፡ ከእግዝእተብሔራችን እም፡ ድንግል ማርያም እና ከልጇ፡ ከእግዚአብሔራችን ወልድ፡ ኢየሱስ መሲሕ ኢትዮጵያዊነት ጋር፡ እንዴት ሊጣጣም እንደሚችል ማብራራት፡ አግባብ ይኾናል፡፡

በመጀመሪያ ደረጃ፡- ነቢዩ ዳዊት፡ "**የሳሌም ንጉሥ**" የተባለው አባቷ መልከ ጼዴቅ የቈረቈራትን "**ኢየሩሳሌም**"ን መነሻ አድርጎ፡ "**ኢትዮጵያ**" ስለተባለችው ድንግል ማርያም፡ በመዝሙሩ ሲተነብይ፡ "**ነኪር ነገሩ በእንቲአኪ፡ ሀገረ እግዚአብሔር። እዜከሮን ለረዓብ፥ ወለባቢሎን፡ እለ የአምራኒ። ወናሁ ኢሎፍሊ፣ ወጢሮስ፣ ወሕዝበ ኢትዮጵያ፤ እለ ተወልዱ በህየ።** የእግዚአብሔር ከተማ (ኢየሩሳሌም) ሆይ! ስለአንቺ የተነገረው ኹሉ፡ ዕፁብ ድንቅ ነው፤ …እነሆ፡ ፍልስጥኤማውያን፥ ጢሮስም፥ የኢትዮጵያም ሕዝብ፡ እነዚህ፡ በዚያ ተወለዱ፡፡" ብሎ የተናገረው ቃል፡ ለዚህ የእምነት ጥያቄ፡ መነሻ መልስ ነው፤ እኚህ የኢትዮጵያ ሕዝብ፡ ጥንት፡ ከመሥራቿ የዘር ግንዳቸው፡ ከመልከ ጼዴቅ ጀምሮ፡ የእርሷ፡ የኢየሩሳሌም ባላባትና ባለርስት ኾነው፡ በእርሱ ስም፡ ያለማቋረጥ ሲያስተዳድሩዋት የኖሩ፥ ዛሬም እየኖሩ ያሉ ለመኾናቸው መሠረታዊው ማስረጃ ይህ መኾኑ፡ ሊታወቅ ይገባል፡፡

"ንግሥተ ሳባ" የምትባለው፡ ኢትዮጵያዊቷ ንግሥት ማክዳ፡ ያን ኹሉ ጓዝ ይዛ፡ ወደኢየሩሳሌም ለመኼድ የቻለችው፡ ከዚሁ ባለቤትነት የተነሣ መኾኑም እንዳይዘነጋ ያስፈልጋል። **የአዲስ ኪዳኑ "አቤሜሌክ"**፥ ወይም፡ "ባኮስ"፥ የተባለው፡ ኢትዮጵያዊው ጃንደረባ፡ **"ሕንደኬ"** የተባለችው የኢትዮጵያ ንግሥት፡ የገንዘብ ምሉኳ [በጅሮንዷ] የኾነው ባለሥልጣን፡ በዚያን ጊዜ፡ ጸንቶ ይሠራበት በነበረው፡ በኦሪታዊው የኢትዮጵያ ሥርዓት፡ ሊሳለም ወደኢየሩሳሌም ኼዶ የተመለሰው፡ የኢትዮጵያ ሀብትና ንብረት፥ ርስትና ይዞታ ወደነበረው፡ ወደጋዛ መኾኑ፡ በሓዋርያት ሥራ መጽሓፍ ውስጥ ተጽፎ የሚነበበው ቃል፡ ይህን እውነታ አረጋግጦ ያስረዳል። (*መዝ. ፹፯፥ ፩-፯። ሉቃ. ፩፣ ፴፮። የሓዋ. ፰፥ ፳፯-፴፱።*)

<u>**በኹለተኛ ደረጃ፦**</u> እኛ ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት፡ ከመሲሕ [ከክርስቶስ] ልደት አንድ ሺ ዓመት በፊት፡ ታቦተ ጽዮን ወደኢትዮጵያ እስከመጣችበት ጊዜ ድረስ፡ በዚህ መልክ፡ በኢየሩሳሌም ነዋሪዎችና ተመላላሾች የነበርን ስንኾን፡ ከዚያ በኋላ፡ በታቦተ ጽዮን ባለአደራነታችን ምክንያት፡ እውነተኞቹ እስራኤላውያን ኾነን መገኘታችን ደግሞ፡ ሌላው እውነታ ነው። ከዚህ የተነሣ፡ በኦሪቱ ሕግና ሥርዓት አፈጻጸም በኩል፡ በሥጋዊዉ ኾነ በመንፈሳዊው፥ በሃይማኖታዊዉም ይዞታ ረገድ፡ በኢትዮጵያም፥ በኢየሩሳሌምም፡ በነበረን ባለመብትነት፡ በኹለቱም ምድሮች፡ ያለችግር እንኖር የነበርን መኾኑ አያጠያይቅም፤ እንዲህ ከኾነ ደግሞ፡ በዚያን ጊዜ፡ እንደዛሬው ኹሉ፡ የኢትዮጵያውያን እና የኢትዮጵያውያት፡ በኢየሩሳሌምና በአካባቢ አውራጃዎቿ፡ በብዛት መገኘትና ነዋሪ መኾን፥ እርስ በርሳቸው ተጋብተውና ተዋልደው መኖራቸውም፡ በምንም መልኩ፡ እንደእንግዳ ነገር ተቆጥሮ፡ ሊያስደንቅ ከቶ አይችልም።

ስለዚህ፡ እንኳንስ፡ ትንቢት እያለ፡ ባይኖርም፡ እንኳ፡ እግዝእተብሔራችን፡ ቅድስት ድንግል ማርያም፡ ሳትወለድ፡ ወላጆቿ፥ ወይም፡ አያቶቿ፥ ወይም ቅድመ አያቶቿ፡ ወደኢየሩሳሌም ኼደው፡ በዚያ፡ ጊዜያዊ ቆይታ፥ ዘመድ ጥየቃ፥ ወይም ጉብኝት ቢያደርጉ፥ ወይም ኑሮ ቢመሠርቱ፥ ከዚህም የተነሣ፡ የካህኑ ዘካርያስ ሚስትና የመጥምቁ ዮሓንስ እናት የኾነችውን፡ ኤልሣቤጥን የመሰሉ፡ ብዙ ኢትዮጵያውያን ወንድሞችና አኅቶች፥ ብዙ ኢትዮጵያውያት እኅቶችና አክስቶች፥ ሌሎችንም፡ የቅርብና የሩቅ ዘመዶችን አፍርተው ቢገኙ፡ አግባብና የሚጠበቅ ውጤት ከመኾኑ በቀር፡ አፍራሽ ትርጉም ሊሰጠው ከቶ አይቻልም።

እንዲያውም፡ "ኤልሣቤጥ" የሚለው የስም አጠራር፡ በአይሁድ ዘንድ ስለሌለ፥ ምንም እንኳ፡ ባለምሥራቹ ሉቃስ፡ የእውነተኞች ኢትዮጵያውያት መለያ በኾነው እስራኤላዊትነቷ፡ "ከአሮን ልጆች ነበረች፤" ቢላትም፡ ያ ስሟ፡ ኢትዮጵያዊ መኾኑ፡ በእርሷና በድንግል ማርያም ማንነት ይረጋገጣል፤ ይኸውም፡ በኢትዮጵያ ልጆች ዘንድ እንጂ፡ በእነርሱ፡ በአይሁድ ዘንድ የሌለውን፡ "ኢየሱስ" እና "ዮሓንስ" ብሎ፡ ለገንና ለመጥምቁ፡ አዳዲስ ስሞችን ባወጣላቸው፡ በመልአኩ፡ በቅዱስ ገብርኤል አንደበት፡ ኤልሣቤጥ፡ የድንግል ማርያም ዘመድ መኾኗ ስለተነገረ ነው። ይህም፡ ለተነሣንበት የእውነት ፍለጋ፡ ተጨማሪ ማስረጃ ሊኾነን ይችላል። (፩ነገ. ፲፥ ፩-፲፫። መዝ. ፹፯፥ ፫-፬። ሉቃ. ፩፥ ፭፡ ፲፫፡ ፴፯፡ ፶፱-፷፫።)

# የኢየሱስ መሲሕ በዓለ-ልደት።

በዚህ፡ በመስከረም ፩ ቀን በሚውለው የበዓል ዕለት ከሚታሰቡት፡ ከኢትዮጵያ ነጻነት እና ከሌሎቹ ታላላቅ ብሔራውያን ምክንያቶች ጋር ተዋሕዶ የሚዘከር፣ ጥልቅ የኾነ መንፈሳዊ አንክሮንና ተዘክሮንም የሚያሳድርብን፡ ቀዳሚ የኾነ፡ አንድ ታላቅ የእውነት ቊም ነገር አለ፤ ያም፡- በተለይ፡ እግዝእተብሔር እም፡ በሰውነት ከተገለጠችባት፡ ከድንግል ማርያም የትስብእት ልደት ጋር የተያያዘው፡ የፈጣሪያችን እና የሰላማችን፡ የእግዚአብሔር ወልድ፡ ኢየሱስ መሲሕ፡ የትስብእት ልደት ኾኖ ይገኛል። እሱም፡ "**አነ፥ ወአብ፡ አሐዱ ንሕነ!** እኔ እና አብ፡ አንድ ነን!" ባለው፡ በእግዚአብሔር ወልድ፡ ኢየሱስ መሲሕ ሰውነት፡ እግዚአብሔር አብ የተገለጠበት ነው። ይህ በመኾኑ፡ እግዚአብሔር አምላክ፡ ሰውን፡ በዚህ የፍጹምነት መጠን፡ ከመውደዱ የተነሣ፡ ራሱን፡ እስከመጨረሻው ደረጃ አዋርዶ፡ በሰውነት መወለዱ ብቻ ሳይኾን፡ እንደነገሥታት ልጆች፡ በቤተ መንግሥት መቀማጠሉ ቀርቶበት፥ ከድኃ ሴት እንደተወለደ ሕፃንም እንኳ፡ በደሳሳ ጎጆ ውስጥ፡ መጠጊያ ማግኘት በዝቶበት፡ በሰውነት ኑሮ፡ እጅግ ወራዳ እስከኾነው ዝቅጠት ደርሶ፡ ልደቱን፡ በእንስሳት በረት ማድረጉ ነው:: (ዮሐ. ፲፥ ፴፤ ፲፯፥ ፲፩ እና ፳፪።)

ለዓለማቱ ፈጣሪና ባለቤት፡ አልጋው፥ ፍራሹና ብርድልብሱ፥ መደቡም ቀርቶበት፥ የሚጠቀለልበትም በቂ ጨርቅ እንኳ ታጥቶ፡ የተኛው፡ በሣር ጒዝጓዝ በተሸፈነ፡ በባዶው መሬት ላይ ሲኾን፥ ከበረቱ የሌሊት ብርድ ያማሟቁት፡ በበረቱ ውስጥ የነበሩት እንስሳት ናቸው:: በዲያብሎስ የባርነት አገዛዝ፥ የኃጢኣት ቀንበርና የሞት ፍዳ ተቀፍድዶ ይማቅቅ የነበረው ፍጥረት፡ በቃተተ ተስፋ ይጠባበቀው የነበረውን፡ የእግዚአብሔር ወልድን፡ ከእግዝእተብሔር እም ድንግል ማርያም የመወለዱን ምሥራች፡ ከሰማይ መላእክት የሰሙት፡ በእልፍኝ የሚኖሩት፡ ቅምጥሎቹ ምሉካንና ካህናት፥ መኳንንትና የሕዝብ አለቆች ሳይኾኑ፡ ከመንጎቻቸው ጋር በሜዳ ያደሩ፡ ምስኪኖቹ የገጠር እረኞች ናቸው::

አዎን! አምላካችን፡ ስለእኛ ሲል፡ ከነእናቱ የተቀበላቸውን መከራዎች፡ መቋቋም የጀመረው፡ ገና በማሕፀን ሣለ አንሥቶ መኾኑ፡ ከዮሴፍ ጥርጣሬና ከአይሁድ ጥላቻ መንጭቶ በደረሰበት እንግልት ይታወቃል፤ ከፅንሰቱ በኋላ የቀጠለው፡ ይኸው መከራው፡ እነሆ፡ በበረትም ተከሠተ! እንግዴህ፡ ፈጣሪያችን እግዚአብሔር፡ እኛን፡ የጠፋነውን በጎቹን፡ እንደቃል ኪዳኑ ሊፈልገንና ሊያድነን የመጣው፥ ያዳነንም፡ እንዲህ አድርጎ ነው::

ታዲያ! ለዚህ ፍቅሩና ቤዛነቱ፡ የምንመልስለት ውለታ፡ ከቶ ምንድር ነው? እርሱ እንደወደደን፥ እኛም፡ እርሱን መውደድ መኾኑን፥ እርሱን መውደዳችንንም፡ የምናውቀው፡ ጠላቶቻችንን ሳይቀር፡ ሰውን ኹሉ ስንወድድ መኾኑን፡ ራሱ ነግሮናል:: ይህን ትሩፋት ማድረግ የምንችለው፡ እግዚአብሔርንና ሰውን ያስታረቀ፥ ሥጋንና ነፍስንም ያስማማ፡ እውነተኛ ሰላማችን፡ እርሱ፡ ኢየሱስ መሲሕ፡ ቅዱስ መንፈሱን፡ በሰውነታችን ውስጥ ያሳድር ዘንድ፡ የየልቦናችንን በር እያንኳኳ ነውና፡ ስንከፍትለት ብቻ ነው:: ስለዚህ፡ የየልቦናችንን በር እንክፈትለት እንጂ፡ “እንቢ!” አንበለው! እያንዳንዳችንንም፡ በየስማችን እየጠራን ነውና፡ “አቤት!” ብለን፡ ፈቃዱን እንፈጽም!

# የኢየሱስ መሲሕ የልደት በዓል፡ መስከረም ፩ ቀን ስለመኾኑ፡፡

“የኢየሱስ መሲሕ የልደት በዓል፡ በታኅሣሥ ፳፱ ቀን ይውላል!” ተብሎ፡ እስከዛሬ፡ በዚህ መልክ ሲከበር ስለመቆየቱና አኹን፡ ይኸው፡ የእግዚአብሔራችን የኢየሱስ መሲሕ፡ እውነተኛው የልደት ቀን፡ “መስከረም ፩ ቀን ስለኾነ፡ በዚሁ ቀን ሊኾን ይገባል!” ስለሚያሰኘው ምክንያት፡ ከዚህ የሚከተለውን፡ ጠለቅና ሰፋ ያለ መግለጫ መመልከቱ ይጠቅማል፡፡

ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት፡ “ዓመተ ምሕረት ገባ! ተጀመረ!” ብለው፡ በታላቅ ደስታና ምስጋና፡ የሚያከብሩት፡ ዋናው የዐውደ ዓመት በዓላቸው፡ እስከዛሬ፡ እስከ፳፻፲ [፪ሺ፲) ዓመተ ምሕረት ድረስ፡ ይኸው፡ መስከረም ፩ ቀን መኾኑ፥ ዘመኑንም፡ ዓመተ ፍዳ ተወግዶ፡ ዓመተ ምሕረት መተካቱን አረጋግጦ ለማሳወቅ፡ “ዓመተ ምሕረት” አሰኝቶ፥ ዓመቱን፡ ፩ ብሎ እንዲጀመር ያደረገው፡ ይኸው የኢየሱስ መሲሕ ልደት መኾኑ፡ ሊታበል የማይቻል ሕያው ኾኖ፡ በኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት ዘንድ፡ እስከዛሬ ድረስ፡ በገሃድ ሲፈጸም የኖረ፥ ዛሬም እየተፈጸመ ያለ፡ ቋሚ እውነታ ነው፡፡

የቤተ ክህነት ሊቆቻችንም፡ በረቡዕ ውዳሴ ማርያም ትርጓሜ ማብቂያ ላይ፡ “አድኃነ ነፍሳቲነ በምጽአቱ ቅዱስ”፡ ማለትም፡ እግዚአብሔር ወልድ፡ "በልዩ አመጣጡ፡ ሰው ኾኖ፡ ነፍሳችንን አዳነ!” ብለው፡ ቃል ለቃል የተረጎሙትን ኃይለ ቃል፡ “የቀደመው የረድኤት፡ ማለትም፡ በመንፈስ፡ ነው፤ የዛሬው የኩነት፡ ማለትም፡ ራሱ፡ ሰው ኾኖ፡ በሕያው ሥጋ የፈጸመው ነው!”የሚል አጭር ሓተታን ከሰጡት በኋላ፡ በቀጠለው አንድምታቸው፡ “በጽኑ ቀጠሮው መጥቶ አዳነን፤ 'በጽኑ ቀጠሮው አለ!' አምስት ሺ ከአምስት መቶ ዘመን ሲፈጸም፡” ቀጠሮውን፡ ማለትም፡ በድንግል ማርያም ማሕፀን ተፀንሶ፡ ከእርሷ የተወለደባትን ጊዜ፡ “ለአንዲት ሰዓት እንኳ አላሳለፈምና!” ብለው የምስጢር ፍቻቸውን ያቆማሉ፡፡

በእግዚአብሔር የእውነት ቃልና ዕፁብ ድንቅ ሥራው፥ እስካኹን ጸንቶ በቀጠለውም፡ በኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት የዘመን አቆጣጠር ሥርዓት፥ እንዲሁም፡ “ጽኑ ቀጠሮውን፡ ለአንዲት ሰዓት እንኳን አላሳለፈም” በሚለው፡ በውዳሴ ማርያሙ ትርጓሜ መሠረት፡ ኢየሱስ መሲሕ፡ ከድንግል ማርያም የተወለደባትን ጊዜ፡ በጳጉሜ ፭ ቀን፥ ፭ሺ፭፻ ዓመተ ዓለምና ዓመተ ኪዳን፡ ከሌሊቱ ልክ ፮ ሰዓት ሞልቶ፡ አንዲት ካልዕት ለማትሞላ አፍታ፡ ጥቂት እልፍ ብላ በነበረችው ቅጽበት ውስጥ መኾኑ ነው፡፡ መስከረም ፩ ቀን፥ ፩ ዓመተ ምሕረት ተብሎ፡ የዓመተ ምሕረት ዘመን አቆጣጠር የጀመረውም፡ ከዚያች፡ የዓመተ ኵነኔ፡ ወይም የዓመተ ፍዳ ማብቂያ ከኾነችው፡ ከጳጉሜዋ ፭ ቀን፥ ፭ሺ፭፻ የፍጥረቱ ዓመተ ዓለም፥ የኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት ዓመተ ኪዳን፡ ከሌሊቱ ፮ ሰዓት በኋላ ከነበረችው ቅጽበት ጀምሮ ኾኗል!

“ለአንዲት ሰዓት እንኳ አላሳለፋትም” የተባለችው ጊዜ፡ “ከፅንሰቱ ይልቅ፡ ልደቱን ይመለከታል!” ማለቱ ትክክል ይኾናል፤ ምክንያቱም፡ ብሥራቱ፡ የእግዝእተብሔር እማችንን፡ ለአምላክ እናትነት መመረጥ ለማስታወቅ፡ በመልአኩና በእርሷ መካከል፡ በምስጢር የተካኼደ ንግግር ሲኾን፡ ልደቱ ግን፡ የሰማይ መላእክትና የምድር ሠራዊት በይፋ የተነጋገሩበት፥ “ለዓለሙ ኹሉ የሚኾን ታላቅ የደስታ ምሥራችን” የተሳተፉበት በዓል ስለኾነ ነው፡፡

ይህም: "**ወሀለዉ ኖሎት ውስተ ውእቱ ብሔር፤ ይትግሁ፤ ወይሔልዉ፤ ወየዐቅቡ መራዕይሆሙ፡ ሌሊተ፣ በበዕብሬቶሙ። ወናሁ ቆመ፡ መልአከ እግዚአብሔር ኀቤሆሙ፤ ወስብሓተ-እግዚአብሔር፡ ሠረቀ ላዕሌሆሙ። ወፈርሁ ዐቢየ ፍርሀተ። ወይቤሎሙ መልአክ፡- 'ኢትፍርሁ! እስመ ናሁ እዜንወክሙ፡ ዐቢየ ዜና ፍሥሐ፣ ዘይከውን ለክሙ፣ ወለኵሉ ዓለም። እስመ ናሁ፡ ተወልደ ለክሙ ዮም፡ መድኅን! ዘውእቱ መሲሕ፣ እግዚእ፥ ቡሩክ፣ በሀገረ ዳዊት!**

"በዚያም ምድር: መንጋቸውን: በየተራቸው: በሌሊት: ነቅተው እና ተግተው ሲጠብቁ: በሜዳ ያደሩ እረኞች ነበሩ:: እነሆም: የእግዚአብሔር መልአክ: ወደእነርሱ መጥቶ ቆመ። የእግዚአብሔር ክብርም በላያቸው አበራ! ታላቅ ፍርሃትም ዐደረባቸው። መልአኩም: እንዲህ አላቸው:- 'አይዟችሁ! አትፍሩ! እነሆ፥ ለእናንተና ለዓለሙ ኹሉ የሚኾን: ታላቅ የደስታ ምሥራችን እነግራችኋለሁና! ዛሬ: በዳዊት ከተማ: እግዚአብሔር ወልድ፡ በሰላሙ ሊያድናችሁ፡ ቡሩኩ መሲሕ ኾኖ ተወልዶላችኋልና!'" በሚለው የመልአኩ ቃል ተረጋግጦ ይታወቃል (ሉቃ. ፪፥ ፰-፲፬::)

እዚህ ላይ: "ለዓመተ ምሕረት የጊዜ አቆጣጠራችን: መሠረቱና መጀመሪያው፥ ለዓመተ ፍዳም: ድምድማቱና መጨረሻው: "**ቃል: ሥጋ ኾነ**! አምላክ ሰው ኾነ!" የተባለበት: የኢየሱስ መሲሕ የልደት ቀን ከኾነ፥ የተወለደባት ቀን ደግሞ: በጳጕሜ ፩ ቀን፥ ፭ሺ፭፻ ዓመተ ዓለም: ከሌሊቱ ልክ ፮ ሰዓት ላይ ከኾነ፥ አለዚያ: መቼም ሳይወለድ: "ዓመተ ምሕረት ገባ! ወይም ተጀመረ!" ማለት ስለማይቻል፥ በአጠቃላይ: እውነታው: ይህ ሲኾን ሣለ: *በግብፃውያን መነኮሳት እና ጳጳሳት: "ኢየሱስ መሲሕ: ተወልዶበታል! እርሱም: በየዓመቱ ታኅሣሥ ፳፱፥ በየአራት ዓመቱ ደግሞ: በታኅሣሥ ፳፰ ቀን ይውላል!" ተብለን* እንድናከብረው የተደረግነው: ይህ: የገና ወይም የልደት በዓል: ታዲያ ከየት መጣ?

"**በጽኑ ቀጠሮው: አንዲት ሰዓት እንኳ ሳያሳልፍ: ልክ: የ፭ሺ፭፻ው ዓመተ ፍዳ ሲያበቃ: ተወለደ!**" ብለን እያወጅን፥ **እውነታውም፡ ይህ ኾኖ ሣለ**: ***ለምን፥ ወይም፡ እንዴት: ከመስከረም ፩ ቀን በኋላ: አራት ወሮችን ቆይተንና አሳልፈን: "በታኅሣሥ ፳፰ ወይም ፳፱ ቀን ተወለደ!" ብለን: እንደገና በዓሉን እናከብራለን?*** የሚል ጥያቄ መነሣቱ አይቀርም::

ለዚህ ጥያቄ: የሚሰጠው መልስ: እንደሚከተለው ነው:- ይህን ግዙፍ ስሕተት ያደረሰው ማ መኾኑን ለማወቅ: እምብዛም አያዳግትም::

የግብፅ ኦርቶዶክሳውያን መነኮሳት እና ጳጳሳት: በዚህ ረገድ ብቻ ሳይኾን: የልደቱን ቀን: በየአራት ዓመቱ: በዘመነ ዮሓንስ: ከታኅሣሥ ፳፱: ወደኋላ: ወደታኅሣሥ ፳፰ ቀን "ይመለስ!" ብለው በፈጠሩብን ውዝግብ የተነሣ: ችግሩ እየጨመረ እንዲኼድ ተደርጓል።

ይህን ድርጊት "ትክክል ነው!" ብለው አምነው የተቀበሉ ወገኖች ካሉ: "ታዲያ! ለምንድር ነው: በዚያው ዓመት ውስጥ ተቀምረው የተወሰኑትን: ቢያንስ ቢያንስ: የድንግል ማርያምን እና የኢየሱስ መሲሕን በዓላት: በየአራት ዓመቱ: ወደኋላ: በአንድ ቀን እንዲቀነሱ ያላደረጉት?" ለሚለው ጥያቄ መልስ መስጠት ይኖርባቸዋል:: ከኹሉም ይልቅ: "የኢየሱስ መሲሕ የልደት በዓል ቀን: እንዲህ: በአንድ ቀን ተቀንሶ: ከታኅሣሥ ፳፱: ወደኋላ: ወደታኅሣሥ ፳፰ ቀን ከተመለሰ እኮ: ሌሎቹ ኹሉ: የዓመቱ በዓላትና አጽዋማት: እንዲሁ: በአንዳንድ ቀናት: በግድ: ወደኋላ መሸጋሸግ አለባቸው::

ስለዚህ፡ ከዚህ ኹሉ የማያስፈልግ ውዝግብና ችግር መዳን የሚቻለው፡ “ሰላማችን ኢየሱስ መሲሕ የተወለደው፡ አንድ ጊዜ ብቻ ስለኾነ፥ ተወልዶም፡ ተልእኮውን፡ ለአንዴና ለመቼውም ጊዜ ስለፈጸመ፥ በየዓመቱ የሚከበረው፡ የልደት በዓሉም፡ በመታሰቢያነትና ለመታሰቢያነት ብቻ በመኾኑ፡ በየአራት ዓመቱ፡ አንድ ቀንን እየተቀነሰ እንዲከበር ማድረጉን ትተን፡ በዚያው በታኅሣሥ ፳፱ ቀን እንጹና!” ማለት ይችሉ ነበር።

ይኹን እንጂ፡ ይህ ሳይኾን፡ እስካሁን ተኑርዋል። ስለዚህ፡ ለዚህ ቀላል ችግር፡ ይህ ውሳኔ፡ ጊዜያዊ መፍትሔ ሲኾን፡ ለዘለቄታው የሚኾነው መፍትሔ ግን፡ ይኼው የኢየሱስ መሲሕ፡ የልደቱ በዓል፡ ወደጥንታዊው እውነተኛ ዕለት ተመልሶ፡ በመስከረም ፩ ቀን እንዲውል ማድረግ ብቻ ነው።

ታዲያ፡ የቤተ ክህነት ሊቆቻችን፡ “የልደት በዓል፡ በየአራት ዓመቱ፡ በታኅሣሥ ፳፰ ቀን ሊውል ይገባዋል” በሚለው፡ አወዛጋቢ ውሳኔ ምክንያት፡ የተፈጠረውን፡ ይህን ትንሹንና ቀላሉን ጉዳይ፡ ቀደም ብሎ በተገለጸው መልክ፡ ለባዕዳኑ የግብፅ ኦርቶዶክሳውያን አለቆቻቸው፡ በትክክል አስረድተው መቋቋም ሲችሉ፡ ይህን ማድረግ ያቃታቸው ከኾነ፡ ይኸኛውን ትልቁን፡ የዘመን መለወጫ የኾነውን የልደቱን ቀን፡ እንደጥንቱ፡ “እንደኢትዮጵያ ልጆች ሥርዓት፡ በመስከረም ፩ ቀን መጹናት አለበት!” ብለው፡ እንዴት ሊያስረዱና ሊያስተካክሉ ይችላሉ? አዎን! በእርግጥ ሳይችሉ ቀርተዋል።

እንግዲህ፡ እግዚአብሔር የሠራውን፥ ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያትም፡ በቃል ኪዳን ታማኝነታቸው፡ ጠብቀው ያኖሩትን ሥርዓት ለማናጋት መሞከር፡ ውጤቱ፡ ይህን የመሰለውን፡ ምስቅልቅልና ዝብርቅርቅ፥ ውስብስብና አሳዛኝም ኹኔታን ማስከተል ነው፤ ስለዚህ ነው፡ ይህ ችግር የተፈጠረው። ይህንም ችግር የፈጠሩት፡ የወዳጅ ጠላቶቻችን፡ ግብፃውያን መኾናቸው፡ ስለባሕረ ሓሳቡ፡ በዋቢነት የሚጠቀሰው ድሜጥሮስ፡ ራሱ ያስረዳል። ይኹን እንጂ፡ እርሱም ቢኾን፡ በተለይ፡ የእግዚአብሔር ወልድ፡ ኢየሱስ መሲሕን፡ የልደት ቀን በሚመለከት፡ በተፈጸመው ስሕተት፡ ራሱን፡ ከተጠያቂነት፡ ነጻ ማድረጉን፡ ጥቂት ቆይተን እንገነዘባለን።

ዐውደ ዓመት በኾነው፡ በመስከረም ፩ ቀን፡ የእግዚአብሔር ሥነ ፍጥረት፡ ተዘርዝሮና ተጠቃልሎ የሚነገርበት፥ ከራብዒትና ከኬክሮስ ተነሥቶ፡ እስከዓመትና ዘመናት የሚደርሰው የጊዜ አቆጣጠር፡ በሒሳብ ተሰልቶ የሚወጣበት፡ ባሕረ ሓሳብ የሚባለው ሥነ ዕውቀት በይፋ ይቀርባል። በዚህ ዕለት፡ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ በሚደረግ፡ የካህናትና የምእመናን ጉባኤ ላይ፡ በየዓመቱ፡ ምድር ከምታበቅለው፡ የአትክልት፥ የአዝርእትና የዕፀዋት ዓይነት መካከል፡ ከፈጣሪ ለተገኘው በረከትና ለእርሱ ለሚቀርበው ምስጋና፡ ምልክት ይኾን ዘንድ፡ ስንዴና የወይን ፍሬ (ዘቢብ)፡ ጧፍና ዕጣን፥ በመሶበ ወርቅ ኾኖ፥ የዕንቍጣጣሽ አበባ ጉንጉን ጭምር ተዘጋጅቶ በሚታይበት፡ የቤተ ክህነት ሊቃውንት፡ የዚያን አዲስ ዓመት፡ የበዓላትና የአጽዋማት ውሳኔ፡ በዚሁ ባሕረ ሓሳብ አማካይነት፡ በዐዋጅ ያሰሙበታል።

**ለዚህ ባሕረ ሓሳብ ቅመራ፡ መሠረት እና መነሻ ኾኖ፡ የዘመኑ፡ የሰዓትና የዕለት፥ የመዓልትና የሌሊት፥ የወርና የዓመት አቆጣጠር፥ እንዲሁም፡ የአጽዋማትና የበዓላት ቀኖች አመዳደብ የሚወሰንበት፡ የመጀመሪያው መግቢያ፡ <u>“መስከረም ፩ ቀን”</u> ነው።**

የየአንዳንዱ ቀን: የመዓልትና የሌሊት ልክ ታውቆ የሚወጣበት: "አበቅቴ" የሚባለው መሥፈሪያ÷ አጽዋማትና በዓላት የሚውሉባቸውንም ዕለታት የሚወስነው: "መጥቅዕ" የሚባለው መቀመሪያ: ኹለቱም መሥፈሪያዎች: በየመልካቸው ተሰልተው የሚወጡት: ይህንኑ: "መስከረም ፩ ቀንን" መደብ አድርገው ነው:: ከዚህ በኋላ ነው: የቀኑና የሌሊቱ ቁጥር÷ እንዲሁም: የዓመቱ የጾም መግቢያዎችና ማብቂያዎች፣ የበዓላትም ዕለታት የሚታወቁት::

በዚህ ዐዋጅ ላይ: ከሰባቱ አጽዋማት መካከል: የገና ጾም የሚባለው: ጾመ ነቢያት እና ከእርሱ ጋር የተያያዘው: "ጾመ ገሃድ" የሚባለው: የጥምቀት ዋዜማ ጾም÷ እንዲሁም: ጾመ ፍልሰታ÷ ከዓበይት በዓላት መካከል ደግሞ፣ የእግዝእተብሔር እም: ድንግል ማርያምን የሚመለከቱት ብቻ ሳይኾኑ፣ የእግዚአብሔር ወልድ: ኢየሱስ መሲሕ: የፅንሰቱና የልደቱ÷ የጥምቀቱም በዓላት ዕለታት እንኳ ሳይቀሩ: እንዳይጠቀሱ ተደርገዋል።

## የኢየሱስ መሲሕ ልደት: ከነአጽዋማቱና በዓላቱ: ከቀመሩ ዐዋጅ ተለይቶ ስለመኖሩ::

በባሕረ ሓሳቡ ተቀምረው ወጥተው የሚታወጁት አጽዋማት: በ"በዓለ ኢትዮጵያ" የተተካው: የቀድሞው ጾመ ኢትዮጵያ (ጾመ ነነዌ)÷ ዓቢይ ጾም÷ ጾመ ሓዋርያት (የሰኔ ጾም)÷ ጾመ ድኅነት (ረቡዕ እና ዓርብ) ብቻ ሲኾኑ: የሰላማችን የኢየሱስ መሲሕ በዓላት ደግሞ: ደብረ ዘይት÷ ሆሣዕና÷ ስቅለት÷ ትንሣኤ እና ዕርገት ናቸው። ከእነዚህም ጋር: ርክበ ካህናት እና በዓለ መንፈስ ቅዱስ ይገኛሉ።

ዳሩ ግን: የሰላማችን የኢየሱስ መሲሕ: የትስብእቱ (የፅንሰቱ) እና የልደቱ÷ የጥምቀቱም በዓላት ቀኖች÷ ከእነርሱም ጋር የተያያዘው: የነቢያት ጾምና ጾመ ገሃድ: በዚህ በባሕረ ሓሳቡ ቀመራ ውስጥ ሊገቡ አልቻሉም። "ያልቻሉት: ለምንድር ነው?" ለዚህ ጥያቄ: መልሱ: አጭር ነው፤ ይኸውም: በቅድሚያ: "የሰላማችን የኢየሱስ መሲሕ: የልደቱ ቀን: ከመስከረም ፩ ቀን ተነሥቶ: ወደሌላ ዕለት ሊዛወር የማይቻል በመኾኑ ነው፤ ቀጥሎም: ከዚህ የተነሣ: እነዚህ: ጥቂት አጽዋማትና በዓላት: በባሕረ ሓሳቡ ውስጥ እንደተያዙት: እንደሌሎቹ አጽዋማትና በዓላት: መግቢያቸውና ማብቂያቸው÷ በዓላቱም: የሚውሉባቸው ቀናት: ወደላይ የማይወጡና ወደታች የማይወርዱ: ማለትም: ለምንጊዜውም: ሳይነዋወጡ: በቋሚነት ተወስነው የተመደቡ በመኾናቸው ነው!" የሚል ይኾናል::

ወይስ: ይህን የመሰለው ቀውስ የተፈጠረው: ይኸው: የሰላማችን የኢየሱስ መሲሕ: የልደቱ ቀን: ከእውነተኛው: ከመስከረም ፩ ቀን ተነሥቶ: አላገባብ: ወደታኅሣሥ ፳፱ ቀን በመቀየሩ ይኾን? ለዚህ ጥያቄ: መልስ ለመስጠት: በኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት ባሕረ ሓሳብ ውስጥ: ስማቸው የሚጠቀሰውን: ግብፃውያኑን ድሜጥሮስንና አቡሻኽርን: እንደተለመደው: እንደዋቢ አድርገን ልናቀርባቸው ያዳግተናል::

ምክንያቱም: የሰላማችን የኢየሱስ መሲሕ: የፅንሰቱንና የልደቱን: የበዓላት ቀኖች÷ ከእነርሱ ጋር የተያያዙትንም የአጽዋማት ቀኖች: ማለትም: ጾመ ነቢያትንና ጾመ ገሃድን÷ እንዲሁም: ጾመ ፍልሰታን ጨምረው: ከቀመራቸው ውጪ ስላደረጓቸው ነው:: እነርሱም ቢኾኑ: ከዚህ ቀደም ብሎ እንደተጠቆመው: እየራሳቸውን: ከስሕተቱ ነጻ ያደረጉ ይመስላሉ::

ታዲያ፥ ይኼ ኹሉ የስሕተት ድርጊት፡ ምንን ያስረዳል? ወደምንስ ያመለክታል? ለራሱ፡ ለኢትዮጵያዊው ባሕረ ሓሳብና ለአቆጣጠሩ፡ እንደመስከረሙ ወር ኹሉ፡ መሠረቱ እና መነሻው እርሱ፡ የሰላማችን የኢየሱስ መሲሕ፡ የልደቱ ቀን በመኾኑ አይደለምን? መሠረት ከተነዋወጸ ደግሞ፡ በእርሱ ላይ የቆመው ኹሉ ይፈራርሳል።

ስለዚህ፡ መሠረቱ፡ የግብፅ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያንን ጨምሮ፡ በባዕዳኑ ዘንድ ሲፋለስ፥ "በኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት ዘንድ፡ እስከዛሬ አልተነዋወጸም!" ማለት ነው። አዎን! እርሱ፡ ራሱ፡ መሠረቱ፥ ባለቤቱ፡ ኢየሱስ መሲሕ፡ ዓለሙን በፈጠረባትና በተወለደባት ቀን፡ ራሱ ተመልሶ መጥቶ፡ ዓለሙን እስከሚያሳልፍባት ዕለት ድረስ፡ መስከረም ፩ ቀንን፡ የሰላማችን የኢየሱስ መሲሕን የልደት በዓል የሚያደርገው፡ ይህ፡ የጊዜ አቆጣጠር ሥርዓት፡ በኢትዮጵያ ልጆች ዘንድ ተጠብቆ፡ ወደፊትም፡ ሳይነዋወጽ ጸንቶ ይቆያል።

የሰላማችን የኢየሱስ መሲሕ፡ የልደቱ ዕለት፡ በመስከረም ፩ ቀን መኾኑን ከሚያረጋግጡት ድርጊቶች መካከል፡ እናቱ፡ ቅድስት ድንግል ማርያም፡ እርሱን፡ ሕፃን ልጇን፡ ኢየሱስ መሲሕን፡ ከሄሮድስ ሠይፍ ለማዳን፡ በሊቀ መላእክቱ፡ በቅዱስ ገብርኤል ቃል መሠረት፡ ዐቅፋና አዝላ፡ ከጃንደረባዋ፡ ከዮሴፍና ከሰሎሜ ጋር፡ <u>ወደምድረ ግብፅ የተሰደደችበት ጊዜ፡</u> እንደኦሪቱ ሥርዓት፡ በተወለደ በአርባኛው ቀን፡ አስፈላጊውን ቊርባን ይዛ፡ በእግዚአብሔር ፊት ልታቀርበው፡ ወደቤተ መቅደስ እንዲገባ ካደረገችበት፡ ከጥቅምት ፲ ቀን በኋላ፡ እስከኅዳር ፮ ቀን፡ ባለው ወራት ውስጥ መኾኑ፡ ሌላው ተጨባጭ እውነታ ኾኖ ይገኛል። በዚህ መሠረትኮ ነው፡ እግዝእተብሔራችን ድንግል ማርያም፡ ሕፃን ልጇንና ተከታዮቿን ይዛ፡ ከኢየሩሳሌም ተነሥታ፡ የኢትዮጵያውያን ርስት እኾነችው፡ ቊስቋም ገዳም፡ በኅዳር ፮ ቀን፡ በደኅና የደረሰችው። ይኸው፡ ዛሬ፡ እኛ የኢትዮጵያ ልጆችም፡ በወርኃ ጽጌ የሚውለውን፡ የስደትን ጾም ፈጽመን፡ የቊስቋምን በዓል፡ በዚሁ፡ በኅዳር ፮ ቀን የምናከብረው።

እንግዴህ፡ እውነታው፡ እንዲህ መኾኑ ከተረጋገጠ፣ የትስብእቱ (የፅንሰቱና የብሥራቱ) ወርና ዕለት፡ ልደቱ ከዋለበት ከመስከረም ፩ ቀን፡ ወደኋላ፡ ፱ ወር ከ፭ ቀን ሲቆጠር፡ ፅንሰቱ፡ ታኅሣሥ ፩ ቀን መኾኑ ይረጋገጣል፤ ከዚህ የተነሣ፡ የብሥራቱ፥ የጾመ ነቢያትና የጥምቀቱ ወራትና ዕለታት፡ አኹን የሚውሉበትን ትክክለኛ ጊዜያት እንደያዙ ይቀጥላሉ።

በሌሎቹ ሥራዎቻቸው የምናደንቃቸው፡ የእኛ ሊቃውንት ግን፡ የዛሬዎቹ ጭምር፡ ይህንኑ ስሕተት ተቀብለው፡ እንዲህ ሥር ሰድዶ ይኖር ዘንድ፡ ዝም ብለው መመልከታቸው፡ ያስገርማል፤ ከተጠያቂነት ሊያመልጡ የሚችሉም አይመስለንም።

ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት፡ ከፈጣሪያቸው ተቀብለውት፡ በመለኮታዊው ቃል ኪዳን ያጸኑትና የጠበቁት፡ በቅዱሳት መጻሕፍት የተረጋገጠውን ሃይማኖታቸውን ብቻ ሳይኾን፡ ሥርዓታቸውን ጭምር ስለኾነ፡ እኒህን፡ ሕያዋን ቅርሶቻቸውን፡ በሰውኛ ዕውቀትና ብልሃት ሊያሻሽሉ፡ ወይም ሊለውጡ ቀርቶ፡ ከቶ ሊያስቡትም አይሞክሩትም። እንደህልውናቸው ኹሉ፡ በዘመን አቆጣጠር ስልታቸውም ረገድ፡ በሌሎቹና በጥንቶቹ ግብፃውያን ላይ ሳይቀር፡ ቅድሚያ ያላቸው መኾኑ፡ አንከባክበው በኖሩት፡ የትውፊትና የቅርስ ይዞታቸው ይታወቃል። ለዚህም፡ ግዙፉ ማስረጃ፡ የጥንቶቹ ግብፃውያን፡ የዘመን አቆጣጠራቸውን ባህል፡ የመሠረቱት፡ በታላቁ የዓባይ ወንዝ ውሃ ምልዓትና ጉድለት ላይ መኾኑ ነው።

የዓባይ ወንዝ ምንጭ ባለይዞታዎች፥ ጠባቂዎችና ባለአደራዎች የኾኑት የኢትዮጵያ ልጆች፡ በአዳምና ሔዋን ከሚጀምረውና በኖኅ ሃይማኖታዊ ምግባር፡ ከድምሳሴ ተርፎ ከቀጠለው ህልውናቸው አንሥቶ፡ ኢየሱስ መሲሕ፡ ከድንግል ማርያም በመወለዱ፡ ፭ሺ፭፻ኛው ዓመት ኮነኔ እስከተፈጸመባት፥ አዲሱም ዓመተ ምሕረት እስከተተካባት ቅጽበት ድረስ፥ ከዚያም ወዲህ፡ ሰዓታቸውን፥ ቀናቸውን፥ ሳምንታቸውን፥ ወራቸውንና ዓመታቸውን ለመቁጠር፡ አንድ ብለው የሚነሡበት ምልክት፡ የዓባይ ውኃ፡ በክረምቱ ዝናብ ምክንያት፡ ከመጨረሻው ምልዓቱ ደርሶ፡ የመቀነስ ርደቱን ማሳየት የሚጀምርበትን ዕለት ነበር፡፡ ያንንም ዕለት፡ "መስከረም ፩ ቀን" ብለው ሠይመው፡ ዓመቱና ወሩ፥ ዕለቱና ሰዓቱ የሚብቱበት (የሚጀምሩበት) እንዲኾን ወስነውታል፡፡

በግብፃውያን ምድረ በዳ እየፈሰሰ፡ በሲሳይ ሰጪነቱ፡ ሕዝቡን የሚመግበው፡ ይኸው፡ በኢትዮጵያ ድልብ አፈርና የዝናብ ውኃ የሞላው፡ የዓባይ ወንዝ፡ ከመልካው አፍ አልፎ መፍሰሱን፡ መቀነስ የሚጀምርበት ጊዜ፡ ይኸው፡ መስከረም ፩ ቀን በመኾኑ፡ እነርሱም፡ ማለትም፡ ራሳቸው፡ የኢትዮጵያ ልጆች የኾኑት፡ ጥንታውያኑ ግብፃውያን፡ ከኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት ባገኙት ዕውቀት፡ የአዲስ ዓመታቸው መግቢያ፡ በዚሁ ዕለት እንዲኾን አድርገዋል፡፡

እዚህ ላይ፡ ኢትዮጵያ፡ እንደዛሬው ሳይኾን፡ በዚያን፡ በጥንቱ ጊዜ፡ ስፋትዋ፡ እስከአስዋን ደርሶ፡ የዛሬዪቱን ግብፅ የምትዋሰን፡ ድንበረተኛ ብቻ ሳትኾን፡ ራስዋን፡ ግብፅንም ጭምር ጠቅልላ ታስተዳድር እንደነበረ፡ ማስታወስ ያሻል፤ የኢትዮጵያ አካል የነበረችው ኑብያ፡ ጥንታዊ ስሟን ለውጣ፡ በቅርቡ የተፈጠረችውን፡ ሱዳንን ትቶ ማለት ነው፡፡

ስለዚህ፡ ከዚያ ወዲህ የደረሰውን፥ በዛሬዎቹ "የሃይማኖት ወገኖች" በተባሉት፡ የግብፅ ኦርቶዶክሳውያንም የተፈጸመውን እንተወውና፡ በዚህ፡ በዘመን አቆጣጠር ሥርዓት ረገድ፡ የኢትዮጵያ ልጆች፡ በግብፃውያን ላይ ቅድሚያ እንደነበራቸው፡ ቀደም ብሎ የተገለጸው ቃል ያመለክታል፡፡

ይህ፡ የኢትዮጵያ ልጆች አቋም፡ እስከዛሬ ጸንቶ የኖረውና ዛሬም የማይናወጸው፡ ምክንያቱ፡ ይኸው፡ የሰዓትና የቀን፥ የሳምንትና የወር፥ የዓመትና የዘመን አቆጣጠራቸው፡ በቅዱሳት መጻሕፍት ተመዝግቦ የሚገኘውን፡ የእግዚአብሔርና የተፈጥሮ የኾነውን ሥርዓት ሳይለቅ በመቀጠሉ ነው፡፡

እንዲህ ከኾነ፡ ታዲያ፥ የኢየሱስ መሲሕ ልደት፡ ከዚህ አቋሙ እንዲነዋወጽ ለምን ተደረገ? ለሚለው ጥያቄ፡ መልሱ፡ ያው የታወቀውና የተለመደው፡ **"ኢትዮጵያን፡ ከእነርሱ ይልቅ፡ ቀደምት የሚያደርጓትን የማስረጃ ምልክቶች ኹሉ፡ ደብዛቸውን ሳይቀር፡ ጨርሶ ለማጥፋት ነው!"** በሚል፡ አጭር ቃል ይጠቃለላል፡፡

ይህን እውነት ለማረጋገጥ፡ አንድ፡ ሊያስተሐቅሩት የማይቻለውን፡ ዛሬም ቆሞ የሚጮኸውን ምስክር ማቅረብ ይቻላል፡፡ ያም፡ በኢየሩሳሌም፡ ዐፅመ ርስት የኾነውን፡ የኢትዮጵያን ይዞታ፡ በኃይልና በሓሰት ነጥቀው ወስደው፡ ለሚሞግቱን፡ የሃይማኖት ወገኖች ለተባሉት አብያተ ክርስቲያናት፡ ቀንደኛ መሪ የኾኑት እነማን ናቸው? እኒሁ፡ የግብፅ ቤተ ክርስቲያን መነኮሳት፥ ጳጳሳትና መሪዎቻቸው አይደሉምን?

ስለዚህ፡ የግብፅ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን መሪዎችና ተጠሪዎች፡ ኢትዮጵያ፡ በኢየሩሳሌም የዓጽመ ርስት ይዞታዎቿና በዚያ በሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት ላይ፡ እስካኹን ሲፈጽሙት የኖሩትን፥ አኹንም፡ እየፈጸሙት ያለውን ክፋት፥ ጥፋትና በደል፡ በማስተዋል ለሚያየውና አትኩሮ ለሚያመዛዝነው እውነተኛ ታዛቢ፡ ኢትዮጵያንና ልጆቿን በሚመለከት፡ በየሌሎቹ ዘርፎች፡ በየመልኩ ካደረሱት በላይ፡ ይህንንም የዘመን አቆጣጠራችንን ሥርዓት ለማፋለስ፡ በተፈጸመው ስሕተት፡ ዓይነተኛውን የተፅዕኖ አስተዋጽኦ "አላደረጉም!" ሊባል ከቶ አይቻልም፡፡

## ስለስሕተቱ፣
## ስሕተቱ መኖሩንም ስለማወቅና ስላለማወቅ።

ይህ ስሕተት፡ የኢትዮጵያዊነት መሠረታዊ አቋማችንን ለማናጋት፡ ኾን ተብሎ፡ በጥናትና በዕቅድ የተፈጸመ መስሎ ስለሚታይ፡ እኛም፡ በከፍተኛ ሃይማኖታዊና ብሔራዊ ደረጃ ይዘን፥ ብርቱ ጉዳያችንም አድርገን፡ ልንከታተለው፥ በቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነት እውነትና ዕውቀትም ልናስተካክለው ይገባናል።

አዎን! ስሕተቱ፡ መቼም፡ ከሃይማኖት ጋር የተያያዘ በመኾኑ፡ በቀላል ታይቶ፡ ሊታለፍ የሚገባው አይደለም፤ የስሕተቱን መኖር ለማያውቀው ወገን፡ "እኔ፡ መቼ፡ ይህን አወቅሁ!?"፥ ለሚያውቀውም፡ "እኔ፡ መቼ እንዲህ መሰለኝ" ብሎ፡ ኋላ፡ ምክንያት እንዳያቀርብ፡ ኹሉም፡ ስለዚሁ፡ ዓቢይ ጉዳይ፡ እውነቱን እንዲያውቅ ለማድረግ፡ ኹላችንም፡ ኪዳናውያንና ኪዳናውያት የኢትዮጵያ ልጆች ኃላፊነት አለብን። እኛም፡ ይህንኑ ጉዳይ በሚመለከት፡ ያለውን ትክክለኛ መረጃ፡ ምንም እንኳ፡ ቀደም አድርገን፡ በተለያየ መንገድ ገልጠነው የነበረ ቢኾንም፡ አኹን፡ እንደገና፥ ወደፊትም፡ እንዲሁ እያብራራን ማስረዳታችን አይቋረጥም።

በዚህ መሠረት፡ እዚህ ላይ፡ ስለኢየሱስ መሲሕ የልደት በዓል ቀን፡ ለጊዜው፡ በኹለት ቁም ነገሮች ተወስነን፡ ከዚህ የሚከተለውን ሓተታ፡ በመልክ በመልኩ እናቀርብላችኋለን፡-

<u>**የመጀመሪያው ቍምነገር፤**</u> እኛ ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት፡ የዓለሙ ሰላም፡ ኢየሱስ መሲሕ፡ በእውነተኛው፡ የኢትዮጵያ ልጆች ቀን፥ ይኸውም፡ መስከረም ፩ ቀን፡ ከድንግል ማርያም ስለተወለደ፡ **"ዓመተ ፍዳ ተሸሮ፡ ዓመተ ምሕረት ተተካ!"** ብለን፡ በዕለቱ፡ ታላቅ የዐውደ ዓመት በዓል እናደርጋለን።

ለዚህ ላበቃን አምላክም፡ ከአራሲቱ ቅድስት እናቱና ከጃንደረባዋ ጻድቅ ዮሴፍ፥ ከመላእክትና ከእረኞች፥ ከሰብአ ሰገልና ከእንስሶች ጋር፡ በእውነተኛው መንፈሳዊ አምልኮ ኾነን፥ በምሥራች ዝማሬና በሓሤት ቃል፡ የደስታ ምስጋናችንን እናቀርባለን። ነገር ግን፡ ይህ ኹሉ ከኾነ በኋላ፡ ለአራት ወራት ቆይተን፡ በታኅሣሥ ፳፱ ቀን፡ እንደገና እንድናከብረው ሲደረግ ቆይቷል። ለምን? ምክንያቶች ስላሉት፡ እስኪ፡ እነዚህኑ ምክንያቶች፡ ጥቂት ጠለቅ ብለን እንመልከታቸው?!

በአኹኑ ጊዜ፡ የኢየሱስ መሲሕ የልደት በዓል፡ በመስከረም ፩ ቀን ከምናከብረው፡ ከእኛ፡ ከቅዱሱ ኪዳን የኢትዮጵያ ልጆች በቀር፡ በተቀረው፡ በመላው የክርስቲያኑ ዓለምና በቤተ ልሔም የሚከበረው፡ በታኅሣሥ ወር፥ ያውም በአንድ፡ በተወሰነ ቀን ሳይኾን፡ በዚሁ ወር መጨረሻና በጥር ወር መጀመሪያ ባሉት ቀኖች አካባቢ፡ በተለያዩ አብያተ ክርስቲያናት፡ ቢያንስ ቢያንስ፡ በአራት የተለያዩ ዕለታት ነው። በዚህም፡ የሃይማኖት ወደረኞቻችን፡ አይሁድም፥ እስላሞችም፥ አረማውያንም፥ ሃይማኖተ ቢሶችም እንደሚያፌዙብን ይነገራል፤ ይታያልም።

ምዕራባውያንና አብዛኛዎቹ ምሥራቃውያን ክርስቲያኖች፡ የልደትን በዓል የሚያከብሩት፡ በእነርሱ የዘመን አቆጣጠር፡ በDecember 25 (ዲሴምበር ፳፭)፥ (በኢትዮጵያውያን አቆጣጠር፡ በታኅሣሥ ፲፮) ሲኾን፡ የግብፅ ኦርቶዶክስ ተቀጥላ የኾኑት፡ ኢትዮጵያውያንና ጥቂቶች ምሥራቃውያን ክርስቲያኖች ደግሞ፡ ያው፡ በታኅሣሥ ፳፱ ቀን፡ በእነርሱ አቆጣጠር፡ በJanuary 7 (ጃንዋሪ ፯)፥ ሌሎቹም የቀሩት አናሳ ወገኖች፡ በእነዚህ ቀኖች መካከል ባሉ፡ የተለያዩ ኹለት ዕለታት ያከብራሉ።

በምዕራባውያን፥ ይልቁንም፡ በካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን የሥነ ከዋክብት ሊቃውንት ዘንድ፡ የኢየሱ ስ መሲሕ የልደት ቀን፡ "በትክክል አይታወቅም" የሚለው የግምት አስተሳሰብ፡ እስከዛሬም እንደጸና ይገኛል፡፡ ከዚህ የተነሣ፡ ከቀድሞ ጀምሮ፡ የልደቱ ቀን፡ "በዚህ ዕለትና ዓመት ይኹን!" እያሉ የወሰኑት፡ በሥጋ ፍልስፍናና በዘፈቀደ፥ በምናልባትና በመላምት ብቻ መኾኑ ተረጋግጧል፡፡ እኒህ፡ የምዕራባውያን ቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት፡ የዱሮውን የሮማውያንን አረማዊ ባህል አስወግደው፡ በእርሱ ሥፍራ፡ B.C. (Before the Birth of Christ) "ከክርስቶስ ልደት በፊት" እና A.D. (Anno Domini) "ዓመተ ምሕረት"፥ ወይም፡ "ከክርስቶስ ልደት በኋላ" የሚለውን የዘመናት መክፈያ ሥርዓት ለመተካትና ለመመሥረት ተገድደዋል፡፡

ይህም የኾነው፡ ትክክለኛውን የኢየሱስ መሲሕን የልደት ቀን፡ ማለትም፡ በዓመተ ኵነኔውና በዓመተ ምሕረቱ መገናኛ ላይ፡ አልቦ (zero ዜሮ) ቁጥር የሚኾነውን ጊዜ፡ በቁርጥ ለማግኘት ስላቃታቸው፡ ይህን ዕለት ፈጥረው፡ በዘፈቀደ እንደወሰኑት ታውቋል፤ ለዚህም፡ በዋቢነት፡ ስሙ የሚጠቀሰው፡ Dionysius Exiguus ዲዮኒሲዩስ ኤክሲጉዑስ የተባለው፡ ጣልያናዊ፡ የካቶሊክ መነኵሴ ነው፡፡ እርሱም ይህን አሳብ ያመነጨው፡ እንደእነርሱ አቈጣጠር፡ ከ፭፻ እስከ ፭፻፶፭ ዓመተ ምሕረት ባለው ዘመን ውስጥ ነበር፡፡

እግዚአብሔራችን ኢየሱስ መሲሕ፡ በነቢያት ትንቢት መሠረት ይወለድ ዘንድ፡ በቅድስት እናቱ ድንግል ማርያም ማሕፀን ኾኖ ፡ በጻድቁ ቅዱስ ዮሴፍ ጀንደረባነት፡ ከገሊላ ናዝሬት መኖሪያቸው፡ ወደቤተ ልሔም በረት የተጓዙት፡ የሮማው ገዢ የነበረው፡ አውግሥጦስ ቄሣር፡ በግዛቱ ውስጥ የሚኖረው ሰው ኹሉ፡ በየትውልድ ቦታው እየኼደ እንዲመዘገብ፡ ባወጀው ትእዛዝ መነሻነት መኾኑ ይታወቃል፡፡ ያ ትእዛዝ የታወጀበት ጊዜም፡ ምዕራባውያን፡ "የክርስቶስ የልደት ቀን ነው" ብለው የወሰኑትን፡ የዘመን አቈጣጠራቸውን ቀመር ተከትሎ ሲሰላ፡ "ከክርስቶስ ልደት በኋላ" በ፯ኛው ዓመተ ምሕረት ላይ የዋለ ኾኖ ተገኝቷል፡፡

ከእኒህ ኹሉ ማስረጃዎች ጋር፡ የኢየሱስ መሲሕን፡ የልደት በዓል ለማክበር ሲባል፡ የልደቱ ቀን፡ ቀደም ብለው የተጠቀሱትን ዕለታት በሚያካልለው፡ በዚህ፡ በአንድ ሰሞን፥ በተለይም፡ በእነርሱ የቀን አቆጣጠር፡ በDecember 25 (ዲሴምበር ፳፭)፡ እንዲውል የተደረገበት፡ አንድ፡ ሌላ፡ የታወቀ ዋና ምክንያት ደግሞ አለ! ይኸውም፡ በእምነታቸው፡ ገና አረማውያንና አሕዛብ የነበሩት፡ ሮማውያንና የቀሩት የአውሮጳ ሕዝቦች፡ የጣዖትና የባዕድ አምልኳቸውን ልደት፡ ወይም፡ የመመሥረቻ ቀን ምክንያት በማድረግ፡ በተመሳሳይ መልክ ይፈጽሙት ከነበረው፡ የፍና ተሣልቆ [የፈንጠዚያ] በዓላቸው ጋር፡ አዲሱ የኢየሱስ መሲሕም ልደት፡ ዐብሮ ኾኖ በዚሁ ሰሞን እንዲከበር፡ የቀድሞዎቹ ክርስቲያኖች፡ በቅን ዓላማ መፈለጋቸው ነው፡፡

"ከኢየሱስ መሲሕ ልደት ጋር ተመሳሳይነት ነበራቸው!" የተባሉት፥ በዚያው ዕለት፡ ማለትም፡ በእነርሱ የቀን አቆጣጠር፡ በDecember 25 (ዲሴምበር ፳፭)፥ ወይም በዚያው ሰሞን የሚውሉትና የሚከበሩት፡ እነዚያ፡ የአረማውያኑ በዓላት፡ ለምሳሌ ያህል ዋና ዋናዎቹ፡ እኒህ ነበሩ፡-

፩ኛ፡ ሮማውያን፡ ስሙን በመታሰቢያነት፡ January (ጃንዋሪ) ብለው፡ ለዓመቱ የመጀመሪያ ወር የሰጡለት፡ Janus (ጃኑስ) የተባለው ጣዖታቸው በዓል፤

፪ኛ: Natalis Solis Invicti (ናታሊስ ሶሊስ ኢንቪክቲ): ማለትም: “ያልተደፈረችው ፀሓይ የልደት ቀን” የሚለው የልደት በዓል፤

፫ኛ: “ሚዕራ” የምትባለው: የኢራናውያን (የፋርስ) የምስጢር ጣዖት: የልደት በዓል ቀን፤

፬ኛ: የአረማውያኑ በዓል: ጥንቱኑ: ኾን ተብሎ: እንዲውል የተደረገው: በበረዶው ወራት መካከል ኾኖ: ያም ወቅት: አረማውያኑ: ለክረምትና ለፀሓይ: በጥድ ዛፍ የሚያቀርቡትን የባዕድ አምልኮ ሥርዓታቸውን የሚፈጽሙበት፥ ሓሤት የሚያደርጉበትና የመልካም ምኞት ስጦታን የሚለዋወጡበት [የፍና ተሣልቆ] ታላቅ በዓል::

እንግዴህ: እዚህ ላይ: በዚያን ዘመን: አረማውያንና አሕዛብ የነበሩት ሮማውያንና አውሮጳውያን: የክርስትናን እምነት እንዲቀበሉ በተደረገበት ጊዜ: ይህንኑ አዲስ የክርስትና ሃይማኖታቸውን በበለጠ እንዲያጸኑት ለማበረታታት ሲባል: በጊዜው የነበሩት የቤተ ክርስቲያን ልኡካንና መሪዎች: የተጠቀሙበትን ዘዴ: በቀላሉ መመልከት ይቻላል፤ ቅዱስ ጳውሎስ: ጣዖት አምላኪዎች ለነበሩት ለግሪክ ሰዎች: በአቴና ከተማ: በአርዮስፋጎስ አደባባይ ተገኝቶ በሰበከላቸው አቀራረብ ዓይነት ማለት ነው::

ይኸውም: “ያ: በዛፍና በልዩ ልዩ ምልክቶች ታመልኩት የነበረው አምላክ: እነሆ: ሰው ኾኖ ተወልዶ: ከሰይጣን ገዢነት፥ ከኃጢአት ቀንበርና ከሞት ዕዳ አዳነን! የእርሱ ልጆች የምንኾንበትንም ጸጋ ሰጥቶን: የዘለዓለም ሕይወት ወራሾች አደረገን!” በማለት: በዚያው: የአማልክቶቻቸውን የልደት ወይም የመታሰቢያ በዓላት በሚያከብሩበት ቀንና በዚያው: በጥንቱ: የአምልኮ ምልክታቸው፥ ባህላቸውና ሥርዓታቸው ተቀይሮ እንዲቀጥል ማድረጋቸው ነው:: ይህ ኹሉ: በራሳቸው: በምዕራባውያኑ የዝክረ ነገር መጽሓፍ ውስጥ ተመዝግቦ ይገኛል:: (የሓዋ. ፲፥ ፳፪-፴፬። Encyclopaedia Britannica, CD 2000, Christmas.)

በምዕራባውያን ዘንድ: ዛሬ: የኢየሱስ መሲሕ: የልደቱ ቀን: ቀደም ብሎ በተጠቀሰው ዕለት እንዲውል የተወሰነው፥ ምልክቱና ሥርዓቱም: በተጌጠ የጥድ ዛፍ እንዲኾን የተደረገው: በዚህ ምክንያት መኾኑን: በተለይ: እየራሳችንን: "ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት ነን!" የምንል ኹሉ: ልናጤነው ይገባናል:: የገናን በዓል: በጥድ ዛፍ የማክበሩ ባህል: ለእኛ: ምናችንም አለመኾኑን: በብርቱ ልንገነዘበው ያስፈልጋል:: ይህንም ነገር: በቦታው: ርእስ አድርገን እንወያይበታለን::

በእነርሱ: በምዕራባውያኑ በኩል: ይህን ወጋቸውን እንዲጠብቁ የተገደዱበት: ቀደም ብለን የገለጽንላችሁ ምክንያት: ከእኛ ጋር የሚነጻጸርበት ኹኔታ አለ፤ ይኸውም: ከፍጥረት መጀመሪያ አንሥቶ: በኪዳነ ልቦናው እምነትና ሥርዓት: ጸንቶ የኖረው: የኢትዮጵያ ሕዝብ: ቀደም ብሎ: ወደኪዳነ ኦሪቱ፥ በመጨረሻም: ወደኪዳነ መንፈስ ቅዱሱ እምነትና ሥርዓት በተሸጋገረበት ጊዜ: በታቦተ ጽዮን አማካይነት ሲካኼድ የቆየውን አምልኮተ እግዚአብሔር: በሠመረ ሽግግር እንዲቀጥል ያስቻለ ስልት: በቤተ ክህነቱ ዘርፍ ባሉት ኢትዮጵያውያን አዋቆች ተተልሞ: በሥራ ላይ መዋሉ ነው፤ ያም ስልት: የቀድሞዋን የሚተካ: በአዲሱ ኪዳን መሠረት: ከዕብነ-በረድ እና ከእንጨት የተቀረጸ ጽላትና ታቦት ተዘጋጅቶ: በየቤተ መቅደሱ እንዲገኝ ማድረጉ ነበረ::

በዚህ ሓተታ: የመጀመሪያውን ቁም ነገር እናጠናቅቃለን።

ኹለተኛው ቁም ነገር፡ ከዚህ ይቀጥላል፡- ይኸውም፡ የፈጣሪያችን የኢየሱስ መሲሕ፡ የልደት ቀን፡ በምዕራባውያኑ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ዘንድ ሳይቀር፡ በትክክል ባለመታወቁ፡ እኚሁ መሪዎች፡ ለዚህ ችግር "መፍትሔ ይኾናል!" ብለው የፈጸሙትን ዘዴ፡ በመመርመር ነው።

አዎን! መፍትሔው፡ ይህንኑ፡ የኢየሱስ መሲሕን የልደት በዓል፡ ወደክርስትና ሃይማኖት የተመለሱት፡ አዲሶቹ ምእመናንና ምእመናት፡ ቀድሞ፡ በአረማዊነታቸው ጊዜ፡ የበዓላቸው ዕለት አድርገው ያከብሩት በነበረው፡ በDecember 25 (ዲሴምበር 'ታኅሣሥ' ፳፭) ቀን እንዲውል መወሰን ብቻ ኾኖ ተገኘ:: ይህንም ያደረጉት፡ በአዲሶቹ ክርስቲያኖች ዘንድ፡ የቀድሞው የበዓላቸው ቀን ሳይፋለስ መቀጠሉ፡ ለክርስትናው እምነት መመሥረት፥ መጽናትና መስፋፋት፡ ጠቃሚና መልካም ዘዴ ሊኾን እንደሚችል በማመናቸው መኾኑን፡ ቀደም ብለን ካቀረብነው ሐተታ፡ ተረድታችሁታል::

የዚህ ሐተታ ፍሬ ነገር ሲጠቃለል፡ "ኢየሱስ መሲሕ፡ የተወለደበት ነው" ተብሎ የሚከበረውን ቀን፡ አጠራጣሪ የሚያደርግ፡ የስሕተት ጭብጥ መኖሩን የሚያመለክት ከመኾኑ ጋር፡ ወደሌላ የማስረጃ ፍለጋና ምርምር እንድናመራ የሚጋብዝ፡ አስተማማኝ ፍንጭንም ያበረክትልናል:: ምርምራችንም፡ ኢየሱስ መሲሕ፡ "ተወልዶበታል!" የሚባለው፡ የDecember (ዲሴምበር 'ታኅሣሥ') ወር፡ ቤተ ልሔም በምትገኝበት፡ በሰሜኑ ክፍለ ዓለም ክልል፡ ክረምትና በረዶ የሚጸናበት ጊዜ ስለኾነ፡ "ያ፡ የክረምትና የበረዶ ወራት፡ በእርግጥ፡ ኢየሱስ መሲሕ የተወለደበትን ቀን የያዘ ነበር ወይ?" የሚለውን ጥያቄ ለመመለስ መቻል ይኾናል:: ይህን ችሎታ የሚያስገኝልን ደግሞ፡ ቀጥሎ ያለው የምሥራቹ (የወንጌሉ) ቃል ነው:-

**"ወኮነ በውእቱ መዋዕል፡ ወጽአ ትእዛዝ፡ እምአውግስጦስ ቄሣር፡ ከመ ይጸሐፍ ኵሉ ዓለም። ወውእቱ ጻሕፍ፡ ቀዳሚ፣ አመ ቄሬኔዎስ መስፍን ለሶርያ። ወሖረ ኵሉ ሰብእ፡ ይጸሐፍ በበሀገሩ። ወዐርገ ዮሴፍኒ እምገሊላ፡ እምሀገረ ናዝሬት፣ መንገለ ይሁዳ፡ ኀበ ሀገረ-ዳዊት፣ እንተ ስማ 'ቤተ-ልሔም'፤ እስመ እምቤተ-ዳዊት፣ ወእምአዝማደ ቤቱ ውእቱ። ወሖረ ይጸሐፍ ምስለ ማርያም፡ እንተ ፈሀሩ ሎቱ፣ እንዘ ፅንስት ይእቲ። ወእምዝ፡ እንዘ ሀለዉ ህየ፡ በጽሐ ዕለተ-ወሊዶታ። ወወለደት ወልደ ዘበኵራ፤ ወአሰረቶ መንኮብያቲሁ፤ ወአስከበቶ ውስተ ጎል፤ ወጠብለለቶ በአፅርቅት፤ እስመ አልቦሙ መካን፡ ውስተ ማኅደሮሙ። ወሀለዉ ኖሎት ውስተ ውእቱ ብሔር፤ ይተግሁ፤ ወይሔልዉ፤ ወየዐቅቡ መራዕይሆሙ፡ ሌሊተ፣ በበዕብሬቶሙ።**

"በዚያም ወራት፡ ዓለሙ ኹሉ እንዲጻፍ፡ ከአውግስጦስ ቄሣር ትእዛዝ ወጣ:: ቄሬኔዎስ፡ በሶርያ አገር፡ ገዥ በነበረ ጊዜ፡ ይህ፡ የመጀመሪያ ጽሕፈት ኾነ:: ኹሉም፡ እያንዳንዱ፡ ይጻፍ ዘንድ፡ ወደከተማው ሄደ:: ዮሴፍም ደግሞ፡ ከዳዊት ቤትና ወገን ስለነበረ፡ ከገሊላ፡ ከናዝሬት ከተማ ተነሥቶ፡ ቤተ ልሔም ወደምትባል፡ ወደዳዊት ከተማ፡ ወደይሁዳ፡ ፀንሳ ከነበረችው፡ ከእጮኛው ማርያም ጋር ይጻፍ ዘንድ ወጣ:: በዚያም ሣሉ የመውለጃዋ ወራት ደረሰ፤ የበኵር ልጇንም ወለደች፤ ዐውራ ጣቱንም አሰረችው፤ በጨርቅም ጠቀለለችው፤ በእንግዶች ማደሪያም፡ ሥፍራ ስላልነበራቸው፡ በበረት አስተኛችው:: በዚያም ምድር፡ መንጋቸውን፡ በየተራቸው፡ በሌሊት፡ ነቅተው እና ተግተው ሲጠብቁ በሜዳ ያደሩ እረኞች ነበሩ::"

አውግስጦስ ቄሣር፡ ይህን ትእዛዝ ያስተላለፈው፡ "**ወአንቲኒ ቤተ-ልሔም፡ ምድረ-ኤፍራታ! ኢትቴሐቲ እምነገሥተ ይሁዳ፤ እስመ እምኔኪ ይወጽእ ንጉሥ፤ ዘይርዕዮሙ ለሕዝብየ እስራኤል።** አንቺ ቤተ ልሔም! የኤፍራታ ምድር! ከይሁዳ ንጉሦች ከቶ አታንሺም! ሕዝቤን፡ እስራኤልን የሚጠብቅ ንጉሥ፡ ከአንቺ ይወጣልና!" የሚለው፡ የእግዚአብሔር የትንቢት ቃል እንዲፈጸም ለማድረግ መኾኑ የታመነ ነው:: (ሉቃ. ፪፥ ፩-፰፤ ሚክ. ፭፥ ፪። ማቴ. ፪፥ ፭-፮::)

ይኹን እንጂ፡ "አውግስጦስ ቄሣር፡ በዘመኑ እጅግ ሰፊ በነበረው ግዛቱ ውስጥ ይኖር የነበረው፡ ያ ኹሉ እልፍ አእላፋት ሕዝቡ፡ ዝናሙና በረዶው፡ በዚያ ክፍለ ዓለም በሚከፋበትና በሚበረታበት፡ በክረምቱ ወራት፡ ከያለበት እንዲንቀሳቀስ ያደረገውን፡ ያን የመሰለውን ትእዛዝ ያስተላልፋል!" ተብሎ እንዴት ሊታሰብ ይችላል? አይቻልም:: ወራቱ፡ በእርግጥ ክረምት ከኾነ፡ "ቄሣራዊዉን ትእዛዝ በመፈጸምና በማስፈጸም ረገድ፡ በእያንዳንዱ ዜጋና ቤተሰብ፥ በመንግሥቱ ባለሥልጣኖችና ሠራተኞችም ላይ ሊደርስ ይችላል!" ተብሎ የሚገመተውን እንግልትና ጫና፡ እንኳንስ፡ የክረምቱ አሠቃቂ ጠንቅ ተጨምሮበት ይቅርና፡ በዚያው በበጋው ወራት ፀሓያማ ኹኔታም እንኳ እያሉ፡ በድንግል ማርያም እና በጻንደረባዋ ዮሴፍ ላይ በደረሰው፡ የጉዞና የማረፊያ ቦታ ማጣት ችግር፡ በቀላሉ መረዳት ይቻላል::

ታዲያ! ልትወልድ እንደተቃረበችው፡ እንደእግዝእተብሔራችን ድንግል ማርያም እና እንደጻንደረባዋ ዮሴፍ፤ እንደረዳቲቱ ሰሎሜ ጭምር፤ ከመኖሪያ ቀበሌያቸው ተነሥተው፥ እንደዛሬው እንኳ፡ ተሽከርካሪና ምቹ መጓጓዣ ባልነበረበት ኹኔታ፡ ጓዛቸውን ጭነው ወይም ተሸክመው፡ ያን ያህል፥ ከዚያም ሊርቅ የሚችል የእግር መንገድ ጉዞን ለሚያደርጉ ዜጎቹ፡ ያ የቄሣር መንግሥት አያስብምን? በእርግጥ፡ ያስባል እንጂ። ለዜጎቹ የማያዝን እንኳ ቢኾን፡ ትእዛዙን ለማስፈጸም፡ መንግሥቱ ራሱ፡ የሚያደርገው ዝግጅትና ድርጅት እንዴት ሊከናወንለት ይችላል? አይችልም:: ዛሬ፡ የመገናኛና የማጓጓዣ ዘዴዎች፡ ተሟልተው እና ተከናውነው በሚገኙበት ጊዜ እንኳ፡ በማንኛውም አገር፡ የሕዝብ የምርጫ ሥርዓት የሚካኼደው፡ የወራቱ አየር ጠባይ፡ ተስማሚ መኾኑ በተረጋገጠበት፡ የበጋ ወራት እንደኾነ ይታወቃል::

የአይሁድ ሎሌዎች እና የጲላጦስ ወታደሮች፡ እግዚአብሔራችን ኢየሱስ መሲሕን ይዘውና አስረው፡ ወደሊቀ ካህናቱ ግቢ የወሰዱበት የምሽቱ ጊዜ፡ "**ወህለዉ ይቀውሙ፡ አግብርቲሆሙ፥ ወወዓልያኒሆሙ፤ ወይበቍጹ እፍሓመ፤ ወይስሕኑ፤ እስመ ብዙኅ ቍሩ፡ ለይእቲ ሌሊት። ወይቀውም፡ ጴጥሮስኒ፤ ወይስሕን ምስሌሆሙ።** ጽኑ ብርድ ነበርና፡ አገልጋዮቻቸው እና ሎሌዎቻቸው፡ የፍም እሳት አንድደው፡ ቆመው ይሞቁ ነበር፤ ጴጥሮስም ደግሞ፡ ከእነርሱ ጋር ቆሞ፡ ይሞቅ ነበር።" የሚለውን የመሰለ፡የባለምሥራቹ (የወንጌላዊው) አገላለጽ፡ በዚህ፡ በኢየሱስ መሲሕ፡ የልደት ጊዜ አልተወሳም:: ኢየሱስ መሲሕ የተወለደበት ወራት፡ እንኳንስ የክረምት ዝናምና በረዶ ይቅርና፡ ብርድ እንኳ የነበረ መኾኑን፡ የሚያመለክት፥ የሚያስረዳም፡ አንዳችም ምልክት የለም:: ቢኖርም እንኳ፡ ወራቱ፡ ምንም ዓይነት፡ የክረምት ምልክት የሌለው፡ እንዲያውም፡ ፍጹም በጋ መኾኑን የሚያረጋግጥ ኾኖ ይገኛል::

ይኸውም፡ ባለምሥራቹ (ወንጌላዊው) ሉቃስ፡ ስለኢየሱስ መሲሕ ልደት ኹኔታ፥ በጊዜው ስለነበረው፡ የአየሩ ጠባይ እና ስለተፈጸመው ተአምራዊ ድርጊት፡ በጻፈው ዜና ውስጥ ያለው እና ቀደም ብሎ የተጠቀሰው ቃል ነው።

አዎን! በተለይ: “**ወሀለዉ ኖሎት ውስተ ውእቱ ብሔር፤ ይትግሁ፤ ወይሔልዉ፤ ወየዐቅቡ መራዕይሆሙ፡ ሌሊተ፣ በበዕብሬቶሙ።** በዚያም ምድር: መንጋቸውን፡ በየተራቸው፡ በሌሊት: ነቅተው እና ተግተው ሲጠብቁ በሜዳ ያደሩ እረኞች ነበሩ::” የሚለው ቃል እና ምንም ዓይነት የአየር ጠባይ ችግር ያልታየበት፣ ያልነበረበትም፡ ያ፡ ረዥሙም፣ አጫጭሩም፡ የሰብአ ሰገል የውደት (የዝውውር) ጉዞ: ለዚህ ምስክርነት ይበቃሉ:: ይህም: ኢየሱስ መሲሕ የተወለደበት ወራቱ: የመስከረም በጋ እንጂ: ዝናም እና በረዶ የሚወርድበት: ክረምት: ማለትም: የታኅሣሥ ወር ያለመኾኑን ያረጋግጣል:: ለዚህ ጉዳይ: ከባለምሥራቹ (ከወንጌላዊው) ያለፈ: ሌላ ምስክር አያሻም:: (ዮሐ. ፲፰÷ ፲፰፤ ሉቃ. ፪÷ ፰::)

“ቊር ወይም ብርድ ነበረ” ተብሎ የሚሰጥ የትርጓሜና ትችት ቢኖር እንኳ: ያ ቊር ወይም ብርድ: በአገራችን: በጥቅምትና በጥር ማታና ሌሊት የሚወርደውን የሚመስል መኾን ይኖርበታል:: የሌሊት ቀዝቃዛ ነፋስ: ወዲያና ወዲህ በሚነፍስበት÷ ዝግ ግድግዳ በሌለው እና በፍርግርግ በተከለለ በረት ውስጥ: "ብርድ የለም!" እንዴት ሊባል ይቻላል? ከዚህ የተነሣም: ጌታ በተወለደበት በረት ውስጥ የነበሩ እንስሳት ሳይቀሩ: “**በእስትንፋሳቸው አሟሟቁት**” ተብሎ በተጨማሪ ሓተታ ቢተረጐም: አያስደንቅም::

እንግዴህ: በዚህ ኹሉ ማስረጃ: ያ: እግዚአብሔር ወልድ፡ ኢየሱስ መሲሕ የተወለደበት ወራት: ቤተ ልሔምን÷ መካከለኛውን ምሥራቅና መላውን አውሮጳን ባቀፈው በሰሜኑ ክፍለ ዓለም: የፀሓይ ብርሃንና ሙቀት የሚሰፍንበት: በእኛ: የክረምት ወራት÷ በእነርሱ ደግሞ: የሓጋይ፥ ወይም: የበጋ ወራት መኾኑ: አሌ ሊባል ከቶ አይቻልም::

የመስከረም ወር: በዚያ ክፍለ ዓለም: ተስማሚ የአየር ጠባይ የሚታይበት: የበጋው ወራት ማብቂያ ስለኾነ: በትክክል ሊታወቅ ያልተቻለው÷ ነገር ግን: በሰዎች: የምናልባትና የመላምት ውሳኔ: በDecember 25 (ዲሴምበር 'ታኅሣሥ' ፳፭) ቀን እንዲውል የተደረገው: የሰላማችን የኢየሱስ መሲሕ፡ የልደቱ ቀን: እውነተኛውና ትክክለኛው: በኢትዮጵያኑ የጊዜ አቀጣጠር: “**መስከረም ፩ ቀን ነው!**” ብለን መደምደም ይኖርብናል::

በዚህ ሓተታ: ኹለተኛው ቁም ነገር ይጠቃለላል::

## የኢትዮጵያ ልጆች: የዘመን አቆጣጠር: ከሌሎቹ የሚለይበት ባሕርይ::

ቀደም ብሎ እንደተገለጸው: በይበልጥ: በአረማዊነት ባህል÷ በመጠኑም: በከዋክብት ሥነ-ዕውቀት ላይ የተመሠረተው የምዕራባውያን የዘመን አቆጣጠር: ከኢትዮጵያ ልጆች የዘመን አቆጣጠር የሚለይበት ባሕርይና አኹን ያለበት ቀውስ የደረሰበት፡ ለምን እንደኾነ: ሊብራራ ስለሚገባው: የዚሁ ቀውስ፡ ዝርዝር ዘገባ፡ ከዚህ በሚከተለው ሓተታ ቀርቧል:-

የኢትዮጵያ ልጆች: በቅዱሱ ኪዳን ሃይማኖታቸው ላይ የመሠረቱትን: ይህን የጊዜ አቆጣጠር ሥርዓት: ምዕራባውያን÷ ኦርቶዶክሳውያን የተባሉት አብያተ ክርስቲያናት ጭምር: በአረማዊው: ዩልየስ ቄሣርና ጎርጎርዮስ (ግሬጎሪ) ፲፫ኛ በተባለው: በካቶሊካዊው ርእሰ ቤተ ክርስቲያን ስሞች እየሰየሙ÷ በየጊዜው እየለዋወጡና በመጨረሻ: ፰ ዓመታት ከ፲ ቀናትን ያህል አክለውበት መቆየታቸው ይታወቃል::

በዚህ የአቆጣጠራቸው ስልት፡ የእግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ መሲሕን የልደት ቀን፡ ከ፬ እስከ፯ ዓመታት ለሚደርስ ዘመን፡ ከፍ አድርገው እንዲጨምሩ በመገደዳቸው፡ ይህን፡ ሰው ሠራሽ ቀውስ አስተካክለው ለማስታረቅ አቅቷቸው፡ እነሆ፡ እስካኹን ሲባዝኑ ይገኛሉ፡፡ በዚህ፡ በእነርሱው አቆጣጠር፡ ኢየሱስ መሲሕ የተወለደው፡ "በ፬÷ በ፮ ወይም በ፯ ዓመተ ምሕረት ላይ ሳይኾን አይቀርም" ከማለት በስተቀር፡ እርግጠኛውን ቀን፡ በቁርጥ ሊወስኑ ሳይቻላቸው ቀርቷል፡፡

ይህ ቀውስ የተፈጠረባቸው፡ የኢየሱስ መሲሕን የልደት ዓመት፡ አንድ ብለው መቁጠር ከጀመሩ በኋላ፡ ያ፡ የዓመተ ምሕረት መነሻ ዘመን፡ በአረማዊነት ዘመናቸው፡ "ጁልያን" በሚል ስምና በተለያየ ስልት ይጠቀሙበት በነበረው የአቈጣጠር ሥርዓታቸው፡ በ፬÷ በ፮ ወይም በ፯ ዓመታት ላይ ውሎ ስላገኙት ነው፡፡

ሌላው፡ ይህን ችግር የፈጠረባቸው ምክንያት፡ የምዕራባውያን የጊዜ አቈጣጠር፡ እንደኢትዮጵያው አቀማመር፡ ያው፡ በአንድ መሠረት ላይ ታንጾ፥ በአንድ፡ በተስተካከለ ሥርዓት ተቀምሮ የሚመራ ባለመኾኑ ነው፡፡ ይህንም፡ ከዚህ የሚከተለውን ማነጻጸሪያ ሓተታ በመመልከት፡ መረዳት ይቻላል፡፡

የኢትዮጵያ ልጆች፡ "የእግዚአብሔር ገነት" ተተክላባት፡ አዳምና ሔዋን የተፈጠሩባት አገራቸው የምትገኘው፡ በምድር ማእከል፥ ወይም መቀነት ክልል ውስጥ ስለኾነ፡ የጊዜ አቈጣጠራቸው ሥርዓት፡ መዓልቷና ሌሊቷ፡ ዓመቱን ሙሉ፡ በ፲፪÷ በ፲፪ ሰዓታት፡ እኩል በተከፈለበት የአሠፋፈር ስልት ላይ ተመሥርቶ፡ የባሕረ ሓሳቡ ቅመራ፡ ሥርዓቱን ጠብቆ፡ ያለችግር ይካኼዳል፡፡

ይኸውም፡ ወደኋላ፡ ወደረቂቃኑ ሳንኼድ፡ ከሣልሲት ተነሥተን፡ እስከዓመት ብንቈጥር እንኳ፡ ቀመሩ፡ የተስተካከለ ኾኖ እናገኘዋለን፡፡ ማለትም፡ ፷ (ስድሳ) ሣልሲታት፡ ፩ (አንድ) ካልዕት (Second)÷ ፷ (ስድሳ) ካልዕታት፡ ፩ (አንድ) ደቂቃ÷ ፷ (ስድሳ) ደቂቃት፡ ፩ (አንድ) ሰዓት÷ ፳፬ (ሃያ አራት) ሰዓታት፡ ወይም ፷ (ስድሳ) ኬክሮስ፡ ፩ (አንድ) ዕለት ይኾናሉ፡፡ ፩ዱ (አንዱ) ዕለት ደግሞ፡ ፀሓይ እንድትሠለጥንበት የተመደበው፡ ፲፪ (ዐሥራ ኹለት) ሰዓታትን የያዘው፡ የብርሃን ጊዜ፡ "መዓልት"÷ ጨረቃ እንድትሠለጥንበት የተመደበው፡ ፲፪ (ዐሥራ ኹለት) ሰዓታትን የያዘው፡ የጨለማ ጊዜ ደግሞ፡ "ሌሊት" ይባላል፡፡

የመዓልቱ የጊዜ አቆጣጠር፡ የተፈጥሮውን ሥርዓት በመከተል፡ "ከቀትር በፊት" እና "ከቀትር በኋላ" ተብሎ፡ ፀሓይ፡ ጮራዋን በምትፈነጥቅበት፡ በንጋቱ ፩ (አንድ) ሰዓት ይጀምርና፡ በምትጠልቅበት፡ በምሽቱ ፲፪ (ዐሥራ ኹለት) ሰዓት ያበቃል።

የሌሊቱም ጊዜ፡ እንደዚሁ፡ እስከእኩለ ሌሊት ድረስ፡ "ከማታው"÷ ከእኩለ ሌሊት በኋላ ደግሞ፡ "ከሌሊቱ" እየተባለ፡ ጨረቃ ከምትታይበት፡ ወይም ጨለማው ከሚጀምርበት፡ ከምሽቱ፡ ፩ (አንድ) ሰዓት ይነሣና፡ ጎህ በሚቀድድበት፡ በንጋቱ ፲፪ (ዐሥራ ኹለት) ሰዓት ይቆማል፡፡

በዚህ መሠረት የተደለደለችው፡ አንዲቱ ዕለት፡ ሰባት ስትኾን፡ ፯ቱ ዕለታት፡ ፩ ሳምንት ይኾናሉ፡፡

የምዕራባውያኑ ግን፡ እንዲህ አይደለም፡፡

ምዕራባውያን፡ የሰሜኑንና የደቡቡን የመሬት ዋልታ ተከትለው፡ በሰሜንና በደቡብ ክፍላተ ዓለማት የሚኖሩ በመኾናቸው፡ የኢትዮጵያ ልጆች፡ ክረምት (የዝናም ወራት)፥ መፀው (የጽጌ=የአበባ ወራት)፥ ሓጋይ (የበጋ ወራት)፥ ጸደይ (የበልግ ወራት) እንደሚሉት፡ የእነርሱም ዓመት፡ Winter (ዊንተር)፣ Spring (ስፕሪንግ)፣ Summer (ሰመር) እና Autumn (ኦተምን)፥ ወይም፡ Fall (ፎል) በተባሉ፡ በአራት የተለያዩ ወራት ተከፋፍሎ፡ በክረምቱ፡ ሌሊታቸው፡ እስከ ፳ ሰዓታት የሚቀንስበት፥ በበጋው ወራት ደግሞ፡ መዓልታቸው፡ እስከ ፳ ሰዓታት የሚጨምርበት ኹኔታ አለ።

እንዲያውም፡ ወደሰሜኑም ኾነ ወደደቡቡ የመሬት ዋልታ ጫፍ እየተጠጉ በኼዱ መጠን፡ የሚቀነሱት፡ ወይም የሚጨመሩት ሰዓታት እያደጉ ይኼዱና፡ ወደመጨረሻው ጽንፍ ላይ ሲደርስ፡ ከናካቴው፡ ፮ ወራት ሙሉ፡ ሌሊት ብቻ፥ ወይም መዓልት ብቻ ይኾናል፡፡

ይህም ማለት፡ ይህ ኹኔታ፡ በሰሜኑና በደቡቡ ክፍላተ ዓለም፡ በዓመቱ ውስጥ፡ እንዲህ ስለሚፈራረቅ፡ የክረምቱ ብርዳማ ጠባይ፡ ቀደም ብሎ እንደተገለጸው፡ የሰሜኑን ክፍል በሚያጠቃበት ጊዜ፡ በደቡቡ ክፍል ደግሞ፡ የበጋው ፀሓያማ ጠባይ ይሰፍናል ማለት ነው፡፡

ይህ ብቻ ሳይኾን፡ በዓመት፡ ኹለት ጊዜያት፡ በየ፮ (በየስድስት) ወሩ፡ የሰዓት አቆጣጠራቸውን፡ እንደየክፍለ ዓለማቸው አቀማመጥ፡ በ፩ (አንድ) ሰዓት ያሳድጉታል፥ ወይም በ፩ (አንድ) ሰዓት ይቀንሱታል፡፡

የኢትዮጵያ ልጆች ዘንድ፡ ፯ቱ (ሰባቱ) የሳምንቱ ቀኖች፡ የእግዚአብሔር፡ የሥነ ፍጥረት ሥራው፡ በተራና በቅደም ተከተል የተካኼደባቸውንና በቅዱሳት መጻሕፍት የተመዘገቡትን የዕለታት ስም እንደያዙ፡ የአዳምና ሔዋን ቋንቋ በኾነው፡ በግእዝ፡ "አሐዱ"፡ "አንድ"፥ ወይም፡ "መጀመሪያ ቀን" ለማለት፡ "እሑድ"፥ ቀጥሎ፡ "ኹለት"፥ ወይም፡ "ኹለተኛ ቀን" ለማለት፡ "ሰኑይ"፡ "ሰኞ"፥ ቀጥሎ፡ "ሦስተኛውን ቀን"፡ "የሰኞ ማግሥት" ለማለት፡ "ማግሰኞ"፥ ቀጥሎ፡ "አራት"፥ ወይም፡ "አራተኛ ቀን" ለማለት፡ "ረቡዕ"፥ ቀጥሎ፡ "አምስት"፥ ወይም፡ "አምስተኛ ቀን" ለማለት፡ "ሓሙስ"፥"የሥራ ማካተቻ"፥ ወይም፡ "የሰንበት መግቢያ"፥ ወይም፡ "የሳምንቱ ጊዜ፡ የሚጠልቅበት ቀን" ለማለት፡ "ስድስተኛውን ቀን"፡ "ዓርብ"፥ በመጨረሻ፡ በሰንበት ጌታ፡ በኢየሱስ መሲሕ ትንሣኤ፡ ወደዘለዓለማዊነት ከመለወጧ በፊት፡ ቀድሞ የነበረችበትን ኹኔታ ለማስታወስ፡ "ሰባተኛዪቱን ቀን"፡ [በተለይ፡ ራሳቸውን፡ በኢትዮጵያ ስም የሚጠሩት፡ የግብፅ ኦርቶዶክስ ቅርንጫፍ ወገኖች፡ በስሕተት]፡ "ቅዳሜ" ብለው ይጠርዋቸዋል፡፡

ራሳቸውን፡ በኢትዮጵያ ስም የሚጠሩት፡ እኒሁ፡ የግብፅ ኦርቶዶክስ ቅርንጫፍ ወገኖች፡ በስሕተት፡ "ቅዳሜ" ብለው የሚጠሯትን፡ ይህችኑ አንዲት ሰንበት፡ እንደኢትዮጵያ ልጆች፡ በእውነተኛውና በትክክለኛው መለኮታዊ ስሟ፡ በደፈናው፡ "ሰንበት" ብለው በመጥራት ፈንታ፡ "ቀዳሚት ሰንበት"፥ ወይም፡ "ሰንበተ-አይሁድ"፣ እሑድንም፡ "ሰንበተ-ክርስቲያን" ብለው፡ አንዲቷን ሰንበት፡ እኹለት ከፍለዋት እያከበሯት ይገኛሉ። [ይህ የሰንበት ርእሰ-ነገር፣ በየቦታው፡ በአግባብ፡ አስፈላጊው ሓተታ እና ማብራሪያ ተሰጥቶበታል።]

ምዕራባውያን ግን፡ ቀድሞ፡ አረማውያን ሣሉ፡ ለእነዚሁ የሳምንት ቀኖች፡ የሰጧቸውን የአማልክታቸውን ስሞች እንመልከት፡- Sunday: Sun's day (ሳንዴይ)፡ ማለት፡ የፀሓይ ቀን፥ Monday: Moon's day (ማንዴይ)፡ የጨረቃ ቀን፥ Tuesday: Tui's day (ቲዩስዴይ)፡ ማለት፡ የጦርነቱ አምላክ፡ የቲዩ ቀን፥ Wednesday: Woden's day (ዌድንስዴይ)፡ ማለት፡ የታላቁ አምላክ፡ የዎደን ቀን፥ Thursday: Thor's day (ተርስዴይ)፡ ማለት፡ የነጐድጓዱ አምላክ፡ የቶር ቀን፥ Friday: Frigg's day (ፍራይዴይ)፡ ማለት፡ የታላቁ አምላክ፡ የዎደን ሚስት፡ የፍሪግስ ቀን፥ Saturday: Saturn's day (ሳተርዴይ)፡ ማለት፡ የሰማዩ ኮከብ፡ የሳተርን ቀን፡፡

በኢትዮጵያ ልጆች ዘንድ፡ ፴ (ሠላሳ) ዕለታት፡ ፩ (አንድ) ወር ሲኾኑ፥ ፲፪ (ዐሥራ ኹለት) ወራት እና ፭ (አምስት) ዕለታት ተሩብ ደግሞ፡ ፩ (አንድ) ዓመት ይኾናሉ፡፡ ፭ቱ (አምስቱ) ዕለታት ተሩብ፡ "ጳጉሜ" ይባላሉ፡፡ ግእዙ "ጳጉሜ"፡ የቃል ለቃል ትርጉሙ፡ "ተውሳክ"፡ "ጭማሪ"፥ "ተረፍ"፡ "ትርፍ" ማለት ነው፡፡ ፲፪ቱ (ዐሥራ ኹለቱ) የምዕራባውያን ወሮች ግን፡ ፳፰ (ሃያ ስምንት)፡ ዕለታትን፥ በየአራት ዓመቱም፡ ፳፱ (ሃያ ዘጠኝ) ዕለታትን ከያዘውና በተራው፡ኹለተኛ ከኾነው፥ (February ፌብሩአሪ) ከሚባለው ወር በቀር፡ እኩሌቶቹ፡ በ፴ (ሠላሳ)፥ የቀሩትም፡ በ፴፩ (ሠላሳ አንድ) ዕለታት ተመድበው፡ ይህን በመሰለ፡ የተዘበራረቀ መልክ ይቆጠራሉ፡፡

በኢትዮጵያውያንና በኢትዮጵያውያት በኩል፡ ከመስከረም እስከነሓሴ ድረስ ያሉት፡ ፲፪ቱ (ዐሥራ ኹለት) ወሮቻቸውና ጳጒሜ፡ እያንዳንዳቸው የሚጠሩበት ስም፡ ከእግዚአብሔር ከተሰጣቸው፡ የተፈጥሮ ጸጋቸው ጋር የተያያዘው ገጽታቸውን የሚያሳይ ትርጉም ያለው ሲኾን፡ በኢትዮጵያ ልጆች የወራት አመዳደብ መሠረት፡ ከSeptember (ሴፕቴምበር) መስከረም እስከAugust (ኦገሥት) ነሓሴ ድረስ ያሉት፡ የምዕራባውያኑ ወሮቻቸው ግን፡ እንደሳምንቱ ቀኖቻቸው ኹሉ፡ የተሠየሙት፡ በጣዖቶቻቸውና እንደአማልክት ይሰግዱላቸው በነበሩት ገዢዎቻቸው ስም ኾኖ ይገኛል፡፡

ይኸውም፡ መስከረምን፡ ከኢትዮጵያ፥ Augustን (ኦገሥትን)፡ ነሓሴን ደግሞ፡ ከምዕራባውያን፡ ለምሳሌ ያህል ወስደን ብንመለከታቸው፡ "መስከረም"፡ በኢትዮጵያኛ፡ "ከረመ" ወይም፡ "ክረምትን አሳለፈ" ከሚለው ግሥ ወጥቶ፡ "ክረምቱ የሚያበቃበት"፡ ማለትም፡ የዝናሙ ጠል አብቅቶ፡ የፀሓይ ብርሃን የሚፈነጥቅበት፥ የዓባይና የሌሎቹ ወንዞች ሙላትና መጉደል የሚጀምርበት፥ ፍጥረቱ ኹሉ፡ ከተሸሸገበት በዓቱ እየወጣም፡ እርስ በርሱ የሚገናኝበት፡ አዲሱ ዓመት፡ የሚገባበት ማለት ነው፡፡ "መስከረም ጠባ!" የሚባለውም ለዚህ ነው፡፡ በምዕራባውያን ዘንድ ግን፡ August (ኦገሥት)፡ ስለወሩ ኹኔታ፡ ምንም ትርጉም የሌለው ኾኖ፡ እንደጣዖት ይመለክ ለነበረው፡ ለአረማዊው ርእሰ ነገሥት (Emperor)፡ ለአውግስጦስ ቄሣር፡ በመታሰቢያነት የተሰጠ ወር መኾኑን ብቻ ያስረዳል፡፡

የኢትዮጵያውያንና የኢትዮጵያውያት ዓመት የሚጀምረው፡ በ"መስከረም"፥ የሚያበቃውም፡ በ"ጳጉሜ" ሲኾን፡ የምዕራባውያኑ ግን፡ በእነርሱ January (ጃንዋሪ)፡ ማለትም፡ በ"ጥር" ይጀምርና፡ በDecember (ዲሴምበር)፡ ማለትም፡ በ"ታኅሣሥ" ይጨርሳል፡፡ ስሙን፡ በመታሰቢያነት፡ January (ጃንዋሪ) ብለው፡ ለዓመቱ የመጀመሪያ ወር የሰጡለት፡ Janus (ጃኑስ)፡ ለሮማውያን፡ ታላቁ ጣዖታቸው እንደነበረ፡ ቀደም ብሎ ተመልክቷል፡፡

በኢትዮጵያ ልጆች ዘንድ፡ ፬ (አራት) ዓመታት፡ ፩ (አንድ) ዐውደ ዘመን ይኾናሉ። ይህም፡ እያንዳንዱ ዓመት፡ ፫፻፷፭ (ሦስት መቶ ስድሳ አምስት) ከሩብ ዕለታት፡ ወይም ከ፮ (ስድስት) ሰዓታት፥ ወይም፡ ከ፲፭ (ዐሥራ አምስት) ኬክሮስ ያለው ኾኖ፡ "ዘመነ ማቴዎስ"፥ "ዘመነ ማርቆስ"፥ "ዘመነ ሉቃስ" እና "ዘመነ ዮሐንስ" ተብሎ ተሠይሟል፤ እነዚህ፡ የ፬ቱ (አራቱ) ዓመታት ጳጕሜዎች ሰዓታት ሲደመሩ፡ ፩ (አንድ) ዕለት ይሞሉና፡ በ፬ኛው (አራተኛው) ዓመት፡ በዘመነ ሉቃስ መጨረሻ፡ ፮ (ስድስት) ዕለታት በመኾን፡ የባሕረ ሓሳቡ ቀመራ ይካተታል፤ የዘመን አቆጣጠሩም ዐውድ፡ እንዲህ፡ በየአራት ዓመታቱ ይዘጋል። (Encyclopaedia Britannica, CD 2000, Egyptian, Julian & Gregorian Calendar; Week; Months of the year.)

ስለዚህ፡ "የግሬጎሪ" ወይም "ግሬጎሪያን" ተብሎ የሚጠራው፡ የምዕራባውያን፡ የጊዜ አቆጣጠር ባህል፡ እንዲህ፡ ምስቅልቅሉ የወጣ በመኾኑ፡ በእርሱ ሰበብና ጠንቅ፡ ጽኑ የኾነው፡ ሃይማኖታዊና ተፈጥሮአዊ መሠረት ያለው፡ የኢትዮጵያ የዘመን አቈጣጠር ሥርዓት፡ ሊቃወስ ቀርቶ፡ ሊነካ እንኳ፡ ከቶ አይገባም።

## የኢየሱስ መሲሕን፡ የልደቱን ቀን ማናጋት፡ ያስከተለው ብርቱ ጠንቅ።

የእግዚአብሔር ወልድ፡ ኢየሱስ መሲሕ፡ የልደቱ ቀን፡ ከእውነተኛው ዕለት፡ ከመስከረም ፩ ቀን፡ ወደታኅሣሥ ፳፰ (ሃያ ስምንት)፥ ወይም፡ ፳፱ (ሃያ ዘጠኝ) ቀን በመዛወሩ፡ እስካኹን ከተገለጸው በቀር፡ በሃይማኖታችንና በምግባራችን፥ በአምልኳችንና በሥርዓታችን ላይ፡ ሌላ፡ ምን የባሰ ጠንቅን እንዳስከተለ ማወቁ፡ እንደሌላው ኹሉ፡ ስለሚጠቅም፡ በዚህ ቁም ነገር ላይ መተቸቱ አስፈላጊ ይኾናል።

በዚህ ረገድ ያለውን ዕውቀት ማግኘቱ፡ ለማንኛቸውም እውነተኛ ኢትዮጵያዊ፡ እና ኢትዮጵያዊት፡ የቱን ያህል የእፎይታ ስሜትን እንደሚሰጥ አይጠረጠርም፤ ምክንያቱም፡ ይህ ነገር፡ እውነተኞቹን የኢትዮጵያ ልጆች፡ እጅግ ሲያሳዝን፥ ሲያሳስብና ሲያስጨንቅ የኖረ፡ ከባድ ጉዳይ በመኾኑ ነው።

እዚህ ላይ፡ ነገሩ፡ ከተነሣ ዘንድ፡ ይህንኑ ከባድ ጉዳይ፡ እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ፥ እያንዳንዷም ኢትዮጵያዊት፡ በጋለ መንፈሳዊ ቅንዓት አጢነው፡ ለመልካም ፍሬ ሊያበቁት እንደሚገባ ልናሳስብ እንወድዳለን። በዚህ ረገድ፡ አንድ፡ የተለየ፡ ታላቅ ቁም ነገር መኖሩን ልንጠቁማችሁ እንፈልጋለን።

ይኸውም፡ እግዚአብሔር፡ በድንግል ማርያም፡ የአምላክ እናትነትና መድኃኒትነት፥ በእግዚአብሔር ወልድ፡ ኢየሱስ መሲሕም ቤዛነት፡ አርነት [ነጻ] አውጥቶ፡ የቅዱስ ኪዳኑ አገር፥ ሕዝብና መንግሥት የመኾንን፡ የክብር አክሊል፡ መልሶ ያቀዳጃቸውን፡ ኢትዮጵያን እና ልጆቿን፡ ዲያብሎስ፡ እንደገና ነጥቆ፡ የራሱ ተገዢዎች በማድረግ፡ በዚች፡ የሥጋዌ ምስጢረ-መለኮት በተፈጸመባት ልዩ በዓል አማካይነት፡ ከፍተኛ የአጥቂነት በደሉን፡ እንዴት ባለ ረቂቅ ስልትና ዘዴ ፈጽሞ፡ ድልን እንደተቀዳጀ፡ በገሃድ የሚያሳየውን እውነታ፡ በግልጽ ማቅረብ ነው።

እንግዴህ፡ በዚች ዕለት፡ ዲያብሎስ የተቀዳጃቸውን፡ ኹለት ድሎች፡ በማስተዋል ተመልከቷቸው፦

አንደኛ፡- እውነተኛዋ፡ የኢየሱስ መሲሕና የእናቱ፡ የቅድስት ድንግል ማርያም፡ የልደት ቀን በመኾኗ፡ ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት፡ ለሃይማኖታቸውና ለምግባራቸው፥ ለአምልኳቸውና ለሥርዓታቸው፡ አንዷ፡ ዋና መሠረታቸው ያደረጓትን፥ ደግሞም፡ "ርእሰ ዐውደ ዓመታችን ናት!" ብለው፡ በመጀመሪያ፡ በቤተ ክርስቲያን፡ የእግዚአብሔር እም፡ ድንግል ማርያም እና የእግዚአብሔር ወልድ፡ ኢየሱስ መሲሕ፡ ሥጋና ደም የኾነውን፡ ቅዱስ ቍርባንን በመቀበል፡ በፍጹም መንፈሳዊ ሓሤት፥ ከዚህ ቀጥለው ደግሞ፡ በየቤታቸው፡ የመልከ ጼዴቅን በረከት እና የፋሲካን ዕርድ በመሳተፍ፡ በታላቅ በዓላዊ ድምቀት ሊያከብሩዋት የሚገባቸውን፡ መስከረም ፩ ቀንን፡ ዲያብሎስ፡ ኹለንተናዋን፡ እርሱ ወደሚመለክበት፡ ወደታኅሣሥ ፳፰-፳፱ ቀን እንዲያዛውሩ ማድረጉ ነው።

ኹለተኛ፡- ዲያብሎስ፡ ያችኑ፡ ባዶ ኾና ያገኛትን፡ የተቀደሰችውን፡ መስከረም ፩ ቀንን፡ "ይህች ቀን፡ ዓመቱን ሙሉ፡ ለእኔ አሳልፋችሁ ያስረከባችሁኝን፡ በደም የታተመ፡ የአምልኮ ታማኝነታችሁን የምታረጋግጡባት፡ በነጻ ያገኘኋት፡ የእኔ ዕለት ስለኾነች፡ ከየቤታችሁ ሳትወጡ፡ ቀይ፥ ነጭ፥ ጥቍር ዶሮ፥ በግ፥ ፍሪዳ እያረዳችሁ፡ ደም አፍስሱልኝ! ጭዳ፥ ጨሌ፥ ቦረንትቻ፥ ቂጣ፥ ቆሎ፥ ርሚጦ እያላችሁ፡ መባ አቅርቡልኝ! በስሜ ተሰብስባችሁ፥ ቡና አፍልታችሁና ሣር ጐዝጕዛችሁ፥ ዕጣን ዐጢሳችሁና ቅቤ ተቀብታችሁ፡ እየበላችሁና እየጠጣችሁ፡ አምልኩኝ! አወድሱኝ!" ብሎ፡ ኢትዮጵያውያንንና ኢትዮጵያውያትን፡ በቅዱሱ ኪዳን፡ የድንግል እና የመሲሕ ሥጋና ደም በከበረችው፡ በኢትዮጵያ ምድራቸው ላይ፡ አምልኮ ባዕድን እንዲፈጽሙ ማድረጉ ነው::

ለዚህ ባዕድ አምልኮ የሚታረዱለትን፡ የእንስሳቱን የቀለም ዓይነት፡ ሰይጣን፡ "ቀይ፥ ነጭ፥ ጥቁር" ማለቱ፡ በክርስትና ጥምቀት ጊዜ፡ በሚጠመቀው ምእመን እና በምትጠመቀው ምእመኒት አንገት ላይ ሊታሠር የሚገባው፣ የኢትዮጵያ ልጆች፡ በኖኅ ቃል ኪዳን አማካይነት፡ ከፈጣሪያቸው፡ ከእግዚአብሔር አምላክ ያገኙት፡ አረንጓዴ፥ ብጫና ቀይ የኾነው፣ የቅዱሱ ኪዳን ሰንደቅ ዓላማ ቀለማት ማተባቸው፣ በግብፅ ኦርቶዶክስ መነኮሳት እና ጳጳሳት፡ ቀይ፥ ነጭና ጥቁር በኾነው፡ በግብፃውያን የአረማዊ ሰንደቅ ዓላማ ቀለማት ማተብ እንዲለወጥ የማድረጋቸውን፡ ረቂቅ ሰይጣናዊ ዘዴ ልታስተውሉትና ይህን የማተብ ቀለማት ነገር በሚመለከት፡ በሌላ ሥፍራና በሌላ ርእስ ሥር፡ ከተወያየንበት ሓተታ ጋር ልታስተያዩት ይገባል::

"ዐውደ ዓመት"፥ "ዕንቍጣጣሽ"፥ "የዘመን መለወጫ"፥ "ቅዱስ ዮሓንስ" እየተባለ፡ በግል እና በቤተሰብ፥ በኅብረተሰብ እና በአገር ዐቀፍ ደረጃ፡ ታላቅ በዓል ኾኖ በሚከበረው፡ በመስከረም ፩ ቀን፡ ምናልባት፡ ከእናንተም መካከል፡ ከዚህ የአምልኮ ባዕድ ሰይጣናዊ ቀንበር፡ እየራሳችሁን ነጻ ያወጣችሁ ካላችሁ፡ በቤተ ክርስቲያን ተገኝታችሁ፡ ለበዓሉ፡ ከተለመደውና ከሚጠበቀው የሰው ብዛትና ዓይነት ውስጥ፡ ከካህኑም፥ ከምእመኑም፡ ከወንዱም፥ ከሴቱም፡ ምን ያህሉ እንደመጣና እነርሱም፡ እነማን እንደኾኑ፥ በየቤቱም፡ ስለበዓሉ፡ በባዕድ አምልኮ መልክ የሚካኼደውን መሰናዶና የሚፈጸመውን ድርጊት፡ በቅርብ በማየትና በመከታተል፡ የዚህን እውነታ ትክክለኛነት፡ በቀላሉ ልትገነዘቡት ትችላላችሁ::

# ስለገና ዛፍ።

እዚህ ላይ፡ ተያይዞ ሊብራራ የሚገባ፡ ሌላ ዋና ነገር አለ፤ ይህም፡ የገናን ዛፍ የሚመለከት ነው። ቀደም ብሎ በተሰጠው ሓተታ እንደተብራራው፡ የክርስትናን እምነት የተቀበሉት አረማውያን፡ እውነተኛውን፡ የኢየሱስ መሲሕን የልደት ቀን፡ የጣዖትና የባዕድ አምልኮ ልማዳቸውን ወደሚፈጽሙበት ዕለት አዛውረው፡ በዚያን ዕለት እንዲከበር መወሰናቸውና ይህንኑ ውሳኔያቸውን፡ በተግባር ማዋላቸው፡ ያለውን አስፈላጊነትና ተገቢነት፡ በቀላሉ ሊገባን ይችል ይኾናል። ይኸውም፡ እንኳንስ፡ የሃይማኖት መሰሎቻችን የኾኑት፡ የግብፃውያንና የእኛዎቹ ኢትዮጵያውያን እና ኢትዮጵያውያት ወገኖች፡ ግብረ አበርነትና መተባበር ታክሎበት ይቅርና፡ በራሳቸው፡ በአረማውያኑ ዘንድ ብቻም ቢኾን ማለት ነው።

እኛ፡ በቅዱሱ ኪዳን ሃይማኖትና ምግባር፥ አምልኮና ሥርዓት ጸንተን ለኖርነው የኢትዮጵያ ልጆች ግን፡ ይህን፡ ግብፃውያንን የሚጨምረውን፡ የአሕዛብ ውሳኔ ለመቀበል፡ በእርግጥ ይከብደናል። ስለዚህ፡ እስካኹንም፡ አልተቀበልነው፤ ወደፊትም አንቀበለውም።

"ታዲያ! በዚያ፡ በጣዖትና በባዕድ አምልኮ ኖረው፡ በኪዳነ ኦሪቱም በኩል እንኳ ሳያልፉ፡ በቀጥታ ወደክርስትና እምነትና ሕይወት የገቡት ወገኖች፡ ግብፃውያን ጭምር፡ 'የእግዚአብሔራችን፡ የኢየሱስ መሲሕ፡ የልደት በዓሉ ቀን ይኹን!' ብለው፡ በራሳቸው አቈጣጠር፡ በDecember 25 (ዲሴምበር ፳፭)፡ በየቦታው፡ የገና ዛፍ ብለው፡ ሸልመው በሚያከብሩበት ጊዜ፡ ስለዚሁ ሥርዓታቸው፡ ለራሳቸውና ለልጆቻቸው፥ ለሌላውም ለማስረዳት፡ ለእነርሱ፡ በቂ ምክንያት ይኖራቸው ይኾናል።

ለእኛ፡ ለኢትዮጵያ ልጆች ግን፡ "እንዲህ ነው!" ብለን፡ ለእየራሳችንም ኾነ፡ ለልጆቻችን፥ ለሌላውም ለማስረዳት፡ እጅግ ያዳግተናል፤ የአኹኑ የኢትዮጵያውያንና የኢትዮጵያውያት የገና በዓል፡ የባዕዳኑን አቆጣጠር ተከትሎ፡ በታኅሣሥ ፳፰፥ ወይም፡ ፳፱ ቀን እንዲከበር ተደርጎም እንኳ፤ ከእነርሱ በዓል ጋር በአንድ ቀን፡ ዐብሮ ሊውል አለመቻሉ፡ ይኸው ይታያል፤ ስለዚህ፡ የበዓሉ ቀን፡ አኹን ባለው እየቀጠለም ቢኾን፡ ወደፊት፡ በአገር ደረጃ፡ ወደጥንታዊው ትክክለኛ ቀመሩ፡ ወደመስከረም ፩ ቀን እስከሚመለስበት ጊዜ ድረስ፡ እኛ የኢትዮጵያ ልጆች፡ በቅዱሱ ኪዳን ሃይማኖታችን ምክንያት፡ ዐውቀንም ኾነ፡ ሳናውቅ፡ በየግላችንም ኾነ፡ በየቤተሰባችን፡ ይህን ስሕተት ከመፈጸም ልንታቀብና ልንጠነቀቅ ይገባናል፤ ምክንያቱም፡ ይህ፡ የገናው ዛፍ ነገር፡ የአምልኮ ጠንቅ ስላለበት ነው።

ባኹኑ ጊዜ፡ አንዳንድ ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት፥ ካለማወቅ የተነሣ ይመስላል፥ ኢትዮጵያዊዉን የልደት በዓል፡ በየቤታቸው፥ ሕዝባውያን በኾኑ ቦታዎች ሳይቀር፡ በምዕራባውያን ልማድ፡ በጥድ ዛፍ ሲያከብሩት ይታያል። ዳሩ ግን፡ ይህ ድርጊት፡ የሃይማኖት አምልኳችንን የሚነካ በመኾኑ፡ እንኳንስ ሊደረግ፡ ሊታሰብም የሚገባ አይደለም። እንዲህ እንዳይኾንም፡ ከአኹኑ፡ በብርቱ ሊነቃበት ያስፈልጋል።

በተለይ፡ ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት ልጆች፡ ስለዛፉ በሚጠይቁበት ጊዜ፡ ጉዳዩ፡ ሃይማኖታችንንና አምልኳችንን የሚመለከት በመኾኑ፡ ስለሚሰጠው ምላሽ፡ ወላጆችም ኾኑ መምህራን፥ አረጋውያን ወንዶችም ኾኑ ሴቶች፡ በብርቱ ሊዘጋጁበት ያሻል።

የኢትዮጵያ ሕፃናት ልጆች፡ በቤታቸው፥ ወይም፡ በሕዝብ ቦታዎች ተሰናድቶ ስለሚያዩት፡ ስለገናው ዛፍ፡ ጥያቄያቸውን ሲያቀርቡ፡ ኢትዮጵያውያኑና ኢትዮጵያውያቱ፡ የሚሰጧቸው መልስ፡ ምን ሊኾን ነው? ምዕራባውያኑ፡ ለልጆቻቸው፡ "የክርስትናን ሃይማኖት ከመቀበላችን በፊት፡ በዛፍ እናመልክ ስለነበር ነው!" ብለው የሚሰጧቸውን መልስ የመሰለ ሊኾን ነውን? ወይስ፡ ሌላ ምን ዓይነት ምክንያት ልናቀርብላቸው ነው? ከማፈር በስተቀር፡ ምንም የሚነገር ነገር ከቶ አይኖርም፡፡ ደፍሮ፡ ታሪኩን፡ ቀደም ብዬ በዘረዘርሁት መልክ የሚያብራራላቸው ቢኖር እንኳ፡ መቼም፡ የዘመኑ ልጆች፡ ንቁ ጠያቂዎች ናቸውና፡ "ታዲያ! እኛ፡ ለምንድር ነው፡ ይህን፡ የገናን በዓል፡ እንደፈረንጆቹ፡ በዚህ፡ በዛፉ የምናከብረው?" ብለው፡ መልሰው ቢጠይቁን፡ የምንሰጣቸው፡ ምን መልስ ይኖረን ይኾን? በአግባቡ በጠየቁን ልጆቻችን ፊት፡ ከማፈር፥ ወይም፡ ከመዋሸት በቀር፡ ምንም ዓይነት መልስ፡ ከቶ አይኖረንም፡፡

እንግዲህ፡ ምዕራባውያን ኾኑ ምሥራቃውያን፤ ሰሜናውያን ኾኑ ደቡባውያን፡ የገና በዓላቸውን፡ በተጌጠ የጥድ ዛፍ የሚያከብሩት፡ በምን ምክንያት መኾኑን፡ ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት ልጆቻችን፡ በትክክል እንዲያውቁት ከማድረግ በቀር፡ ነገሩን እንደቀላልና እንደዋዛ በማየት፥ ወይም፡ "ልጆችን ያስደስታል!"፥ ወይም፡ "ከማን አንሼ!" በማለት፡ ደን የሚያራቁተውን፡ ይህን የመሰለውን ድርጊት መፈጸሙ፡ በሥጋም፥ በነፍስም፥ በመንፈስም፡ ከባድ ችግር ውስጥ መግባት መኾኑን አውቀን፡ በእኛ በኩል፡ በጊዜው፡ ተገቢውን ጥንቃቄ ልናደርግ ግድ ይኾንብናል፡፡

ስለዚህ፡ ይህ ጉዳይ፡ ሃይማኖትንና አምልኮን የሚመለከት በመኾኑ፡ ወላጆችም፥ መምህራንም፤ አሳዳጊዎችም፤ ሞግዚቶችም፥ ከዚያም በላይ፡ ማናቸውም ኢትዮጵያዊና ኢትዮጵያዊት፥ ኹላችንም፡ ለልጆቻችን፡ ልናሳውቃቸውና ልናስተምራቸው የሚገባን፡ አዎን! እኛ፡ የኢትዮጵያ ልጆች፡ ኹላችን፡ ከዚህ የሚከተለውን በመፈጸም ነው፡-

አንደኛ፡ የፈጣሪያችን፡ የኢየሱስ መሲሕን የልደት በዓል የምናከብረው፡ በኢትዮጵያዊው የቀን አቆጣጠር ሥርዓት እና ስልት፡ <u>በመስከረም ፩ ቀን</u> እንጂ፡ በታኅሣሥ ፳፰ ወይም ፳፱ አለመኾኑን፥ ደግሞም፡ እንደኢትዮጵያዊው ሥርዓት፡ በቅድሚያ፡ በቤተ ክርስቲያን ተገኝተን፡ የድንግል ማርያምን እና የኢየሱስ መሲሕን፡ ቅዱስ ሥጋና ክቡር ደም በመቀበል፤ ቀጥሎም፡ በየቤታችን፡ የተሰናዳውን፡ የፍስክ ድግስ በመጋበዝ እንጂ፡ እንደባዕዳኑ፡ በየቤታችን ኾነ በሕዝባዊ ቦታዎች፡ የጥድ ዛፍን በማስጌጥና በመሸለም፥ በባዕድ አምልኮ ልማድም፡ የእንስሳትን እና ዶሮን የመሰሉትን የአዕዋፋትን ደም አፍስሶ፡ የእነርሱን ሥጋ በመብላት አለመኾኑን በማብራራት፡ ይህን የመሰለው አጉል ባህል እንዳይለመድ፥ ለተተኪውም ትውልድ እንዳይተላለፍ መታገሉ፡ የእነርሱም ግዳጅ መኾኑን፥

ኹለተኛ፡ ጥንት፡ ከአዳምና ሔዋን ጀምሮ፡ በኪዳነ ልቦና፥ በመካከሉ፡ በኪዳነ ኦሪት፥ በመጨረሻም፡ በኪዳነ መንፈስ ቅዱስ፡ እስከዛሬ የኖርነው፥ ዛሬም እየኖርን ያለነው፥ ወደፊትም የምንኖረው፡ የጽላትና የታቦት ሥርዓታችን፡ ከዚሁ፡ ከገናው ዛፍ አምልኮ ጋር ተመሳሳይ ኾኖ እንዳይገኝ፡ ማድረግ ስለሚገባን ጥንቃቄ፡ በዚህ የኅዋ ሰሌዳችን ላይ ተዘርዝረው በወጡት መጽሓፎቻችን እና በየኅዋ መድረኮቹ በሚነበቡት መልእክቶቻችን ውስጥ፡ የተሰጡት ሓተታዎች እንደተጠበቁ ኾነው፡ ያው፡ በእውነትና በመንፈስ፡ በምንፈጽመው፡ በአምልኮተ እግዚአብሔር ሥርዓታችንና ባህላችን ብቻ መኾኑን ነው፡፡

## ስለሺሁ ዓመት፡፡

የኢትዮጵያ ልጆች የዘመን አቆጣጠር ሥርዓት፡ ትክክልና እውነተኛው መኾኑን፡ ለመጨረሻ ጊዜ ለማረጋገጥ የሚያበቃው ከፍተኛ ነጥብ የሚገኘው፡ ስለዚሁ፡ ስለ"ሺሁ ዓመት" ምስጢርና ፍጻሜው፡ የእኛው ሥርዓት ከሚሰጠው የትርጓሜ ሓተታ ነው፡፡ ይህም ሓተታ፡ ባለምሥራቹ (ወንጌላዊው) ቅዱስ ዮሓንስ፡ ስለዚሁ፡ የሺ ዓመቱ ምስጢር፡ በራእይ አይቶ የጻፈውን ትንቢታዊ ቃል፡ መሠረት ያደረገ መኾኑ ይታወቃል፡፡ (ራእ. ፳፥ ፩-፲፡፡)

ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት፡ እንዲህ፡ በቅዱሳት መጻሕፍት የተረጋገጠውን፡ የእግዚአብሔርን ሥርዓት በመከተል፡ እስከዛሬ ጠብቀውት የኖሩትን፡ መሠረታዊዉን የጊዜ አቆጣጠር ስልት፡ ምዕራባውያንና ምሥራቃውያን፥ ኦርቶዶክሳውያን የተባሉትን አብያተ ክርስቲያናት ጨምሮ፡ በአረማዊው፡ ዩልየስ ቄሣርና ግሬጎሪ ፲፫ኛ በተባለው፡ በካቶሊካዊው ርእሰ ሊቃነ ካህናት ስሞች እየሰየሙ፥ በየጊዜውም እየለዋወጡ፥ በመጨረሻ፡ ፰ (ስምንት) ዓመታት ከ፲ (ዐሥር) ቀናት ያህል አክለውበት በመቆየታቸው መኾኑ፡ ቀደም ብሎ ተገልጿል፡፡

ከዚህ የተነሣ፡ ከላይ የተጠቀሰው፡ በራእየ ዮሓንስ የተነገረው፡ የሺሁ ዓመት ምስጢር፡ እንደእነርሱ አቈጣጠር፡ "፩ (አንድ) ሽህኛው ዓመት ተፈጽሞ፡ ፪ (ኹለት) ሽህኛው ዘመን በጀመረባት የጥር ወራቸው መግቢያ እኩለ ሌሊት ላይ በነበረችው፡ በዚያች፡ የመጀመሪያ ሰዓት ይከሠታል!" ብለው፡ በታላቅ ሥጋትና ፍርሃት፥ የመንፈስ ንቃትም፡ የጠበቁት፡ "የዓለሙ ፍጻሜ" ሳይደርስ አልፏል! ታዲያ! የዚህ ምክንያት፡ ምን ይኾን? እነዚያ፡ በሰውኛ ፍልስፍና ታስበውና ተቀምረው የታከሉት፡ ፰ (ስምንት) ዓመታት ከ፲ (ዐሥር) ቀናት፡ በኢትዮጵያኑ አቈጣጠር ላይ መጨመራቸው፡ ስሕተት መኾኑን ለማጋለጥ ይኾንን? አዎን! ነው።

እንግዴህ፡ በዚህ ረገድ፡ ሊጠበቅ የሚገባው፡ በእውነተኛዋ ሃይማኖት ላይ የጸናው፥ ዛሬ የሚሠራበትና ከሽሁ ዓመት ማብቂያ ቀጥሎ፡ እነሆ! በዚህ፡ በአዲሱ፡ የዘመን መለወጫ በኾነው፡ በዘንድሮው ርእሰ ዐውደ-ዓመት በዓላችን፡ ዐሥረኛውን ዓመት መጨመር የጀመረው፡ ይህ የኢትዮጵያውያን የጊዜ አቈጣጠር ሥርዓት ነው፡፡

ይኸው፡ ኢትዮጵያዊው ሥርዓት፡ የተመሠረተው፥ የቆመውና የተደመደመው፡ በእግዚአብሔር ቃልና አምልኮት ላይ ስለኾነ፡ ዕድሜውን ያገኘው ሰው፡ ይህ መለኮታዊ ምስጢር ተገልጾ የተነገረበት፡ "ኢትዮጵያ፡ የዓለሙ መፋረጃ!" የሚለው መጽሓፍ ታትሞ ከወጣበት፡ ከ፩ሺ፱፻፹፫ ዓ. ም. በኋላ፡ ለ፯ ዓመታት ቆይቶ፡ በገባችው፡ በዚያች በ"ሺዋ ዓመት" ፍጻሜ የደረሰውን፡ የራእየ ዮሓንስን የምስጢር ክሥተት፡ በዚሁ የኅዋ ሰሌዳችን አማካይነት ተላልፎ በተነበበው፡ የኹለት ሺህኛው ዓመተ ምሕረት መልእክት እንደተብራራው፡ ሊያየው በቅቷል፡፡

## የድንግል ማርያምን እና የኢየሱስ መሲሕን የልደታት ቀን፡ ወደየተገቢው ጥንተ-ቦታቸው ስለሚመለሱበት መንገድ።

የኢትዮጵያን ልጆች የዘመን አቈጣጠር ሥርዓት በመከተል፡ ወደየነበሩበት የጥንት መደበኛ ቀናቸው ሊመለሱ የሚገባቸውን በዓሎቻችንን እና ጾሞቻችንን በሚመለከት፡ እዚህ ላይ፡ አንዳንድ የማጠቃለያ ቍም ነገሮችን ማውሳት አግባብ ይኾናል።

ይኸውም፡ በግብፅ ኦርቶዶክሳውያን መነኮሳት እና ጳጳሳት፡ ሃይማኖታዊ ተፅዕኖ ምክንያት፡ ለ፩ሺ፮፻ (አንድ ሺህ ስድስት መቶ) ዓመታት ያህል፡ እንዲህ ሥር ሰድዶ፡ በኢትዮጵያ እና በልጆቿ ዘንድ የኖረው፡ በተለይ፡ ይህ የተሳሳተ የልደት በዓል አከባበር፡ ወደነበረበት ጥንታዊ እና ኢትዮጵያዊ ሥርዓቱ እንዲመለስ ለማድረግ፡ ስለሚቻልበት ኹኔታ ማለት ነው።

መቼም፡ እንደሚታወቀው፡ "ሃይማኖት"፡ ቀላል ነገር አይደለም፤ እኛ ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት፡ "ሃይማኖት ነው!" ብለን የያዝነው፡ የህልውና አቋማችን፡ ከፈጣሪያችን፡ ከእግዚአብሔር ጋር፡ በእውነት እና በመንፈስ ቅዱስ የሚያገናኘን፣ አንድ የሚያደርገንም፡ የአምልኮ ሐረግ ነው።

<u>የምናምነውና የምናመልከው እግዚአብሔር ደግሞ፡ እውነት እንጂ፡ ሓሰት ስለማይስማማው፡ ይህንኑ ሃይማኖታችንን፡ በሓሰት ሳይኾን፡ በእውነት፥ በተራ ግዴለሽነትና በቀላል ወላዋይነት ሳይኾን፡ በከፍተኛ ጥንቃቄና በፍጹም ታማኝነት፡ ልንጠብቀው የሚገባን ታላቅ ጉዳይ ነው።</u> ይህ አባባላችን፡ እሙን ስለመኾኑ፡ በማናቸውም ሰብአዊ ፍጡር ዘንድ የታወቀ ነውና፡ በምንም አያከራክርም።

እንዲህ ከኾነ፡ አምላክ ሰው በኾነበት፡ በዚህ፡ በታላቁ የልደት ቀን ላይ የሚኖረን ሃይማኖታዊ አቋም፡ እግዚአብሔር በሚወድደውና በሚቀበለው እውነት ላይ የተመሠረተ ሊኾን ይገባል ማለት ነው፤ ከዚህ በቀር፡ በሌላው "በሓሰቱ መንገድ፡ 'ይቀጥል!' የሚል፡ እውነተኛ ኢትዮጵያዊ ይኖራል!" ብለን አንገምትም። ባለማወቅ ሲሠራበት ለቆየው ስሕተት፡ ተጠያቂነቱ፡ በቀጥታ፡ ዐውቀው ያጠፉትን የሚመለከት ሲኾን፡ ይኹን እንጂ፡ ባላወቁት ዘንድ፡ በኅሊናም፥ በእግዚአብሔርና በሰውም በኩል፡ ከተጠያቂነቱ ነጻ እንደሚኾኑ፥ እውነቱን ካወቁት በኋላ ግን፡ ለማንም፡ ምንም ዓይነት ምክንያት በማቅረብ፡ ከተጠያቂነቱ ለማምለጥ፡ ከቶ እንደማይቻል፡ ማረጋገጡ አግባብ ይኾናል።

አኹን፡ ይኸው ጉዳይ፡ ሃይማኖትንና አምልኮን የሚነካ፥ እያንዳንዱን ኢትዮጵያዊና እያንዳንዷን ኢትዮጵያዊት፡ በኃላፊነት የሚያስጠይቅ ከመኾኑ የተነሣ፡ በግለሰብ ደረጃ እየተፈጸመ የሚቆይ እንጂ፡ "በአኹኑ ጊዜ፡ በአገር ደረጃ፡ በሥራ ላይ ሊውል ይቻላል!" ብሎ ለማሰብ ያዳግታል። በሥራ ላይ ሊውል የሚችለው፡ በኢትዮጵያ፡ ጸንቶ የኖረው፡ የእግዚአብሔር ሥርዓተ መንግሥት፡ በቅድሚያ፡ በምድሪቱ ስፋት እና በሕዝቡ መካከል፡ በይፋ መስፈን ሲጀምር ብቻ ይኾናል። በዚያን ጊዜ፡ ይህም ኾነ፥ በቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነት ላይ፡ የክህደት፥ የዓመፅና የአምልኮ አመንዝራነትን ኃጢአት የፈጸመው፡ "ኢትዮጵያዊ ነኝ!" በሚለው በዚህ ትውልድ ላይ፡ ያለማቋረጥ እየወረደ ላለው መከራ፡ ጠንቀኛ ምክንያቶች የኾኑት፡ ሌሎቹ ተመሳሳይ ጉዳዮች፥ ኹሉም፡ ቤተ ክህነቱንና ቤተ ምልክናውን አጠቃልሎ በያዘው፡ በቤተ ሕዝቡ ታይተውና ተመክሮባቸው የሚወሰኑ ይኾናሉ።

እስከዚያው ግን፡ "በተለይ፡ ስለእግዝእተብሔራችን ድንግል ማርያም እና ስለእግዚአብሔራችን ኢየሱስ መሲሕ የልደታት ቀን፡ የኢትዮጵያ ልጆች ውሳኔ፡ ምን ሊኾን ይገባል? በአኹኑ ዘመን ለምንገኝ ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት፡ ያለን ምርጫ፡ የትኛው ነው?

የእግዝእተብሔራችን የድንግል ማርያም፡ የልደቷ ቀን፥ ለእኛም በዓላችን ኾና ልናከብራት የሚገባን ዕለት፡ ከኹለቱ ዕለታት፡ ማለትም፡ ከግንቦት ፩ዱ እና ከመስከረም ፩ዱ ቀን፡ የትኛዋ ናት?

**ደግሞም፡ የእግዚአብሔራችን የኢየሱስ መሲሕ የልደቱ ቀን፥ ለእኛም በዓላችን ኾና ልናከብራት የሚገባን ዕለት፡ ከኹለቱ ዕለታት፡ ማለትም፡ ከታኅሣሥ ፳፱ኛ እና ከመስከረም ፩ዱ ቀን፡ የትኛዋ ናት?"** ለሚሉት ጥያቄዎች፡ በየግላችን፡ ተገቢውን መልስ በመስጠት መቆየት ያስፈልገናል።

ቀደም ብለን እንዳመለከትናችሁ፡ ነገሩ፡ የቅዱሱን ኪዳን ሃይማኖትን የሚነካ፡ ከበድ ጉዳይ ስለኾነ፥ በዚሁ ሃይማኖታችን አማካይነት፡ እውነቱን ዐውቀነው እና ተቀብለነው ባጸናነው፡ የመምረጥ ነጻነታችን እና የመወሰን ሥልጣናችን ተጠቅመን፡ እውነተኛዪቱ እና ትክክለኛዪቱ ዕለት፡ የትኛዋ እንደኾነች፡ በእግዚአብሔር እውነት እና መንፈስ፡ መርጠን እና ወስነን፡ አንደኛዪቱን መያዝ አለብን፡፡

ይህን ምርጫ እና ውሳኔ፡ በየግላችን እናደርግ ዘንድ፡ ከየፊታችን የሚቀርቡት እውነታዎች፡ ኹለት ናቸው፡፡ ከእነዚህ እውነታዎች መካከል፡-

የመጀመሪያው፡- **"እግዝእተብሔር እም ድንግል ማርያም፡ ሥነ- ፍጥረቱና ቀደምቱ ሰዎች፡ "ተወለዱባት! [ተፈጠሩባት!]"፥ እግዚአብሔር ወልድ፡ ኢየሱስ መሲሕም፡ "በጽኑ ቀጠሮው፡ አንዲት ሰዓት እንኳ ሳያሳልፍ "ተወለደባት!" ያሰኘው እና "ዓመተ ምሕረት" ብለን ዓመቱን የጀመርንበት፡ ጥንታዊው የዘመን አቆጣጠራችንም፡ በእግዚአብሔር አምልኮ፥ በቃሉና በመንፈሱ ተመሥርታ፥ ጸንታና ሕያው ኾና የኖረችው፡ ያች፡ የኹለቱም የልደታት ዕለት፡ "መስከረም ፩ ቀን ናት!" ብሎ ያረጋገጣትና የመሰከረላት ስለኾነ፡ የኢትዮጵያ ወደኾነው፡ ወደዚያ፡ ወደመሠረቱ፥ ወደጥንታዊው ተመልሰን፥ ያንኑ አጽንተን፡ ልናከብር የሚገባን፡ እርሷን፡ መስከረም ፩ [አንድ] ቀንን ነው!"** የሚል ይኾናል።

ኹለተኛው ደግሞ፡- "ይኼ፡ ከእግዚአብሔር ያገኘነው፡ ጥንታዊዉና መልካሙ ሥርዓታችን ተሠርዞ፡ በጣዖት አምልኮ እና በአረማውያን ባህል ላይ በተመሠረተው፡ በባዕዳኑ ሰብአዊ ዘዴ የተተካውን አሠራር ተቀብለን፡ ከወገኖቻችን መካከል፡ ብዙዎች እንዳደረጉት፡ እኛም፡ የቀረነው፡ ኢትዮጵያዊነታችንን ክደን፤ የቀን አቆጣጠራችንንም ዘይቤ ለውጠን፥ በባዕድ አምልኮውም ተዘፍቀን፥ ወደዲያብሎስ ግዛትና ወደአሕዛቡ ሥርዓት፡ ጠቅልለን እንግባወይ?" የሚል ነው፡፡

እንግዲህ፡ ቀደም ባሉት ሐተታዎቻችን፡ መላልሰን እንዳወሳነው፡ ይህ ጉዳይ፡ ሃይማኖትንና አምልኮን የሚመለከት ስለኾነ፡ በተለይ፡ በእኛ በኢትዮጵያ ልጆች ዘንድ፡ እንደማናቸውም ተራ ነገር፡ እንዲያው፡ በዝምታ፥ ወይም፡ በቸልታ፥ ወይም፡ በቆይታ፥ ወይም፡ በእይታ፡ ሊታለፍ የሚገባው አይደለምና፡ አኹን ለጊዜው፡ እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ እና እያንዳንዷ ኢትዮጵያዊት፡ በየግላቸው፥ ወደፊትም፡ በጊዜው፡ በቤተ ሕዝብ፥ በቤተ ክህነትና በቤተ ምልክና አባልነታቸው፡ የሚገባቸውን የመምረጥ እና የመወሰን ግዳጃቸውን እንዲፈጽሙ፡ ኃላፊነቱን፡ ከጽኑ አደራ ጋር፡ ለየራሳቸው በመተው፡ ይህን አጭር ትችት፡ በዚሁ እንገታዋለን፡፡ (ኢትዮጵያ፡ የዓለሙ መፋረጃ! ፲፱፻፺፫ ዓ. ም. በንቡረ እድ ኤርምያስ ከበደ ወልደ ኢየሱስ፤ ገጽ ፩፻፴፬-፩፻፶፫፡፡)

## በዓለ ግዝረት፡፡

"በዓለ ግዝረት"፡ ሰላማችን፡ ሕፃን ኢየሱስ መሲሕ፡ ከቅድስት ድንግል ማርያም፡ በቤተ ልሔም፡ በበረት፡ ከተወለደ በኋላ፡ **"ወአመ ተፈጸመ ሰሙን ዕለት፣ ወሰድዎ ለሕፃን፡ ከመ ይግዝርዎ፤ ወሰመይዎ ስሞ፡ 'ኢየሱስ'፡ በከመ ሰመዮ መልአክ፡ እምቅድመ ትፀንሶ በከርሣ።** ስምንት ቀንም በተፈጸመ ጊዜ፡ ሕፃኑን ሊገዝሩት፡ ወሰዱት፤ ስሙንም፡ ገና በማሕፀን ሳይፀነስ፡ አስቀድሞ፡ መልአኩ እንደሰየመው፡ 'ኢየሱስ' አሉት፡፡" በሚለው፡ የባለምሥራቹ (የወንጌላዊው) ቃል መሠረት፡ በ፰ኛው ቀን፡ "ኢየሱስ" ተብሎ፡ የኪዳነ አብርሃምን ሥርዓት የፈጸመበትን ዕለት በማስታወስ፡ የምናከብረው በዓል ነው፤ እርሱም፡ "በዓለ ግዝረተ ኢየሱስ" ተብሎ፡ በመስከረም ፰ ቀን ይከበራል፡፡ (ሉቃ. ፪፥ ፳፩፡፡)

እኛ የኢትዮጵያ ልጆች፡ ይህን በዓል የምናከብረው፡ የሰላማችን፡ የኢየሱስ መሲሕን ግዝረት ለማስታወስ ብቻ ሳይኾን፡ ሥርዓቱን፡ ቀድሞም፡ በኪዳነ ልቦና፡ ማለትም፡ ከአብርሃም በፊት በኖርንበት አምልኮተ እግዚአብሔር፡ በተፈጥሮ ባሕርያችንና በገዛ ፈቃዳችን፡ የልብ ግርዛትን በመቀበል፡ ስንፈጽመው የቆየን፥ ኋላም፡ በኪዳነ ኦሪቱ፡ በአብርሃም፥ በመጨረሻም፡ በኪዳነ መንፈስ ቅዱስ ምክንያት፡ ያንኑ፡ ጥንታዊ ሥርዓታችንን አጽንተን የቀጠልን መኾናችንን ለማረጋገጥ ጭምር ነው። በዚህም፡ እየራሳችንን፡ በቅዱሱ ኪዳን ጸጋ፡ በነፍስ፡ የሃይማኖትን ግዝረት፥ በሥጋም፡ የምግባርን ግዝረት ተቀብለን፣ በመንፈስ ቅዱስም፡ ከእግዚአብሔር ያገኘነውን፡ አማናዊዉን፡ የልጅነት ክብር የተቀዳጀን መኾናችንን እናዘክርበታለን፡፡

## በዓለ መስቀል፡፡

አምላካችንና ሰላማችን ኢየሱስ መሲሕ፡ ራሱን፡ በቤዛነት አመሳቅሎ በመዘርጋት፥ እጆቹንና እግሮቹንም በመቸንከር፡ ሥጋውን የቀረሰበትን እና ደሙን ያፈሰሰበትን፡ የትስብእት አካሉን የተሸከመው ዕፀ መስቀል፡ ተፈልጎ የተገኘበትና ተቆፍሮ የወጣበት፡ የመታሰቢያ ዕለት፡ በየዓመቱ፡ በመስከረም ፲፯ ቀን ታስቦ፡ በጥልቅ መንፈሳዊ ስሜት፣ በታላቅ የበዓል ሥርዓትም ይከበራል፡፡

ይኸውም፡ **"ንሰግድ ለመስቀለ-እግዚእነ፡ ኢየሱስ መሲሕ፣ ዘተቀደሰ በሥጋሁ፣ ወበደሙ ክቡር፣ ዘነሥአ፡ እምእግዝእትነ ድንግል ማርያም። መስቀል፡ ኃይልነ! መስቀል፡ ጽንዕነ! መስቀል፡ ቤዛነ! መስቀል፡ ሰላመ-ነፍስነ፣ ወሥጋነ፣ ወመንፈስነስ! አይሁድ፡ ክህዱ! ንሕነሰ፡ አመነ፤ ወእለ አመነ፡ በኃይለ-መስቀሉ ሞእነ!** ከእግዝእተብሔራችን ድንግል ማርያም በነሣው ሥጋ ለተቀደሰው፣ በደሙም ለከበረው፡ ለአምላካችን፡ ለኢየሱስ መሲሕ መስቀል እንሰግዳለን! መስቀል፡ ኃይላችን ነው! መስቀል፡ ጽናታችን ነው! መስቀል፡ ቤዛችን ነው! መስቀል፡ የነፍሳችን፣ የሥጋችን እና የመንፈሳችን ሰላም ነው! አይሁድ፡ ካዱት! እኛ ግን፡ አመንንበት! ያመንንበት እኛም፡ በመስቀሉ ኃይል፡ ክፉዉን አሸነፍን!" የሚል ትርጉም ያለውን ጸሎታችንን፡ በግእዝ፡ በየዕለቱ ማለዳ ጀምረን፡ በቀኝ እጃችን ጣቶች፡ የመስቀል ምልክትን በመሥራት፡ ፊታችንን በማማተብ፥ ኹለቱን እጆቻችንንም፡ ወደየጎናችን በመዘርጋት፡ ራሱን፡ ኹለንተና ሰውነታችንን፡ የመስቀል ምልክት በማድረግ፡ መላልሰን የምንጸልይበትንና የክርስትና ምልክታችን አድርገን፡ በየሰውነታችን ላይ የተነቀስነውን፣በየአንገታችንም ላይ፡ በማተባችን ያንጠለጠልነውን፥ በየልብሳችን ላይ የተጠለፈውንና በየእጃችን የያዝነውን መስቀል፥ እንዲሁም፡ የሰላማችንን የኢየሱስ መሲሕን፡ በእንጨት ላይ ተሰቅሎ፡ እስከሞት ያደረሰውን መከራ የሚያስታውሰን በዓል ነው፡፡

# ደመራ::

በመስቀል በዓል ዋዜማ: "ደመራ" የሚባለው የበዓሉ መክፈቻ: በደመቀ ዝግጅትና ሥርዓት ተካኺዶ ይከናወናል:: ይኸውም፡- በየሰበካው ቤተ ክርስቲያን ቅጥር ውጭ ባለው አደባባይ (ማርገጃ) ላይ: የደመራው ቋሚ ተሸካሚ ይኾን ዘንድ: በጫፉ ቅርንጫፍ: የዐደይ አበባ ጉንጉን የታሠረበትን: ወፍራም እርጥብ አጠና: በመጀመሪያ አምጥተው: እንደምሰሶ በመትከል፣ ከዚያ: ከየሠፈሩ የተመረጠ ኹነኛ ወይም ቀንደኛ ሰው÷ ደግሞም: ዓቅሙ የሚፈቅድለትና ለማበርከት የሚፈልግ ማንኛውም ግለሰብ ጭምር: እርጥብና ለጋ የኾነውን የባሕር ዛፍ አጠና: በምሰሶው ዓይነት እያዘጋጀና እያመጣ: በቋሚው ላይ ይደምርበታል፤ "ደመራ" የተባለው: ለዚህ ነው::

የሠርክ ጊዜ ሲደርስ÷ ይኸውም: ከቀትር በኋላ: ወደዓሥራ አንድ ሰዓት ግድም: ሕዝቡ ተሰብስቦና ያማረ መጎናጸፊያን ያገለደመ ደመራውን ከብቦ እንደቆመ: ልብሰ ተክህኖ በለበሱ ልኡካን መሪነት: ካህናቱና መዘምራኑ: መስቀልን በሚመለከት: ለበዓሉ የተመደበውን ሥርዓተ ጸሎት ያደርሳሉ:: በዚህ መሠረት: <u>ካህኑ:</u> " **...መስቀለ መሲሕስ: ቤዛነ÷ ወኃይልነ፤ አግዐዘ ጻድቃነ÷ ወኃጥኣነ: እምግብርናተ ሰይጣን ጸላዒነ፤ ነሢአ ሥልጣነ እምእግዚአብሔር አምላክነ::** የመሲሕ መስቀልማ: ከእግዚአብሔር አምላካችን: ሥልጣንን አግኝቶ: ጻድቃንንና ኃጥኣንን: ከጠላታችን: ከሰይጣን የባርነት አገዛዝ: ነጻ ያወጣ: ቤዛችንና ኃይላችን ነው!" <u>ረዳት ካህኑም</u> "**ሰብሑ፡ ቅድመ መስቀል! ኵልክሙ መሃይምናን: እንዘ ትእኅዝዎ በየማን፤ ወትክህድዎ ለሰይጣን፤ እስመ ተቀደሰ: በደመ መለኮት መድኅን::** ምእመናን ኹላችሁ! በቀኝ እጃችሁ እያማተባችሁና ሰይጣንን እየካዳችሁ: ሰላምን፡ በድሉ ባስገኘልን የመለኮት ደም: በተቀደሰው: በመሲሕ መስቀል ፊት አመስግኑ!" <u>ሕዝቡም:</u> "**ክቡር አንተ፡ ንጉሠ ዕፀዋት መስቀል! አንተ÷ የዛፎች ኹሉ ንጉሥ የኾንህ መስቀል** ሆይ! አዎን! ክቡር ነህ!" የሚለውን: የመስቀል ውዳሴ: በዜማ እየተቀባበሉ ያመሰግናሉ::

ጸሎቱ ሲያበቃ: "**መስቀል አብርሃ! በከዋክብት: አሠርገወ ሰማየ! እምኵሉሰ: ፀሓየ አርኣየ!** እግዚአብሔር፡ ከኹሉም ይልቅ: ደምቆ በሚታየው: በፀሓይ÷ ደግሞም: በከዋክብት: ሰማዩን እንዳስጌጠ: እነሆ: መስቀሉ: በዓለሙ ኹሉ አበራ!" የሚለውን ዜማ እየዘመሩ÷ ቀጥሎም: ሕዝቡ: "**እዮሃ አበባዬ! መስከረም ጠባዬ?!**" የሚለውን: የሆታ መዝሙር: በመቀባበል እያሰማ: ደመራውን: ሦስት ጊዜ ይዞራሉ:: በዚህ: የሥርዓተ ጸሎቱ ፍጻሜ ይኾንና: ወንዱ: የችቦ መብራቱን ሊያበራ: ወደየቤቱ ይኼዳል::

ወደእየቤቱ የተመለሰው ሰው: ችቦውን ከየምድጃው እሳት ለኩሶ ሲወጣ: ትርጉሙ፡ ከላይ፡ ቀደም ብሎ የተነበበውን: "**መስቀል ኃይልነ! መስቀል ጽንዕነ! መስቀል ቤዛነ! መስቀል ሰላምነ! አይሁድ ክህዱ! ንሕነሰ አመንነ! ወእለ አመንነ፡ በኃይለ መስቀሉ ሞእነ!** መስቀል: ኃይላችን ነው! መስቀል: ጽናታችን ነው! መስቀል: ቤዛችን ነው! መስቀል: ሰላማችን ነው! አይሁድ: ካዱት! እኛ ግን፡ አመንንበት! ያመንንበት እኛም: በመስቀሉ ኃይል፡ ክፉዉን አሸነፍን!" " እያለ: በየደጃፉ መድረክ ላይ ከተረኰሰ በኋላ: የችቦ ፋናውን እያንቦገቦገ አምጥቶ: ከተቀጣጠለው የደመራው እሳት ላይ እያነጣጠረ: ከሩቅ በመወርወር ይጥለዋል:: የደመራው እሳት ተያይዞ: ነበልባሉ እየተንቀለቀለ÷ ብርሃኑ: የአካባቢውን ጨለማ÷ ሙቀቱም: የምሽቱን ብርድ ሲያስወግድለት: ሕዝቡ: በመንፈሳዊ ተመስጦ እየዘመረና በሃይማኖታዊ ስሜት እየጨፈረ: የደመራው: የመኻል ምሰሶ ኾኖ የቆመው እንጨት: ነድዶ እስኪወድቅ ድረስ ይቆያል::

ከዚህ በኋላ፡ ደመራው በገጠር የተደረገ ከኾነ፡ እያንዳንዱ አምራች፡ ከጓሮው፡ ወይም ከእርሻው መሬት፡ ፈጣሪው ባርኮ የሰጠው፡ የድካሙ ፍሬ የኾነ ሰብል ቢኖረው፡ ከዚያ ላይ፡ እሸቱን፡ እንደምስጋና መባእ አድርጎ ያቀርብና፡ ያን፡ እሸቱን፡ በደመራው ፍሕም እየጠበሰ፡ እዚያ ካለው፡ ከቀረው ሰው ጋር ተሳትፎ ሲጨርስ፡ ወደየቤቱ ይመለሳል። ደመራው ግን፡ እንዲሁ፡ ሲነድድ ያድራል።

በማግሥቱ ማለዳም፡ እያንዳንዱ ሰው፡ ወንዱም፥ ሴቱም፡ ወደነደደው የደመራ አመድ እየመጣ፥ ከአመዱም፡ በጣቱ እየጠቀሰ፡ የመስቀል ምልክትን፡ በየግን ባሩ ላይ ካተመ በኋላ፡ ለምስጋናው ሥርዓተ-ቅዳሴ ጸሎት፡ ወደቤተ ክርስቲያኑ ይገባል።

## የእውነተኛው መስቀል ፍለጋ እና ፍሬያማ ውጤቱ።

"ነገር ከሥሩ፥ ውኃ ከጥሩ!" እንዲሉ፡ ስለመስቀል ታሪክ ሲወሳ፡ አዳምንና ሔዋንን በሚመለከት፡ ከዚህ የሚከተሉት ቍም ነገሮች ይጠቀሳሉ፤ ይኸውም፡ እኒህ፡ ኹለት የመጀመሪያ ሰዎች፦

፩ኛ፦ የአምላክ ልጆች ኾነው፡ በቅንነት እንዲመሩበትና ለዘለዓለም ሕያዋን ኾነው፡ በገነት ተድላ እንዲኖሩበት፡ ከፈጣሪያቸው ከተሰጣቸው የእውነት ቃልና ከተጎናጸፉት መልካም ሕይወት ይልቅ፡ ዲያብሎስ ከተባለው የሓሰት አበጋዝ የቀረበላቸውን የጥፋት ምክር፡ በራሳቸው ምርጫ ተቀብለው፡ በክፋት ዓለም መኖርን መምረጣቸው፥

፪ኛ፦ ቆይተው ግን፡ ከዚህ የኃጢአት ምግባራቸው ፍጹም ተጸጽተው፡ ንስሓ በመግባት፡ የፈጣሪያቸውን ምሕረት መጠየቃቸው፥ እግዚአብሔርም፡ ሊነገር በማይቻል ቸርነቱ፡ ኃጢአታቸውን ይቅር ማለቱ፥

፫ኛ፦ እግዚአብሔር፡ የዚህ ይቅርታው መገለጫ በኾነው፡ በእግዝእተብሔር እም፡ ድንግል ማርያም መድኃኒትነት፥ በአንድ ልጁ፡ በኢየሱስ መሲሕም ቤዛነት፡ እነርሱኑ፡ አዳምንና ሔዋንን፥ የእነርሱን ፈለግ የተከተልን፡ እኛን፡ ዘሮቻቸውንም፡ በፈቃዳችን ካመጣነው፡ ከዚያ የፍዳ አገዛዝ፥ የኃጢአት ቀንበርና የሞት ዕዳ፡ ካዳነን በኋላ፡ ጥንቱኑ አዘጋጅቶልን ወደነበረው፡ ወደዘለዓለም መንግሥቱ ሕይወት የመለሰን መኾኑ፡ ከኹሉ በፊት፡ መነሻና መሠረት ኾኖ መነገር አለበት።

ይህም ኹሉ ሊኾን የቻለው፡ በቀላል አልነበረም፤ እግዝእተብሔር እም፡ አስቀድማ፡ ጽላተ-ኪዳንን በመዋሓድና በታቦተ ጽዮን በማደር፥ ኋላም፡ በቅድስት ድንግል ማርያም ሰውነት በመገለጥ፡ አማናዊዉንና ዘለዓለማዊዉን መድኃኒትነት በማስገኘቷ ሲኾን፤ ልጇ ወዳጇ እግዚአብሔር ወልድ፡ ኢየሱስ መሲሕ፡ እርሷ፡ መለኮታዊት እናቱ፡ እግዝእተብሔር እም፡ ከተዋሓደቻት፡ ከቅድስት ድንግል ማርያም፡ በፍጹም ሰውነት ተወልዶ፥ ያለኃጢኣት፡ እውነተኛውን ሰብአዊ ሥርዓት በመኖር፡ ለፍጥረቱ በጎ አርአያ ኾኖ፥ የእግዚአብሔርን መንግሥት ኢትዮጵያን ምንነት፡ በትምህርት ገልጦ፤ አምላክነቱንም፡ በተአምራት አሳይቶ፥ ልዩ ልዩ ፈተናዎችን አሸንፎ፤ መከራዎችንም ተቀብሎ፥ በመስቀል ላይ ራቁቱን ተሰቅሎ፥ ከቅድስት ድንግል ማርያም የነሣውን፡ ቅዱስ ሥጋውን ቆራርሶና ክቡር ደሙን አፍስሶ፥ ሙቶና ተቀብሮ፥ በመጨረሻ፡ በትንሣኤው፡ ያን፡ ጠንቀኛ ጠላታቸውን ዲያብሎስን፡ ድል በመንሣት ነው።

ከዚህ ጋር በማያያዝ: "**ዘይፈቅድ ይትልወኒ፡ ይጽልአ ለነፍሱ! ወያጥብዕ! ወይንሣእ መስቀለ ሞቱ! ወይትልወኒ! ወዘይፈቅድ፡ ያድኅና ለነፍሱ፡ ለይግድፋ! ወዘሰ ገደፋ ለነፍሱ በእንቲአየ፡ ይረክባ!** እኔን መከተል የሚወድ ቢኖር: ራሱን ይካድ! ለሞት እስከሚያበቃ የሚደርስ፡ የመስቀል መከራንም ለመቀበል፡ በፍጹም ቆራጥነት ጨክኖ ይከተለኝ! ነፍሱን ሊያድን የሚወድ ኹሉ: ያጠፋታል፤ ስለእኔ ግን: ነፍሱን የሚያጠፋ ኹሉ ያገኛታል!" የሚለው: የመስቀሉ ጌታ: የኢየሱስ መሲሕ ቃል እና የእርሱ ተከታይ ሓዋርያ: ቅዱስ ጳውሎስ: በመንፈስ ቅዱስ ተመልቶ: "**እስመ ነገረ-መስቀሉሰ፡ ዕበድ ውእቱ፡ በኀበ ሕጉላን። ወበኀቤነሰ፡ ለእለ ድኅነ፡ ኃይለ-እግዚአብሔር ውእቱ።** የመስቀሉ ቃል: በሚጠፉት ዘንድ፡ ሞኝነት ነው፤ በእኛ፡ በዳንነው ዘንድ ግን: የእግዚአብሔር ኃይል ነው!" በሚል የመክፈቻ አርእስት: ስለመስቀል ምስጢር የሰጠው የትርጓሜ ሓተታ: ዐብሮ ሊታወስና ሊነገር ይገባል:: (ማቴ. ፲፮÷ ፳፬-፳፭፤ ፩ኛ ቆሮ. ፩÷ ፲፰-፴፩::)

የትርጓሜው ሓተታ እንዲህ ነው:- የአይሁድ ሊቃናት: ከካህናቱና ከሕዝቡ ጋር: በሰይጣናዊ ቅንዓት ተነሣሥተው: በስቅላት ያስገደሉት ኢየሱስ መሲሕ: ሥጋው ከተቀበረም በኋላ እንኳ: ቅንዓታቸው ሊበርድ÷ ጭካኔያቸውም ሊረግብ አልቻለም፤ ያ: ያሠቃዩት: እርሱ፡ እግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ መሲሕ: ስለፍጥረቱ ቤዛነት: የመጨረሻው የፋሲካ በግ ኾኖ የተሠዋበት: ይህን የመሰለው መለኮታዊ ፍቅር ተፈጽሞ: ምስጢሩ የተከሠተበትን እንጨት እንኳ: በርኅራኄያቸው ትተው ሊያልፉት አልፈለጉም:: "ደቀ መዛሙርቱ: ሥጋውን ሠርቀው እንዳይወስዱት" በሚል ምክንያት: መቃብሩን እንዲያስጠብቅላቸው: ወደጲላጦስ ኼደው በመማፀንና እርሱም ፈቃዳቸውን በመፈጸም: በድኑን ሳይቀር እንዳልተዉት ኹሉ: አኹንም: በመስቀሉ ላይ የፈጸሙት ግፍ: ከዚያ ያላነሰ÷ እንዲያውም የባሰና ወደር የማይገኝለት ኾኖ እንዲቀጥል ማድረጋቸውን፡ እነሆ እንመለከታለን::

ይኸውም: መስቀሉ: ደብዛው ሳይቀር: ጨርሶ እንዲጠፋ ያደረጉበት: መሠሪ ዕቅዳቸውና ክፉ ድርጊታቸው ነው:: በዚህ ዕቅዳቸው መሠረት: ማንም ሰው÷ የራሳቸው የኾኑት ወገኖቻቸው እንኳ ሳይቀሩ: ሊጠረጥሩ በማይችሉበት ኹኔታና ሥፍራ: መስቀሉን: በድብቅ አስወስደው ቀበሩት፤ ያም ሥፍራ: ለከተማው የቆሻሻ መጣያ የተመደበው ቦታ ነበር::

በዚህ ድርጊታቸው: ሦስት እኩይ ዓላማዎቻቸውን የፈጸሙ መስሏቸው ነበር:: ከእነዚህ ዓላማዎቻቸው መካከል:-

የመጀመሪያው: የሰማይና የምድር ፈጣሪና አምላክ የኾነው ኢየሱስ መሲሕ፡ ከእግዚአብሔር እም፡ ድንግል ማርያም የነሣው፡ ቅዱስ ሥጋው የተቀረሰበትንና ክቡር ደሙ የፈሰሰበትን ምሥዋዕ (መሠዊያ) መስቀሉን ማርከስ ሲኾን÷

ኹለተኛው ደግሞ:- ሕዝቡ ኹሉ: የቤቱንና የከተማውን ጥራጊና ቁሻሻ: በየቀኑ ያለማቋረጥ በማፍሰስና በመጣል: የዕፀ መስቀሉን መቀበር፡ ማንም ሊያውቅ እንዳይችል÷ ምናልባት ቢታወቅ እንኳ: ምንጊዜም ተቆፍሮ እንዳይገኝና እንዳይወጣ ማድረግ ነው፤

ሦስተኛውም፡- መስቀሉን እንዲህ አድርገው በሚቀብሩበት ጊዜ፡ የክፋታቸው መጠን ምን ያህል የጸና መኾኑን የሚያመለክተው፡ ሌላው ገጽታ ይታያል፤ ይኸውም፡ ዕፀ መስቀሉ፡ ምናልባት ተቆፍሮ የተገኘ እንደኾነ፡ በመለኮታዊትና በትስብእታዊት እናቱ እግዝእተብሔር እም ድንግል ማርያም መድኃኒትነት፡ ለአንዴና ለዘለዓለም ፈጽሞ ለዳነው ፍጥረተ-ዓለም፡ እርሱም፡ ልጇ ወዳጇ እግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ መሲሕ፡ በበኩሉ፡ በመለኮታዊው እና በትስብእታዊው ልጅነቱ ጀግንነት፡ በዝንተ-ዓለም ተፃራሪው፡ በዲያብሎስ ላይ፡ የመጨረሻውን ድል በማግኘት፡ **እውነተኛዋንና ፍጹሟን ሰላም፡ ለአንዴና ለዘለዓለም ያቀዳጀበት፡** እውነተኛው መስቀል፡ የትኛው እንደኾነ ተለይቶ እንዳይታወቅ ለማደናገር ሲሉ፡ በቀኝና በግራ የተሰቀሉትን ወንበዴዎች ብቻ ሳይኾን፡ ሌሎች ወንጀለኞች ጭምር የተሰቀሉበትን እንጨት፡ ከፈጣሪያችን ከኢየሱስ መሲሕ መስቀል ጋር ደበላልቀው እንዲቀበር ማድረጋቸው ነው፡፡

# ዕሌኒ ንግሥት እና ልጇ፡ ንጉሥ ቈስጠንጢኖስ፡፡

ነቢዩ፡ "ጊዜ፡ ገቢር ለእግዚአብሔር" እንዳለው፡ እግዚአብሔር፡ ፈቃዱን የሚፈጽምበት፥ ሥራውንም የሚሠራበት ጊዜ ስላለው፡ የዚህ፡ የመስቀሉ ክብርና ኃይል የሚገለጽበት ቀኑ፡ እነሆ ደረሰ፡፡ ያም ቀን፡ ምድረ ከነዓንን በማጠቃለል፡ በማእከላዊው ባሕር አካባቢ ያለውንና በዘመኑ፡ "ሥጋዊው ሥልጣኔ ዳብሮበታል" የተባለውን ዓለም፡ በቄሣርነት የገዛው ቆስጠንጢኖስ፡ በ፫፻፳፭ ዓ. ም. በእናቱ በንግሥት ዕሌኒ አማካይነት፡ የክርስትናን እምነት ለመቀበል፡ ራሱን ያበቃበት ጊዜ ነበር፡፡ በዚያው ዓመት፡ ሃይማኖታዊት የኾነችው፡ ይህችው ንግሥት እናቱ፡ ኢየሱስ መሲሕ ተወልዶ፥ አድጎና ኖሮ፥ ተሰቅሎና ሞቶ፥ ተነሥቶና ዐርጎ፥ ተልእኮውን በማከናወን፡ ዘለዓለማዊ የምሕረት ጸጋውን፡ ለሰው ልጆች፡ በቃል ኪዳን የሰጠባቸውን ቅዱሳት መካናት ትሳለም ዘንድ፡ ልቦናዋ ተነሣሥቶ፡ ወደኢየሩሳሌም እንድትጓዝ ኾነ፡፡

ዕሌኒ ንግሥት፡ ኢየሩሳሌም ገብታ፡ ቅዱሳት መካናትን እየተዘዋወረች ከጎበኘች በኋላ፡ ስለኢየሱስ መሲሕ ቅዱስ መስቀል በጠየቀች ጊዜ፡ መስቀሉ የተቀበረበት ቦታ ባለመታወቁ፡ እስከዚያን ቀን ድረስ፡ የመስቀሉ ነገር የተሠወረ ምስጢር ኾኖ እንደሚገኝ ተነገራት፡፡ በዚያን ጊዜ፡ መስቀሉን በሚመለከት፡ በመንፈሳዊ የፍቅርና የቅንዓት እሳት በነደደ ልቦናዋ፡ የኢየሱስ መሲሕን፡ ሕማማቱንና የተናገራቸውን ቃላት በማዘከር፡ ወደፈጣሪዋ፡ የእንባ ጸሎት አቀረበች፤ በእርሷ በኩል፡ ምን ማድረግ እንደሚገባት ያመለክቷትም ዘንድ፡ ወደቤተ ክርስቲያን መሪዎችና አገልጋዮች ካህናት፥ በየቦታው ወደዘጉ ባሕታውያን ሳይቀር እየላከች አስጠየቀች፡፡

ከእነርሱም ያገኘችው መልስ፡ ካህናትና ምእመናን፡ በቤተ ክርስቲያን ተሰባስበውና በምሕላ ተጠምደው፥ የዘጉትና የበቁትም፡ በየበዓታቸው ተጠናክረው፥ ኹሉም፡ ባያለበት ጾምና ጸሎት በማድረስ፡ መንፈስ ቅዱስ፡ ምስጢሩን እንዲፈታው መጠየቅ መኾኑን የሚያመለክት ነበረ፡፡ እርሷም፡ ይህ የተባለው መንፈሳዊ ምግባር፡ ራሷ ጭምር በተካፈለችበት፡ እንዲካኼድ አድርጋ፡ የእግዚአብሔር ጽድቅ የተገለጸበትንና መልካም የምሥራች ፍሬ የኾነውን፡ ከዚህ የሚከተለውን መመሪያ ለማግኘት በቃች፡፡

ይህም፡ "ለመሥዋዕት እንደሚደረግ፡ እንጨት ተረብርቦ እንዲነድና በዚያ ላይ፡ በሱባዔና በምሕላ የተጸለየበት ዕጣን ተጨምሮ፡ ጢሰ ቅታሬው፡ ወደሰማይ ከወጣ በኋላ፡ ወደምድር ተወርውሮ የሚተከልበት፡ ያ ቦታ፡ ኢየሱስ መሲሕ የተሰቀለበት፡ እውነተኛው ዕፀ መስቀል የተቀበረበት ሥፍራ መኾኑን አረጋግጦ የሚያሳይ ምልክት ይኹናችሁ!" የሚል ነበር፡፡

በዚህ መሠረት፡ መንፈሳዊቷ ንግሥት፡ ይህንኑ መመሪያ በመከተል፡ የታዘዘው ሥርዓት እንዲፈጸም በማድረጓ፡ በሃይማኖታዊ ተስፋና ቅንዓት የተጠበቀው ውጤት ታየ! አዎን! ከሚነድደው እሳት ተነሥቶ፡ ወደሰማይ የወጣው የዕጣኑ ጢሰ ቅታሬ፡ ወደምድር ተመልሶ፡ ከተራራማነት መጠን ደርሶ በነበረ፡ በአንድ ጉብታ ላይ እንደጦር ተወርውሮ ተተከለ! ይህ ተአምር የታየበት ዕለት፡ መስከረም ፲፯ ቀን፥ ፫፻፳፯ ዓ.ም. ነበር፡፡ በዚያ ተራራ ላይ የሚደረገው ቁፋሮ፡ በዚሁ ቀን ተጀምሮ፡ ወደጥልቅ እየወረደ ሲቀጥል ከቆየ በኋላ፡ በመጋቢት ፲ ቀን፡ መስቀሎች ተከማችተው ከሚገኙበት ዐዘቅት ተደረሰ!

በዚያ ዐዘቅት ውስጥ ከነበሩት፥ ሳይበሰብሱና መሬት ሳይበላቸው ከተረፉት ጥቂት መስቀሎች መካከል፡ ለካ፡ ሰላማችን ኢየሱስ መሲሕ፡ ለፍጥረቱ ቤዛ ኾኖ፡ ከድንግል ማርያም የነሣው ቅዱስ ሥጋው የተቆረሰበት፥ ክቡር ደሙም የፈሰሰበት፡ እውነተኛው ዕፀ መስቀል፡ ዐብሮ ይገኝ ኖርዋል! ነገር ግን፡ የትኛው እንደኾነ ለይቶ ለማወቅ እጅግ አዳጋች ኾነ! ይኹን እንጂ፡ ይህን ችግር ለመፍታት፡ ረዥም ጊዜን አልወሰደም፤ ብዙ ድካምንም አልጠየቀም፤ አማናዊው ቅዱስ መስቀል፡ የተለያዩ ተአምራትን በመፈጸም፡ ራሱን ከሌሎቹ ለይቶ በማቅረብ፡ ማንነቱን፡ በታላቅ ኃይል ገልጦ ሊያሳይ ችሏል፡፡

ዛሬም፡ እኛ ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት፡ "ደመራ" እና "መስቀል" እያልን፡ በየዓመቱ የምናከብረው በዓል፡ መነሻና ዓላማው፡ ይህ ሲኾን፥ መታሰቢያነቱም፡ ለዚህ ነው፡፡

## የንግሥት ዕሌኒ፡ እውነተኛነትና ባለውለተኛነት፡፡

የንግሥት ዕሌኒ፡ እውነተኛ ክርስቲያንነትና ጽኑ ሃይማኖታዊትነት፥ ለክርስቲያኖች ኹሉ፡ በተለይም፡ ለእኛ፡ ለኢትዮጵያ ልጆች፡ ባለውለታችን መኾኗን፡ ራሱ፡ ምግባርዋ ይመሰክራል፤ ይኸውም፡ እንዲህ ነው፡- ይህችው ንግሥት ዕሌኒ፡ በኢየሩሳሌም ባሳለፈችው የጥቂት ዓመታት ቆይታዋ፡ የመጣችበትን፡ ቅዱሳት መካናትን የመሳለም ዓላማዋንና ታላቁ ትሩፋትዋ የኾነውን፡ የመሲሕ ኢየሱስን ቅዱስ መስቀል አስቆፍሮ የማውጣት ተልእኮዋን ማከናወን ብቻ አልነበረም፤ ጎልጎታ በተባለው እና መስቀሉ በተገኘበት ቦታ ላይ፡ የኢየሩሳሌምን ቤተ ክርስቲያን፡ በአምስት ዓመታት አሠርታ ያስጨረሰችው፡ በዚሁ ጊዜ ነበር፡፡ አሠርታም እንደጨረሰች፡ ምዕራቡን፡ ለሮም (ለግሪኮች)፥ ምሥራቁን፡ ለሓበሾች (ለኢትዮጵያውያን) ሰጠች፡፡ ይህም የኾነው፡ ያለምክንያት አልነበረም፡፡

ያም ምክንያት እንደሚከተለው ነው፡- የኢትዮጵያ ልጆች፡ ጥንት፡ ኢየሩሳሌምን ከቈረቈረው፡ ከዘር ግንዳቸው፡ ከመልከ ጼዴቅ ጀምሮ፡ እስከኢትዮጵያዊት ንግሥታቸው፡ ማክዳ፥ ከዚያም፡ ታላቁ እስክንድር እስከተነሣበት ዘመን ድረስ፡ ከትውልድ ወደትውልድ እየተላለፉ፡ በውርስ የደረሷቸው፡ በኢየሩሳሌም ያሉት የዐፅመ ርስት ቦታዎችና ንብረቶች፡ በይዞታቸው ሥር ተጠብቀው ይኖሩ ነበር።

በእስክንድር ዘመንና ከእርሱ በኋላ ግን፡ በእርሱ ሥልጣን ከተተኩት፡ ከአራቱ የጦር አዝማቾቹ አንዱ ወራሽ የነበረው፡ "፬ኛው አንጥያኮስ ኤጺፋንዮስ" የተባለው አረማዊ፡ ከክርስቶስ ልደት በፊት፡ በ፩፻፷፰ ዓመት፡ ኢየሩሳሌም ገብቶ፡ ታላቅ ዕልቂትንና ብርቱ ጥፋትን አደረሰ፤ ከዚህ በኋላ፡ ከክርስቶስ ልደት በፊት፡ በ፩፻፷፯ ዓመት፡ መቃብያን፡ በእርሱ አገዛዝ ላይ በዓመፅ ተነሥተው፡ እስኪያስወግዱት ድረስ፡ እነዚህ፡ የኢትዮጵያ ይዞታዎች፡ በዚያ ከሚገኙት ቅዱሳት መካናት መካከል ጠፍ ኾነው ቆይተው ስለነበረ ነው።

ይህን እውነታ፡ ከዚህ ቀጥሎ ያለው ማስረጃ ያረጋግጠዋል። ስሙ፡ ቀደም ብሎ የተጠቀሰው ቆስጠንጢኖስ፡ ከክርስቶስ ልደት በኋላ፡ በ፫፻፳፮ ዓ.ም. ግድም፡ በሮም (በቍስጥንጥንያ) ነግሦ፡ እናቱን፡ ንግሥት ዕሌኒን፡ ወደኢየሩሳሌም ልኳት፡ እርሷም፡ ቀደም ብሎ እንደተገለጸው፡ የመጣችበትን የተቀደሰ ዓላማዋን÷ ታላቁን ተልእኮዋን እና የሕንፃ ቤተ ክርስቲያን ሥራዋን አከናውና እንደፈጸመች ወዲያው፡ "በጊዜው ለነበሩት ክርስቲያኖች፡ ቦታ በምትሰጥበት ጊዜ፡ አብርሃ ወአጽብሓ የተባሉት፡ የዘመኑ የኢትዮጵያ ወንድማማች ነገሥታት፡ ወደቆስጠንጢኖስ እና ወደእናቱ፡ ንግሥት ዕሌኒ፡ እንዲህ ሲሉ ላኩ፤-

«‹በኢየሩሳሌም፡ 'ገዳመ ንጉሥ' [ኋላ በእስላሞች ጊዜ 'ዴር ሡልጣን'] የተባለ አንድ ቦታ÷ የአሕዛብ ነገሥታት፡ ኢየሩሳሌምን እስኪያጠፏት ድረስ፡ ከጥንት ጀምሮ በኢትዮጵያ ነገሥታት እጅ እንደነበረ፡ ከታሪክ አይታችሁ÷ ከሽማግሌም ጠይቃችሁ፡ እንድትመልሱልን እንለምናችኋለን። ከእናንተ በፊት የነገሡ አሕዛብ፡ እግዚአብሔርን የማይፈሩ÷ ሰውን የማያፍሩ ነበሩና፡ እግዚአብሔር፡ ለሕዝቡ፡ አማኝ ንጉሥ እስኪያነግሥ ድረስ፡ ዝም አልን። አኹን ግን፡ "እግዚአብሔርን የሚፈራ÷ ለሕዝበ ክርስቲያን የሚራራ÷ ርስት የሚተክል እንጂ የማይነቅል፡ 'ቆስጠንጢኖስ' የሚባል ደግ ንጉሥ ነገሠ!" የሚል ዜና ብንሰማ፡ እጅግ በጣም ደስ አለን።

«‹ስለዚህ፡ አንቺም፡ ክብርት ንግሥት ሆይ÷ ደግ ክርስቲያን መኾንሽን እና ጌታችንን፡ ኢየሱስ ክርስቶስን ማፍቀርሽን ሰምተናልና፡ 'የእናት ልመና፡ ፊት አያስመልስ፤ አንገት አያስቀልስ!' እንደሚባለው፡ ለንጉሡ ልጅሽ ነግረሽ፡ ርስታችንን አስመልሽልን!› ብለው ወደዕሌኒ ንግሥት ላኩ።

«እርሷም፡ ይህንኑ፡ ወደልጇ፡ ወደንጉሥ ቆስጠንጢኖስ ልካ አሳወቀችው። ንጉሥ ቆስጠንጢኖስም፡ የኢትዮጵያ ነገሥታት፡ አብርሃ ወአጽብሓ የላኩትን ቃል አይቶ÷ ከታሪክም ተመልክቶ÷ ከሽማግሌዎችም ጠይቆና ተረድቶ÷ የእናቱንም ምክር ሰምቶ፡ በደስታ፡ "እሺ!" አለ። ይኸው፡ በኢየሩሳሌም ቅዱሳት መካናት፡ የኢትዮጵያውያንና የኢትዮጵያውያት፡ ርስታቸው የኾነው ቦታ፡ በንጉሥ ቆስጠንጢኖስ እና በእናቱ በንግሥት ዕሌኒ ትእዛዝ፡ እንደቀድሞው፡ ለኢትዮጵያውያንና ለኢትዮጵያውያት እንዲመለስ ተደረገ።

«ከዚያ በኋላ፡ የኢትዮጵያ መናንያን [መነኮሳት/ዪያት]፡ መኖሪያ ቤት ሠርተው ባገኙት ቤተ ጸሎት፡ እያገለገሉ ቆዩ። ይህም የኾነው፡ ከ፫፻፳፰ ዓ.ም. ጀምሮ ነው። እስከዘመነ ተንባላትም ድረስ፡ (ማለትም፡ እስላሞች ሥልጣን እስኪያዙበት ጊዜ ድረስ፡) ከሦስት መቶ ዓመታት ለሚበልጥ ጊዜ፡ በሰላምና በዕረፍት ኖሩ።»(ደብረ ሥልጣን በኢየሩሳሌም÷ *በኢየሩሳሌም የኢትዮጵያ ገዳማት ታሪክ ማስታወሻ*፤ በአባ ማቴዎስ፡ ሊቀ ካህናት (ሊቀ ጳጳሳት)፤ በ፲፱፻፹፰ ዓ. ም. የታተመ÷ ገጽ ፮-፯÷ ፲፮- ፳፬።)

# የመስቀሉ ዝክረ-ነገር እና ኢትዮጵያዊው አፄ ዳዊት፡፡

የመስቀሉ ነገር፡ በዚህ ኹኔታ፡ ለአንድ ሺ ዓመታት ያህል ተጠብቆ ሲኖር ሣለ፡ በመካከለኛው ዘመን ግድም፡ ከኢትዮጵያ ጋር በተያያዘ መልኩ፡ በመለኮታዊ ሥራ፡ እንደገና ሊነሣሣ የቻለበት ምክንያት ተፈጠረ፤ እርሱንም፡ እዚህ ላይ ወደማዘከሩ እንገባለን፡፡

በ፲፫፻፹፫ ዓ. ም. በኢትዮጵያ ዙፋን ላይ ተቀምጦ፡ ለሠላሳ ዓመታት ያህል፡ በዘውድ ሥልጣን የቆየው፡ ዳግማዊ አፄ ዳዊት፡ በሃያ አምስተኛው የሥልጣን ዘመኑ፡ "ናዝር" የተባለ የእስላም ንጉሥ፡ በኢየሩሳሌምና በግብፅ የሚኖሩትን ክርስቲያኖች ኹሉ አስጨነቀ፡፡ በዚያ መከራ ምክንያት፡ አባ ዮሓንስ የሚባለው፡ የኢየሩሳሌም ሊቀ ካህናት (ኤጲስ ቆጶስ)፡ "ስለእግዚአብሔር ብለህ እርዳን! የክርስቲያን ስም ጠፋ! በእስላምም እጅ ተጨነቅን!" ሲል፡ ወደኢትዮጵያው መሪ፡ ወደአፄ ዳዊት፡ መልእክትን ላከ፡፡

ይህን መልእክት የተቀበለው አፄ ዳዊት፡ በክርስቲያኖቹ ላይ የደረሰውን መከራ፡ ከመልእክተኞቹ በተረዳ ጊዜ፡ እጅግ አዘነ፡፡

ወዲያውም፡ "ምታ ነጋሪት! ክተት ሠራዊት!" ብሎ ወደምድረ ግብፅ ለመዝመት፥ በግብፅና በኢየሩሳሌም፡ በመከራ የሚሠቃዩትንም ክርስቲያኖች፡ ከእስላሞች እጅ ለማዳን ተነሣ፡፡ ቁርጥ ውሳኔው በዚህ ብቻ ሳያበቃ፡ "የምሥርን [የግብፅን] አገር የሚያጠጣውን የዓባይን ውኃ ገድቤ፡ ወደውቅያኖስ እንዲፈስስ አደርገዋለሁ!" ብሎ ላከ፡፡

ምሥሮች (ግብፃውያን)፡ ያለዓባይ፡ ሌላ ውኃ የላቸውምና፡ እስላሞች፡ ይህን ቃል ሲሰሙ፡ ከንጉሣቸው ጋራ ተጨነቁ፡፡ ስለዚህም ነገር፡ በኢየሩሳሌምና በግብፅ ከሚኖሩት ክርስቲያኖች ጋር በግድ ታረቁ፡፡ አፄ ዳዊትም፡ ደስ ብሎት ወደአገሩ ተመለሰ፡፡ (ደብረ ሥልጣን በኢየሩሳሌም፥ *በኢየሩሳሌም የኢትዮጵያ ገዳማት ታሪክ ማስታወሻ*፤ በአባ ማቴዎስ፡ ሊቀ ካህናት (ሊቀ ጳጳሳት)፤ በ፲፱፻፹፰ ዓ. ም. የታተመ፥ ገጽ ፮-፯፥ ፲፮- ፷፬፡፡)

አፄ ዳዊት፡ ይህንና የመሰለውን፡ ታላቅ የመታደግ ሥራ፡ በእግዚአብሔር ፈቃድና ኃይል ስላደረገላቸው፡ ለዚህ በጎ አድራጎቱ የሚመጥን፡ መልካም ውለታ ይኾንላቸው ዘንድ፡ "ምን ዓይነት ቋሚ የመታሰቢያ ስጦታ እናድርግለት?" ብለው፡ የኢየሩሳሌሙ ሊቀ ካህናት (ኤጲስ ቆጶስ)፥ ካህናቱና ምዕመናኑ አሰቡ፤ መከሩም፡፡

በዚያ ምክራቸውም፡ የሰላማችንን የኢየሱስ መሲሕን፡ የመስቀሉን ቀኝ ግማድ (ጒራጅ)፥ ከእርሱም ጋር፡ ዮሓንስ ባለምሥራቹ (ወንጌላዊው) የሣለውን፡ የኢየሱስ መሲሕን ኵርዓተ ርእስ (በሾህ አክሊል ደም የታለለ ራሱን) ሥዕል እና ባለምሥራቹ (ወንጌላዊው) ሉቃስ የሣላትን፡ የምስለ ፍቁር ወልዳን (ድንግል ማርያም፡ ሕፃን ልጇን፡ ኢየሱስ መሲሕን እንደታቀፈች የሚያሳየውን) ሥዕል ሊልኩለት ተስማምተው ወሰኑ፡፡ ወስነውም አልቀረ፡ ይህንኑ ግማደ መስቀል፡ ከኹለቱ ሥዕሎች ጋር ላኩለት፡፡

ይህም የኾነው፡ ግማደ መስቀሉ፡ በሕያው ቅርስነቱ፡ እንደሌሎቹ፡ ማለትም፡ ታቦተ ጽዮንን እንደመሰሉት ንዋያት ቅድሳት ኹሉ፡ የልዑል አምላክ፡ የቃል ኪዳን ባላደራ በኾነችው፡ በኢትዮጵያ ምድር፡ ተጠብቆ፡ ለዘለዓለም ይኖር ዘንድ፡ የእግዚአብሔር ፈቃድ በመኾኑ ነው፡፡

የኢትዮጵያዊው ኢየሱስ መሲሕ፡ ታማኝ አገልጋይ ኾኖ የተገኘው፡ ዕድለኛው አጼ ዳዊት፡ ይህን ዜና በሰማ ጊዜ፥ ዜናውም፡ ወደቤተ ክህነቱ፥ ወደቤተ ምልክናውና ወደቤተ ሕዝቡ ጆሮ ደርሶ በተሰማ ጊዜ፡ ኹሉም፡ ታላቅ ደስታ ተሰማቸው፤ ለፈጣሪያቸውም፡ ልባዊ ምስጋናን፡ በየቤታቸውና በየቤተ ክርስቲያናቸው አቀረቡ፡፡ ግማደ መስቀሉንም ለመቀበል፡ ወደአገራቸው ሰሜናዊ ጠረፍ፡ ጉዞ ለመጀመር፡ አልዘገዩም፡፡ ከአጭር ቀናት ዝግጅት በኋላ፡ "ስናር" ወደተባለችው ግዛት ተጕዘው፡ በመስከረም ፲ ቀን፥ ፲፬፻፲፩ ዓ. ም. ግማደ መስቀሉን፡ ከእርሱም ጋር፡ ኹለቱን ሥዕሎች ተረከቡ፡፡ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ፡ ይህ ዕለት፡ “ተቀጸል ጽጌ” እና “ያጼ መስቀል” ተብሎ፡ እነሆ እስከዛሬ፡ በየዓመቱ ይከበራል፡፡

አጼ ዳዊት፥ እርሱንም የተከተሉት፡ የቤተ ምልክናው፥ የቤተ ክህነቱና የቤተ ሕዝቡ ተጠሪዎች፡ እንዲህ አድርገው ከተረከቡት ግማደ መስቀል፡ ፍጹም የኾነውን መለኮታዊ በረከት ተቀብለውና በመስቀሉ ብርሃን ተመልተው፡ ይህንኑ፡ ቅዱሱንና ሰማያዊዉን ቅርስ ይዘው፡ ወደአገራቸው የሚያደርጉትን የመልስ ጉዞ፡ በታላቅ ሥርዓት ጀመሩ፡፡

አጼው፡ በግርማ መንግሥቱ፥ ቀሳውስቱና ደባትሩ (መዘምራኑ)፡ በቅዳሴ፥ በማኅሌትና በይባቤ፥ አለቆቹና ሠራዊቱ፡ በክብር ሰልፍ፥ እንዲሁም፡ ሕዝቡ፡ ወንዱ፡ በሆታና ሴቱ፡ በእልልታ፡ ግማደ መስቀሉን ዐጅበው፡ የዘመኑ መናገሻ ከተማ ከኾነችው ከተማ አድርሰው፡ በዚያ፡ በተዘጋጀለት ማደሪያ፡ በታላቅ ማዕርግ አሳረፉት፡፡ ያችም ከተማ፡ በላይዋ ከታየው፡ የመስቀሉ ብርሃን የተነሣ፡ የዛሬ መጠሪያ ስሟን ያተረፈችውና በሸዋ፡ ተጉለት የምትገኘው፡ የዘርዓ ያዕቆብ መዲና፡ ደብረ ብርሃን ናት፡፡

ግማደ መስቀሉ፡ ለጥቂት ጊዜያት፡ በዚችው በደብረ ብርሃን ከቆየ በኋላ፡ በመጨረሻ፡ ከዚያ ተነሥቶ፡ በወሎ ምድር ወደምትገኘው፡ ወደግሼን አምባ ተዛውሮ፡ ዛሬ፡ በዚያ ይኖራል፡፡ ይህ፡ በአጼ ዘርዓ ያዕቆብ ዘመን የተፈጸመው ድርጊት የደረሰው፡ ያለምክንያት አልነበረም፡፡

ቀደም ብሎ በተነገረው፡ የትንቢት ቃል መሠረት፡ ለግማደ መስቀሉ፡ የዘለዓለም ማረፊያ እንድትኾን የተመደበችውን ቅዱስ ተራራ ለመፈለግ፡ ከአጼው ጋር፡ የቤተ ክህነቱ፥ የቤተ ምልክናውና የቤተ ሕዝቡ ተጠሪዎች፡ ግማደ መስቀሉን ይዘው፡ ከተራራ ወደተራራ ተዘዋወሩ፡፡

ኢትዮጵያን፡ በቅዱስ መስቀሉ፡ ለሦስት ዓመታት ከሦስት ወራት ካስባረኩ በኋላ፡ በመጨረሻ፡ በተፈጥሮዋ የመስቀል መልክ ባላትና እግዚአብሔር፡ ለቅዱስ መስቀሉ ማረፊያ እንድትኾን፡ አስቀድሞ ባዘጋጃት፡ በግሼን ተራራ ላይ፡ ይኸው ግማደ መስቀል ዐረፈ፡፡ ግማደ መስቀሉ፡ በዚች ተራራ ላይ ከማረፉ በፊት፡ በመላ ኢትዮጵያ፡ በአራቱ ማዕዘናት፡ እንዲዘዋወር የኾነው፡ “የኢትዮጵያ አድባራት፡ በግማደ መስቀሉ ይቀደሱ ዘንድ፡ የእግዚአብሔር ፈቃድ በመኾኑ ነው፤” ተብሎ ታምኗል፡፡ ባኹኑ ጊዜ፡ "ደብረ ከርቤ" ተብላ የምትጠራው፡ ይህች የግሼን ተራራ፡ መጀመሪያ፡ "ደብረ ነገሥት"፥ ቀጥሎ፡ "ደብረ ነጐድጓድ" ትባል እንደነበረም ይታወቃል፡፡ (ድርሳነ መስቀል፡ በሚጣቅ አማኑኤል ገዳም፡ በሰኔ፥ ፲፱፻፺፫ ዓ. ም. የታተመ፤ ገጽ ፶፪-፶፫፥ ፷፯-፸፪፡፡)

ስለመስቀሉ ነገር፡ በመጠኑም ቢኾን፡ ካብራራው፡ ከዚህ ሓተታ የተገኘውና ትምህርታዊ ጥቅም፡ በሚከተለው መልክ እናጠቃልለዋለን፡፡ ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት፡ በያመቱ፡ በመስቀል ዋዜማ፡ በመስከረም ፲፮ ቀን፡ ደመራ ደምረውና በደመራው ዙርያ ተሰባስበው፡ ተገቢውን ሥርዓተ ጸሎት ካደረሱ በኋላ፤ እሳቱን በማንደድ፡ ተከታዩን፡ መስከረም ፲፯ ቀን እያይዘው የሚያከብሩት የመስቀል በዓል፡ በግዙፍ ሲፈጸም ከምናየው ሥርዓትና ድርጊት በላይ፡ ሌላ፡ ጥልቅ ምስጢርና ዓቢይ መልእክት ያለው መታሰቢያ መኾኑ፥ ለታይታ ወይም ለልማድ ብቻ ተብሎ የሚከበር በዓል አለመኾኑም ሊታወቅ ይገባል፡፡

የበዓሉ ዋዜማ፡ "ደመራ" የተባለበት ምክንያት፡ ቀደም ብሎ እንደተገለጸው፡ እያንዳንዱ ምእመን፡ ቆርጦና መልምሎ፥ በጫፉም ቅጠል ላይ፡ የዐደይ አበባ ነዶን አስሮ፡ በመስቀል ዋዜማ ለሚነደው እሳት ያገለግል ዘንድ፡ ለዚህ ተግባር ወደተመደበው፡ ወደቤተ ክርስቲያን አደባባይ የሚያመጣውን፡ ለምለም እጠና (ለጋ ዛፍ)፡ በሌላው ላይ ስለሚደምረው ነው፡፡

ቁም ነገሩ፡ ለጊዜው ነድዶ በጥቂት ሰዓታት ውስጥ አመድ የሚኾነው የእንጨቱ ክምርና ብርሃኑ በድምቀት ተንቦግቡጎ ከታየ በኋላ፡ ወዲያው የሚጠፋው ግዙፉ የእሳት ነበልባል አይደለም፡፡ ቁም ነገሩ፡ ከመስቀሉ በዓል ርእስ መግቢያ ላይ የጠቀስንላችሁ፡ "ፈጣሪያችን ኢየሱስ መሲሕ፡ ስለመስቀሉ የተናገረው ቃልና በቅዱስ ጳውሎስ ብዕር የተጻፈው መልእክት፡ በየልባችን ሰሌዳ ላይ ተቀርጾ፡ ሕይወታችንን እየመራንበት ነወይ? ደግሞስ፡ ከዚህ መለኮታዊ ቃልና ሓዋርያዊ መልእክት የተነሣ፡ ያ፡ በንግሥት ዕሌኒ ልቦና ውስጥ ይነድድ የነበረው መንፈሳዊና ሃይማኖታዊ የቅንዓት እሳት፡ ዛሬ፡ በእኛ፡ በእያንዳንዳችን ልቦና ውስጥ እየነደደ ነወይ?" ለሚለው ጥያቄ የምንሰጠው መልስ መኾኑ ተረጋግጦ ሊታወቅና ሊታመንበት፥ በምግባርም ሊገለጥ ይገባል፡፡

አዎን! የአምላካችንና የሰላማችን የኢየሱስ መሲሕ፡ እውነተኛ መስቀሉ ተቀብሮ ሊገኝበትና የፍቅሩ ዘለዓለማዊ እሳት፡ እንደደመራው እንጨት፡ ሊነድድበት የሚገባው ቦታ፡ ሃይማኖታዊውና መንፈሳዊው ሰውነታችን መኾኑን፡ ይህ፡ የመስቀል በዓል ያስታውሰናል፡፡

## በዓለ ፍልሰተ-ዕርገታ ለማርያም ድንግል፡፡

እኛ፡ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት፡ ዘለዓለማዊት ሃይማኖታችንና አገራችን፥ መድኃኒታችንና መቅደሳችን፥ እናታችንና ንግሥታችን፥ መመኪያችንና ኪዳናችን ለኾነችው፡ ለቅድስት ድንግል ማርያም፡ ያለንን ጽኑ ፍቅር ለመግለጽ፡ በዓመቱ ውስጥ ከምናከብራቸው ታላላቅ በዓሎቻችን መካከል፡ ፍልሰቷን እና ፍልሰተ- ትንሣኤዋን፥ ፍልሰተ- ዕርገቷንም፡ በቅደም ተከተል የምናዘክርባቸው ዕለታት፡ ጥር ፳፩ እና ነሓሴ ፲፮፥ መስከረም ፳፩ ቀኖች ይገኛሉ፡፡

ቀድሞ፡ በሥነ ፍጥረት፥ ኋላም፡ በኢየሱስ መሲሕ ተገልጾ፡ ብዛታቸው ሊቆጠር የማይቻል፡ መልካካም ነገሮችን ላበረከተልን ፈጣሪያችን፡ ለእግዚአብሔር እንደምናደርገው ኹሉ፡ ስለቅድስት ድንግል ማርያምም፡ በየኅሊናችን የምናስበው፥ በአንደበታችን የምንናገረውና በየሕዋሳታችን የምንፈጽመውም ኹሉ፡ በየሕይወታችን ውስጥ፡ ዐብሮን ሕያው ኾኖ፡ ለዘወትር ባለማቋረጥ የሚካኼድ እንጂ፡ በአንድ ቀን ብቻ የተወሰነ አይደለም፡፡

አኹንም፡ እዚህ ላይ፡ ባጭሩ የምናቀርብላችሁ ዜና መዋዕሏ፡ በተለይ፡ በአዲስ ኪዳኑ መጽሐፍ ውስጥ ተመዝግቦ የሚነበበውን፥ ልጇ፡ ፈጣሪያችን እና ሰላማችን ኢየሱስ መሲሕ እስካረገበት፣ መንፈስ ቅዱስ፡ በሐዋርያት ላይ እስከወረደበት ቀን ድረስ ያለውንም አይደለም፤ ከዚያ በኋላ፡ በዚያው መልክና ይዘት የቀጠለው ምድራዊ ሕይወቷ፡ በ፷፬ ዓመታት ዕድሜዋ አብቅቶ፡ ጥር ፳፩ ቀን ከኾነው፡ ከመጀመሪያው ፍልሰቷ ዕለት የሚነሣውን፥ በየዓመቱ፡ በነሐሴ ፲፮ ቀን፡ ለኹለት ጊዜያት በተከታታይ በተከሠተው፡ በዚሁ ፍልሰታዋ በኩል አልፎ፥ በመጨረሻ፡ በመስከረም ፳፩ ቀን በተፈጸመው ዕርገቷ የተደመደመውን ዜና ብቻ ይኾናል፤ እርሱም፡ የዕርገቷን በዓል በምናከብርባት፡ በዚችው በመስከረም ፳፩ ቀን፡ እንዲህ በሚለው ቃል ይገለጻል፡-

የእግዝእተብሔር እም፡ ቅድስት ድንግል ማርያም፡ ምድራዊ ቆይታዋ አብቅቶ፡ በቅዱሳን መላእክት ይባቤ፡ ወደገነት ተነጥቃ የተወሰደችበት፥ ይኸውም፡ የመጀመሪያው ፍልሰቷ የተፈጸመበት ዝክር የሚታሰበው፡ "አስተርእዮ ማርያም" ተብሎ በሚከበረው፡ በጥር ፳፩ ቀን ነው። ከዚያ በቀጠለው፡ በነሐሴ ወር እኩሌታ፡ ኹለተኛውን ሕያው ፍልሰቷን፡ እንደልጇ ትንሣኤ አድርጋ ገለጠች። እንደዚሁ ኹሉ፡ ሦስተኛ ፍልሰቷን ደግሞ፡ እንደልጇ ዕርገት አድርጋ ትገልጠው ዘንድ ፈቃዱ ስለኾነ፡ የሕያው ፍልሰታዋን እውነታ፡ ማሳየትና ማሳወቅ የጀመረችበትን፡ ነሓሴ ፲፬ ቀንንና የጨረሰችበትን፡ ነሓሴ ፲፮ ቀንን፡ እነዚህን፡ ሦስት መዓልታትና ሦስት ሌሊታት መነሻ በማድረግ፡ በአርባኛው ዕለት፡ በመስከረም ፳፩ ቀን፡ እንደልጇ ኢየሱስ መሲሕ፡ ወደሰማይ ዐረገች።

እንግዴህ፡ ይህ፡ "ፍልሰታ" የሚለው ዘይቤ፡ በጥር ፳፩ ቀን በታየው ፍልሰታዊ ምጥቀቷ ተጀምሮ፡ በመስከረም ፳፩ ቀን በኾነው ፍልሰታዊ ዕርገቷ ያበቃውን፡ የፍልሰቷን አስተርእዮ አካትቶ ለማዘከር ተብሎ፡ የተመደበ ቃል መኾኑን፡ በማስተዋል መመልከት ነው።

በልጇ፡ በወዳጇ፡ በእግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ መሲሕ ብኵርናና ቀዳሚነት የተጀመረው፡ ያ፡ የመለኮት ምስጢራዊ ትንግርት የኾነው፡ የትንሣኤና የዕርገት ዕፁብ ድንቅ ነገር፡ እነሆ፡ አኹን ደግሞ በመጨረሻ፡ በእርሷ፡ በእናቲቱ በእግዝእተብሔር እም፡ ቅድስት ድንግል ማርያም ፍልሰትና ዕርገት፡ በበለጠ፡ ገሃድና እውን ኾኖ ታየ። ይህም ብቸኛ ታላቅ ተአምር፡ ዛሬ፡ በኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት የምሥራች ተልእኮ አማካይነት፡ ይኸው፡ ለፍጥረተ-ዓለሙ ኹሉ፡ በይፋ ተነገረ።

ይህን፡ የእግዝእተብሔር እም፡ ቅድስት ድንግል ማርያምን፡ ፍልሰታተ ትንሣኤ እና ዕርገት፡ በአንድ ጊዜ ለማየት፣ ምስክርም ለመኾን የታደለው፡ የመጀመሪያው ሐዋርያ፡ ቅዱስ ቶማስ ብቻ ኾነ። የፈጣሪያችንንና የሰላማችንን፡ የኢየሱስ መሲሕን፡ የትንሣኤውን ምሥራች፡ ከቀሩት ሐዋርያት ኹሉ ቀድማ ለማየት እና ለመስማት፥ ለእነርሱም፡ አስቀድማ ለማሰማት፡ ማርያም መግደላዊት፡ የመጀመሪያዋ ሐዋሪት እንደኾነች ኹሉ ማለት ነው።

አዎን! እርሱ፡ ሐዋርያው ቶማስ፡ ቀድሞ፡ የልጇን፡ የኢየሱስ መሲሕን፡ የትንሣኤ ምሥራች፡ ከቀሩት ሐዋርያት ጋር ዐብሮ ለመስማት እና ለማየት፡ ሳይታደል ቀርቶ የነበረ ሲኾን፡ አኹን ግን፡ ትንሣኤ-እሙታን ያላስፈለገውን፡ ይህን፡ ለእግዝእተብሔር እም ቅድስት ድንግል ማርያም፡ የሕያው ህልውናዋ፡ ገሃድ አስተርእዮ፡ ማረጋገጫ የኾነውን ፍልሰተ-ትንሣኤዋን፥ እንዲሁም፡ የዚሁ ፍልሰታዋ አማናዊ መገለጫ የኾነውን ዕርገቷን ጭምር፡ በአንድነት፡ ለብቻው ለማየት እና ቃሏን ለመስማት፡ ከቀሩት ሐዋርያት መካከል፡ ተለይቶ የታደለው፡ ይኸው፡ ሐዋርያው ቶማስ ኾኖ ተገኘ።

ከዚሁ፡ ከሐዋርያው ቶማስ ጋር የተያያዘው፡ የዚህ ርእሰ-ጉዳይ፡ ዝክረ ነገር፡ እንዲህ የሚል ነው፡-

"እግዝእተብሔር እም፡ ቅድስት ድንግል ማርያም፡ በመጀመሪያው ፍልሰቷ፡ በመላእክት ይባቤ ተነጥቃ፡ በገነት፡ በዕፀ ሕይወት ቦታዋ፡ የማረፍዋን፣ በገነት ለሚገኙ ቅዱሳን እና ቅዱሳት ነፍሳትም፡ በመለኮታዊ እና ትስብእታዊ ክብሯ ተገልጣ፡ የፍልሰታዋን ምሥራች የማሰማቷን ዕፁብ ድንቅ እግዚአብሔራዊ ሥራ፡ ወንድማቸው ዮሓንስ፡ ዐብሮ ተነጥቆ ኼዶ፡ አይቶ ኖሮ፡ የቀሩት ሐዋርያት ግን፡ ያን ታላቅ ተአምር ሳያዩ በመቅረታቸው አዝነው፡ "እኛስ ሳናይ፡ እንዴት እንቀራለን!? እናታችን ሆይ! ይህን ቸርነትሽን፡ ለእኛም አድርጊልን!" ብለው በመማፀን፡ በሚቀጥለው ነሓሴ ፩ ቀን፡ ሱባዔ ያዙ።

"ይህ ኹሉ ሲኾን፡ ማለትም፡ በመጀመሪያው ሱባዔ ጊዜ፡ ሐዋርያው ቶማስ፡ በቦታው አልነበረም። ለሐዋርያት በተሰጣቸው፡ የመንፈስ ቅዱስ ጸጋና ኃይል፡ እርሱም እንደለመደው፡ ደመና ጠቅሶ፡ እግዚአብሔር ባወቀውና ባደረገው ምክንያት ዘግይቶ፡ በዚያ በደመናው እየተጓዘ፡ ከሀገረ ስብከቱ፡ ወደወንድሞቹ ሐዋርያት ሲመጣ፡ እግዝእተብሔር እም፡ ቅድስት ድንግል ማርያም፡ እያረገች ሣለች፡ እርሷ በፈቀደችው በጎ መንገድ፡ ለእርሱ፡ ለቶማስ ተገለጠችለት።

"ያችም ዕለት፡ የእርሷ ፍልሰታዊ ትንሣኤ፡ እንደልጇ እንደኢየሱስ መሲሕ አማናዊ ትንሣኤ፡ ለሐዋርያት፡ በአስተርእዮ የተከሠተባት፥ ከነሓሴ ፲፬ እስከ፲፮ ቀን ያሉትን፡ ሦስቱን መዓልታትና ሦስቱን ሌሊታት ያጠቃለለችውና መነሻ ያደረገችው፥ እንደልጇም ዕርገት፡ በአርባኛው ዕለት፡ ወደሰማይ ያረገችባት፡ መስከረም ፳፩ ቀን እሑድ ናት።

"በዚህ ጊዜ፡ ቶማስ፡ ከደመናው ሊወድቅ እስኪናወጽ ድረስ፡ ሰውነቱ ታውኮበት፡ 'ቀድሞ፡ ሌሎቹ ወንድሞቼ ሐዋርያት ኹሉ ታድለው፡ የልጅሽን ትንሣኤ ሲያዩ፡ እኔ ብቻ ሳላይ ቀረሁ። አኹን ደግሞ፡ እነርሱ፡ ኹላቸው፡ ይኸው፡ የአንቺን ፍልሰት፡ ቀድመውኝ ሲያዩ፡ እኔ ብቻ ሳላይ ቀረሁ!' ብሎ፡ ማዘኑን ገለጠላት።

"እግዝእተብሔር እም፡ ቅድስት ድንግል ማርያምም፡ 'አይዞህ! አትዘን! እኒያ ወንድሞችህ፡ በልጄ ጊዜ፡ በመጀመሪያ፡ የእርሱን የትንሣኤ ምሥራች፡ ከሌሎች ሴቶች ሐዋርያት ሰምተው ሳያምኑ በመቅረታቸው፡ ኋላ፡ ከአንተ በፊት፡ እነርሱ ያዩት ቢኾንም፥ አንተ፡ ለጊዜው፡ በራስህ ፍላጎት፡ በዚያ ባለመኖርህ፡ ሳታየው ብትቀርም፡ ዕርገቱን፡ ዐብረሃቸው ኾነህ አይተሃል።

አኹንም፡ እንደዚያኑ ጊዜ፡ እነርሱ፡ የእኔን፡ ፍልሰቴን ያዩ ኾነው፡ አንተ፡ ያላየህ ብትኾንም፡ ይኸው፡ አኹን ደግሞ፡ ፍልሰተ-ዕርገቴን ያየህ፡ አንተ ብቻ እንጂ፡ እነርሱ አላዩም። ስለዚህ፡ ከእነርሱ ይልቅ፡ በበለጠ የታደልህ፡ አንተ ነህ፤ ፍልሰቴንም፣ ዕርገቴንም፡ ኹለቱንም፡ በአንድነት አይተሃልና!" ብላ አጽናናችው።

"ቀጥላም፡ እንዲህ አለችው፦ 'አኹንም፡ ወደእነርሱ ኼደህ፡ ‹ዐረገች!› ብለህ፡ የፍልሰታዬን ዕርገት ምሥራች ንገራቸው።' ይህንም ብላ፡ የውስጥ መጐናጸፊያዋን ሰጥታ፡ ሰደደችው። እርሱም፡ በግንባሩ ሰግዶና በእጁ ተባርኮ፡ በደስታ እና በምስጋና ዓይኖቹ እየተመለከታት ተሰናበታት።

"ቶማስ፡ ከቦታው ደርሶ፡ በሱባዔና በጉባኤ የሰነበቱ ወንድሞቹን ሐዋርያትን ሲገናኛቸው፡ 'እረ! የእናታችን ነገር፡ እንደምን ኾነ?" ብሎ ጠየቃቸው።

"እነርሱም፡ የኾነውን ትንግርት ኹሉ፡ ምንም ሳያስቀሩ፡ አንድ በአንድ እየተቀባበሉ ነገሩት።

"ቶማስም፡ ጸጥ ብሎ፡ ነገራቸውን አዳምጦ፡ ካስጨረሳቸው በኋላ፡ 'ታዲያ! አኹን፡ የት ነው፡ ያለችው? እጅግ ናፍቃኛለችና፡ ኼጄ፡ እንድሳለማት፤ እንድሰግድላትም፡ ያለችበትን ንገሩኝ!' አላቸው።

"በዚህ ጊዜ፡ ቅዱስ ጴጥሮስም፥ ዐብረውት ያሉት፡ የቀሩት ሐዋርያትም፡ ኹሉም፡ የሚመልሱት አጥተው፥ አቀርቅረው፡ ዝም አሉ።

"ቶማስም፡ ጥያቄውን በመቀጠል፡ 'እንዳወጋችሁልኝ፡ በትንሣኤ መልክ ከታየችበት፡ ከመጀመሪያው የፍልሰቷ አስተርእዮ በኋላ፡ እስካኹን እንዳስለመደቻችሁ፥ ልጇ ጌታችን ኢየሱስ መሲሕም፡ እስከዕርገቱ ድረስ፡ ዐልፎ ዐልፎ እየተገለጠ ያነጋግረን እንደነበረው ኹሉ፡ ምናልባት፡ እርሷም፡ ድንገት፡ በመካከላችን፡ ትገኝ እንደኾነ፡ እንጠብቃት ይኾን?" አላቸው፣ እያንዳንዳቸውን፡ ተዘዋውሮ እየተመለከተ።

"እነርሱም፥ ኹሉም፡ 'አዎን! ልክ ነህ፤ ይህ ያልከው ነገር፡ 'አይኾንም!' አይባልም። ምናልባት፡ ሊኾን ይችላል!' በሚል ስሜት፡ ቀና ብለው እያዩት፡ ወደዝምታቸው ተመለሱ።

"በዚህን ጊዜ፡ ቶማስ፡ ባጭር ቃል፡ 'መቼም፡ ‹አታምኑኝም!› ብዬ ነው እንጂ፡ ደስ ይበላችሁ! እናታችን እግዝእተብሔር እም፡ ቅድስት ድንግል ማርያም፡ በፍልሰታዋ እንዳለች ኾና፡ ዐርጋለች! በልጇ፡ በጌታችን እግዚአብሔር ወልድ፡ ኢየሱስ መሲሕ የትንሣኤ ዕለት፡ በገዛ ድክመቴና ጥፋቴ፡ ከወንድሞቼ ሐዋርያት ጋር፡ ዐብሬ ባለመገኘቴ፡ በራሴ ላይ ያሳደርሁትን፡ የዘለዓለም የጸጸት እሳት፡ በርኅራኄዋና በቸርነቷ ልታስወግድልኝ ፈቃዷ ኾኖ፥ ለዚያ በደሌ፡ ዋጋዬን፡ እኔ መክፈል ሲገባኝ፡ እንዲያውም፡ ‹ይህ ካሣ ይኹንህ!› ብላ፡ ይህን ቸርነት፡ ለእኔ፡ ለአገልጋይዋ አደረገችልኝ!' በማለት፡ ወንድሞቹ ሐዋርያት፡ ትኩር ብለው እየተመለከቱት፡ በግንባሩ ተደፍቶ፡ ሥቅሥቅ ብሎ አለቀሰ፤ የደስታ እንባውንም አፈሰሰ።

"እነርሱም፡ ባንድነት ኾነው፡ ከወደቀበት ካነሡት በኋላ፡ 'እንኳን ደስ አለህ!' ከሚል ቃል ጋር፡ እያቀፉ፡ በፍቅር አጽናኑት።

"ቶማስም፡ በደስታ ፈክቶ፡ 'እኔ በሌለሁበት ስለኾነው ኹሉ፡ እናንተ፡ አኹን ያላችሁኝን ጨምሮ፡ ከእርሷ ሰምቼዋለሁ። ለኹላችንም የሚኾን የእናትነት ምክሯንም ለግሳኛለች። በብዙ አጽናንታኛለች። ይህን የውስጥ ተደራቢ መጐናፀፊያዋን፡ ለኹላችንም፡ ለበረከት እንዲኾነን፡ ይኸውላችሁ፡ በእኔ እጅ ሰድዳላችኋለችና፡ እንካችሁ ተረከቡኝ!' ብሎ ሰጣቸው።

"ሓዋርያት፡ ያን፡ የእናትነት ስጦታዋን በማየታቸውና በማግኘታቸው፡ እጅግ ደስ ብሏቸው፡ በቅዱስ ጴጥሮስ አማካይነት ተቀብለው፡ ለበረከት ተካፈሉት።

"ይህ በኾነ፡ ልክ በዓመቱ፡ የቀሩት ሓዋርያት፡ 'ቶማስ፡ ፍልሰታዊ ዕርገትሽን አይቶ፡ እኛ ሳናይ፡ እንዴት እንቀራለን? እኛንም፡ ለዚህ ዕድል አብቅተሽ፡ እባክሽ አሳዪን!' ብለው፡ ወደፈጣሪያቸው የሚቀርብ፡ ኹለተኛውን፡ የ፪ ሳምንት ሱባዔያቸውን፡ ቶማስ ጭምር፡ ዐብሮአቸው በተሳተፈበት፡ በሚቀጥለው ነሓሴ ፩ ቀን፡ በተገቢው ጾምና ጸሎት፥ ትህርምትና ብሕትውና፡ በአንድነት ጀመሩ።

"የኹለተኛው ሳምንት ሱባዔ፡ በነሓሴ ፲፬ ቀን፡ እንደተፈጸመም፡ በነሓሴ ፲፭ ቀን፡ ሓዋርያት፡ በቅድሚያ፡ ከእየግል በአታቸው ወጥተው፡ በአንድነት በተሰበሰቡበት፡ በመንበረ ጳባዖት ቅድስት ሥላሴነቷ እና በኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥትነቷ፥ በኪዳነ ምሕረትነቷም፡ ኹሉን አንድ አድርጋ የምትመለከውና የምታስመልከው፡ እግዝእተብሔር እም፡ ድንግል ማርያም ተገልጣ፡ መለኮታዊ ክብሯንና ብርሃኗን ተጎናጽፋ፡ በመካከላቸው ተገኘችላቸው።

"በዚህ ጊዜ፡ እጅግ ደስ ብሏቸው፡ ወድቀው ከሰገዱላት በኋላ፡ ዙሪያዋን ኾነው፡ ሱባዔያቸውን፡ በሰላምና በፍቅር ስላስፈጸመቻቸው፥ በእርሱም፡ ተስፋ ያደረጉትን አማናዊ መልስ ስላስገኘችላቸው፡ ምስጋናቸውን፡ በኅብረት ጸሎታቸውና ዝማሬያቸው፥ ውዳሴያቸውና ቅዳሴያቸው አቀረቡ።

በመጨረሻ፡ በነሓሴ ፲፮ ቀን በሚውለው፡ በፍልሰታ ለማርያም በዓል ዕለት፡ ሓዋርያትና እነርሱን የመሰሉት ኹሉ፡ በእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ፡ ወደሰማያዊቷ ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት ተነጥቀው ኼደው፡ እግዝእተብሔር እም፡ ቅድስት ድንግል ማርያም፡ በመንበረ ጸባዖትነቷና በቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያነቷ የምትገኝበትን ክብርና ምስጋና አዩ! ለዘለዓለምም፡ እያዩ ይኖራሉ።

ልጇ እግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ መሢሕ፡ እርሷን፡ ቅድስት እናቱን፡ መንበር፥ ራሱን፡ ሠራዒ (ዋና) ካህን፥ ሊቀ ሓዋርያት ጴጥሮስን፡ ንፍቅ (ረዳት) ካህን፥ ቀዳሜ ሰማዕት እስጢፋኖስን፡ ሠራዒ ዲያቆን፥ ኢትዮጵያዊዉን ጃንደረባ አቤሜሌክን ያጠመቀውን ፊልጶስንም፡ ተራዳኢ (ንፍቅ) ዲያቆን አድርጎ፡ ቀድሶ፥ ራሱም ቆርቦ፥ እናቱንም አቍርቦ፥ ቀዳስያኑን ካህናትና የቀሩትን ሓዋርያት፣ እነርሱን የመሰሉትንና በዚያ የታደሙትን አማኞቹን ኹሉ አቆረበ። ለዘለዓለምም፡ እያቆረበ ይኖራል።

በዚያን ጊዜ፡ በመላው ፍጥረታተ-ዓለማት ዘንድ፡ በሥጋም፥ በነፍስም፥ በመንፈስም፡ ታላቅ ደስታ፥ ታላቅ ሓሤት ኾነ! ለዘለዓለምም፡ እየኾነ ይኖራል። (ራእ. ፲፩፥ ፲፱፤ ፲፪፥ ፩-፲፯።)

ስለዚህ: ይህን የእግዝእተብሔር እም፡ ቅድስት ድንግል ማርያምን: በዓለ ፍልሰተ-ዕርገት: በያለንበት፥ በተለይም: የልጇ፥ የወዳጇ፥ የፈጣሪያችንና የሰላማችን፡ የእግዚአብሔር ወልድ፡ ኢየሱስ መሲሕ: የዕፀ መስቀሉ ዜና: ተስፋፍቶ በሚነገርባት እና በሚወደስባት: በግሼን ማርያም ደብር: በዛሬዪቱ መስከረም ፳፩ ቀን ለማክበር ስላበቃን: ቸሩ አምላካችንን እያመሰገንነው: "**ንግሥተ ሰማያት ወምድር፡ ማርያም ድንግል! ተፈጸመ ፍልሰታሃ፥ ወዕርገታ ዘልዑል!**" ማለትም፡ "ድንግል ማርያም፡ የሰማይና የምድር ንግሥት ናት! ሉዓላዊ የኾነው ፍልሰቷ፥ ዕርገቷም፡ እነሆ፡ ተፈጸመ!" ከሚለው የይባቤ መዝሙራችን ጋር፡ “ዐርገት ውስተ አርያም፡ ማርያም ድንግል! **በፍልሰተ-ሕያው ሥጋሃ** ዘልዑል! ማርያም ድንግል፡ የልዑል ልጇን ዕርገት በመሰለ ይባቤ፡ በሕያው ሥጋዋ ፍልሰት፡ ወደሰማያት ዐረገች!" በሚለው የምሥራች ቃል: "እንኳን አደረሰን!" በማለት፡ ለኹላችንም: በያለንበት፡ “መልካም በዓል ይኹንልን!” እንላችኋለን::

## በዓለ በአተ መቅደስ፥

## በዓለ ስምዖን።

“በዓለ በአተ መቅደስ”፥ ወይም: “በዓለ ስምዖን” ተብሎ፡ ጥቅምት ፲ ቀን የሚከበረው በዓል: ሕፃኑ እግዚአብሔር ወልድ፡ ኢየሱስ: መሲሕ፡ እንደኦሪቱ ሥርዓት: በእግዚአብሔር ፊት ሊያቆሙት: በአርባ ቀኑ: በእናቱ በእግዝእተብሔር እም፡ ድንግል ማርያም ዕቅፍ: ከመሥዋዕቱ ጋር: ወደቤተ መቅደስ የገባበትንና ለአረጋዊው ጻድቅ፡ ለስምዖን ተገልጾ የታየበትን ዕለት የሚያስታውሰን ነው:: በዚያች ዕለት የኾነውን ዝክረ ነገር: ከዚህ የሚከተሉት: የኦሪታውያኑ አይሁድ፡ የብሉዩ እና ከእርሱ ጋር የተያያዙት፡ የሓዲሱ ኪዳናት መጻሕፍት ጥቅሶች ይናገሩታል::

**“ወይቤሎ እግዚአብሔር ለሙሴ፡- 'ቀድስ ሊተ፡ ኵሎ በኵረ፣ ቀዳሜ ውሉድ፣ ኵሉ ዘይፈትሕ ማህፀነ፡ እምደቂቀ እስራኤል፣ እምሰብእ እስከእንስሳ፣ ሊተ ውእቱ።** እግዚአብሔርም: ሙሴን፦ 'ከእስራኤል ልጆች፡ ከሰው ጀምሮ፡ እስከከብቱ ድረስ፡ የእናቱን ማሕፀን ከፍቶ፡ በመጀመሪያ የተወለደው ኹሉ: ለእኔ ነውና፣ ብኵር በኵሩን ኹሉ ለይልኝ!' አለው።

ደግሞም፡ "**ወነበቦ እግዚአብሔር ለሙሴ፤ ወይቤሎ፡- «በሎሙ! ለደቂቀ እስራኤል፤ ወንግሮሙ፡ እንዘ ትብል፡- 'ብእሲት፡ አመ ፀንሰት፣ ወወለደት ተባዕተ፣ ርኵስት ይእቲ፡ እስከሰቡዕ ዕለት፣ በከመ መዋዕለ ትክቶሃ። ወበሳምንት ዕለት፡ ታገዝሮ፡ ከተማ ነፍስቱ። ወሠላሳ ወሠለስቱ ዕለተ፡ ትንብር፡ በእንተ ደማ፡ ለነጺሖታ፡ እምኵሉ ርኵስ፤ ወእምኵሉ ቅዱስ፡ ኢትግሥሥ! ወቤተ-መቅደስ ኢትባእ! እስከ ትፌጽም፡ መዋዕለ ንጽሓ። ወእመሰ፡ ወለደት አንስተ፣ ርኩስት ይእቲ፡ ዐሠርተ ወአርባዕተ መዋዕለ፣ በከመ ትክቶሃ። ወስሳ፥ ወስድስተ ዕለተ፡ ትነብር፡ በእንተ ደማ፡ ለነጺሖታ። ወአመ ተፈጸመ፡ መዋዕለ ንጽሓ፣ እመኒ፡ በእንተ ወልድ፣ ወእመኒ፡ በእንተ ወለት፡ ታመጽእ በግዐ ዘዓመት፡ ለመሥዋዕት።**

**"«'ወእመኒ፡ ዕጕለ ርግብ፣ አው ዘማዕነቅ፡ በእንተ ኃጢኣት፤ ኀበ ኆኅተ ደብተራ ዘመርጡል፡ ኀበ ካህን። ወያበውእ ካህን፡ ቅድመ እግዚአብሔር፤ ወያስተሰሪ ላቲ፡ ካህን፤ ወያነጽሓ፡ እምነቅዐ ደማ። ዝንቱ ውእቱ ሕጉ፡ ለእንተ ትወልድ፡ እመኒ፡ ተባዕተ፣ ወእመኒ አንስተ። ወእመሰ አልባቲ ውስተ እዴሃ፣ ወኢተአክል ለበግዕ፡ ታመጽእ ክልኤተ ማዕነቀ፣ አው፡ ክልኤተ ዕጕለ ርግብ፣ አሐዱ ለመሥዋዕት፣ ወአሓዱ፡ ዘበእንተ ኃጢኣት፤ ወያስተሰሪ ላቲ፡ ካህን፤ ወትነጽሕ።'»**

"እግዚአብሔር ለሙሴ፡- እንዲህ ብሎ ተናገረው፡- «ለእስራኤል ልጆች፡ እንዲህ ብለህ ንገራቸው አለው፡- 'ሴት ብታረግዝ፥ ወንድ ልጅንም ብትወልድ፡ ሰባት ቀናት ያህል የረከሰች ናት፤ እንደግዳጅዋ የመርገም ወራት ትረክሳለች:: በስምንተኛውም ቀን፡ ሕፃን ልጁ፡ ከአባለ-ዘሩ ሸለፈት፡ ይገረዝ! ከደምዋም እስክትነጻ፡ ሠላሳ ሦስት ቀናት፡ ከሰው ተለይታ፡ ትቀመጥ! የመንጻትዋ ቀንም እስኪፈጸም ድረስ፡ የተቀደሰ ነገር አትንካ! ወደቤተ-መቅደስም አትግባ!'

“«'ሴት ልጅንም ብትወልድ፡ እንደመርገምዋ ወራት፡ ኹለት ሳምንታት ያህል፡ የረከሰች ናት፤ ከመርገም ደምዋ እስክትነጻ ድረስ፡ ስድሳ ስድስት ቀናት ለብቻዋ ትቀመጥ! የንጽሕናዋ ወራት፡ የወንድ ልጅ ኾነ፥ የሴት ልጅ፡ እንደሙሴ ሕግ፡ በተፈጸመ ጊዜ፡ አንድ ዓመት የኾነውን በግ ታምጣ! ስለኃጢኣት፡ ከርግብ፥ ወይም፡ ከዋኖስ ወገን ቢኾን፡ ካህን ወዳለበት፡ ወደኦሪት ድንኳን ደጃፍ ታምጣ! ካህኑም፡ በእግዚአብሔር ፊት አቅርቦ፡ ኃጢኣቷን ይስተስርይላት! ከደሟም ያንጻት! ወንድ ልጅ ኾነ፥ ሴት ልጅ ለምትወልድ ሴት፡ ሕጉ ይህ ነው። ነገር ግን፡ በእጁ፡ ምንም ገንዘብ ስለሌላት፡ ለመሥዋዕት የሚቀርበውን በግ ለመግዛት የማይቻላት ቢኾን፡ ኹለት የርግብ ግልገሎች፥ ወይም፡ ኹለት ዋኖሶች፡ አንዱን፡ ለመሥዋዕት፣ አንዱን፡ ስለኃጢኣት ታምጣ! ካህኑም፡ ከኃጢኣት ያንጻት! ኃጢኣቷንም ያስተስርይላት!'»

[በሓምሌ ፲፮ ቀን፥ ፳፻፱ ዓመተ ምሕረት በታወጀው፡ በመለኮታዊው ዐዋጅ ቊጥር ፲፩/፳፻፱ ዓ. ም. እንደተብራራው፡ ይህን በሓሰት፡ "የእግዚአብሔር፥ ወይም፡ የሙሴ ነው!" የተባለውን ኦሪታዊ እና ሰይጣናዊ ሕግ፡ በእውነት የእግዚአብሔር ሳይኾን፡ የክፉ ሰዎች ጭማሪ በመኾኑ፡ **ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት፡** ፈጽማ አትቀበለውም። ነገር ግን፡ ወልደ-አብ ወልደ-ማርያም፡ እግዚአብሔር ወልድ፡ ኢየሱስ መሲሕ፡ የፊት ተቃዋሚዎቹ፣ የኋላ ሰቃዮቹ እና የመጨረሻ ገዳዮቹ ኾነው የተገኙትን፣ "የእስራኤል ልጆች" የተባሉትን፡ አይሁድን ብቻ፡ ሊያድናቸው፡ ሰው ኾኖ የመጣ በመኾኑ፡ "**ኢይምሰልክሙ፡ ዘመጻእኩ፡ እስዓሮሙ፡ ለኦሪት፥ ወለነቢያት፤ ዘእንበለ ዳእሙ፡ ከመ እፈጽሞሙ!** የእኛ የእግዚአብሔር የኾኑትን፡ የኦሪትን እና የነቢያትን ቃላት፡ ልፈጽማቸው ካልኾነ በቀር፣ ልሽራቸው የመጣሁ አይምሰላችሁ!" ባለው ቃሉ መሠረት፡ ይኸው፡ ከማሕፀን ጀምሮ ሲፈጽማቸው ይታያል።]

**"በከመ ዝ ሕገ-ሙሴ፡ ወአመ ተፈጸመ ሰሙን ዕለት፡ ወሰድዎ ለሕፃን፡ ከመ ይግዝርዎ፤ ወሰመይዎ ስሞ፡ 'ኢየሱስ!' በከመ ሰመዮ መልአክ፡ እምቅድመ ትፅንሶ በከርሣ። ወአመ ተፈጸመ፡ መዋዕለ ንጽሖሙ፡ ወሰድዎ ኢየሩሳሌም፤ ያቅምዎ ቅድመ እግዚአብሔር። በከመ ጽሑፍ፡ ውስተ ሕገ-እግዚአብሔር፡- 'ኵሉ ተባዕት፡ ዘይፈትሕ ማሕፀነ እሙ፡ 'ቅዱሰ ይሰመይ ለእግዚአብሔር!' ወከመ ያብኡ መሥዋዕተ፡ በእንቲአሁ፣ በከመ ተብህለ፡ ውስተ ሕገ-እግዚአብሔር፡- ዘውገ ማዕነቅ፤ ወእመ አኮ፡ ክልኤቲ ዕጕለ ርግብ።**

በዚህ፡ በሙሴ የኦሪቱ ሕግ መሠረት፡- ስምንተኛው ቀን በተፈጸመ ጊዜ፡ ይገዝሩት ዘንድ ወሰዱት። በማሕፀንዋ ከመፀነሱ በፊት፡መልአኩ፡ እንደሰየመውም፡ ስሙን፡ 'ኢየሱስ!' ብለው ሰየሙት። የመንጻታቸውም ወራት በተፈጸመ ጊዜ፡ በኦሪቱ ሕግ፡- "የእናቱን ማሕፀን የሚከፍት ወንድ ኹሉ፡ 'ለእግዚአብሔር የተቀደሰ ይባላል!' ተብሎ እንደተጻፈ፡ በእግዚአብሔር ፊት ሊያቆሙት፥ በእግዚአብሔርም ሕግ፡- 'ኹለት ዋልያ፡ ወይም፡ ኹለት የርግብ ጫጩቶች' እንደተባለ፡ መሥዋዕት ሊያቀርቡ፡ ወደኢየሩሳሌም ወሰዱት።።"

**"ወሀሎ ፩ዱ ብእሲ፡ በኢየሩሳሌም፡ ዘስሙ 'ስምዖን'፤ ወውእቱ፡ ጻድቅ፥ ወየዋህ፤ ወይሴፎ ይርአይ መድኃኒቶሙ፥ ወፍሥሓሆሙ ለእስራኤል፤ ወመንፈስ ቅዱስ ላዕሌሁ። ወአርአዮ መንፈስ ቅዱስ፡ ከመ ኢይመውት፡ ዘእንበለ ይርአይ መሲሐ ለእግዚአብሔር። ወወሰዶ መንፈስ ምኵራበ። ወሶበ አብእዎ አዝማዲሁ ለሕፃን ኢየሱስ፣ ከመ ይግበሩ ሎቱ ዘበሕጉ። ተወክፎ ውእቱኒ፣ ወአንበሮ ውስተ ሕፅኑ፤ ወባረኮ ለእግዚአብሔር፤ ወይቤ፡- 'ይእዜ፡ ትስዕሮ ለገብርከ፤ በሰላም እግዚኦ፡ በከመ አዘዝከ። እስመ ርእያ አዕይንትየ፡ አድኅኖተከ፤ ዘአስተዳለውከ፡ ቅድመ ኵሉ ሕዝብከ። ከመ ትክሥት፡ ብርሃነ፡ ለአሕዛብ፤ወክብረ፡ ለሕዝብከ እስራኤል።**

"እነሆም፡ በኢየሩሳሌም፡ 'ስምዖን' የሚባል አንድ ሰው ነበረ፤ እርሱም፡ እውነተኛ እና ደግ ነበረ። ይህም ሰው፡ የእስራኤልን መድኃኒታቸው እና ደስታቸው የኾነውን ሊያይ፡ በተስፋ ይጠባበቅ ነበር፤ መንፈስ ቅዱስም፡ በእርሱ ላይ ነበረ። በእግዚአብሔር የተቀባውንም ሳያይ፡ እንዳይሞት፡ መንፈስ ቅዱስ ገልጦለት ነበር።። በመንፈስ ቅዱስ፡ ወደቤተ-መቅደስ መጥቶ ሣለ፡ እናቱ እና ዘመዶቹ፡ እንደሕጉ ልማድ ያደርጉለት ዘንድ፡ ሕፃኑን ኢየሱስን፡ ይዘውት፡ ወደመቅደስ ባገቡት ጊዜ፡ እርሱ ደግሞ፡ በክንዱ ተቀብሎ፡ ዐቀፈው፤ እግዚአብሔርንም እያመሰገነ እንዲህ አለ፡- 'እግዚአብሔር ሆይ! አቤቱ! በሰላምህ እንዳዘዝህበት ቃልህ፡ ዛሬ፡ እኔን አገልጋይህን፡ በሰላም ታሰናብተኛለህ፤ ብርሃንን፡ ለአሕዛብ፥ ክብርንም፡ ለሕዝብህ፡ ለእስራኤል ትገልጽ ዘንድ፡ በሕዝብህ ኹሉ ፊት ያዘጋጀኸውን ማዳንህን፡ ዓይኖቼ አይተዋልና።።'

**"ወዮሴፍሰ፥ ወእሙ ያነክሩ፡ በእንተ ዘይነብብ ላዕሌሁ። ወባረኮሙ ስምዖን፤ ወይቤላ ለእሙ ማርያም፡- 'ናሁ ዝንቱ ሕፃን፡ ሥዩም፣ ለድቀቶም፥ ወለተንሥኦቶሙ፡ ለብዙኃን፡ እምውስተ እስራኤል፤ ወለትእምርት፡ በዘይትወቀሱ። ወለኪሰ፡ ይበውእ ውስተ ልብኪ፡ ኵናተ ኑፋቄ፡ ከመ ይክሥት ኀሊና ልቦሙ ለብዙኃን።** "ዮሴፍ እና እናቱም፡ ስለእርሱ በተባለው ነገር፡ ይደነቁ ነበር።። ስምዖንም ባረካቸው። እናቱን ማርያምን ፡- 'እነሆ፡ ይህ ሕፃን ፡ በእስራኤል ላሉት፡ ለብዙዎቹ፡ ለመውደቃቸው እና ለመነሣታቸው፥ ባለማምናቸውም ሊወቀሱበት፡ ምልክት ኾኖ ተሾሟል።። በአንቺ ግን፡ የብዙዎችን ሰዎች፡ የልባቸውን አሳብ ይገልጥ ዘንድ፡ በነፍስሽ፡ የጥርጣሬ ሠይፍ ይገባል!' አላት።።

**"ወሀለወት ሐና ነቢይት፡ ወለተ-ፋኑኤል፣ እንተ እምነገደ አሴር። ወኀለፈ መዋዕሊሃ፤ ወምስለ ምታሰ፡ ነበረት፡ ሰብዓተ ክረምተ፣ እምድኅረ ነበረት በድንግልናሃ። ወኮነት መዓስብተ ሰማንያ ወአርባዕተ ክረምተ። ወኢትወጽእ እምኵራብ፣ መዐልተ፥ ወሌሊተ፣ እንዘ ትትቀነይ በጾም፥ ወበጸሎት። ወተንሥአት ሶቤሃ፤ ወገነየት፥ ወአእኰተቶ ለእግዚአብሔር። ወነገረት በእንቲአሁ፡ ለኵሎሙ እለ ይሴፈዉ፡ መድኃኒታ ለኢየሩሳሌም።**

ከአሴር ወገን የምትኾን፡ የፋኑኤል ልጅ፡ ሐና የምትባል፡ አንዲት ነቢይትም ነበረች። እርሷም፡ በዕድሜዋ የገፋች ነበረች። ከድንግልናዋ ጀምራ፡ ከባልዋ ጋር፡ ሰባት ዓመት፤ ከዚያም፡ ሰማንያ አራት ዓመት ያህል፡ መበለት ኾና ኖረች። በጾምና በጸሎትም ተጠምዳ፡ ሌሊትና ቀን እያገለገለች፡ ከመቅደስ አትለይም ነበር፡፡ በዚያችም ሰዓት ቀርባ፡ እግዚአብሔርን እያገነነች አመሰገነች፤ የኢየሩሳሌምንም የመዳኗን ቤዛ ለሚጠባበቁ ኹሉ፡ ስለእርሱ ትናገር ነበር፡፡"

እኛ ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት፡ ዛሬ፡ ሕፃናት ልጆቻችንን፡ ወንዶቹን፡ በ፵፥ ሴቶቹንም፡ በ፹ ቀናቸው፡ ወደቤተ ክርስቲያን ወስደን፡ በዚያ፡ የክርስትናን ጥምቀት የምናስጠምቃቸው፡ አንዱ መሠረታዊ ምክንያት ይህ ነው፡፡ (ዘፀአ. ፲፫፥ ፩። ዘሌዋ. ፲፪፥ ፩-፱። ማቴ. ፳፥ ፲፯-፲፰። ሉቃ. ፪፥ ፳፩-፴፰፡፡)

## ወርኀ ጽጌ፡፡

ከመስከረም ፳፮ እስከ ኅዳር ፮ ቀን ድረስ፡ አርባ ዕለታት ያለው ወራት፡ "ወርኀ ጽጌ" ወይም፡ "ዘመነ ጽጌ" ይባላል፡፡ እግዝእብሔር እም፡ ድንግል ማርያም እና ሕፃን ልጇ፡ እግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ መሲሕ፡ የተቀበሉትን፡ ቀዳሚ የስደት መከራ በማሰብ፡ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት፡ "ጾመ ስደት" ብለው፡ በየዓመቱ የሚፈጽሙት፡ የመጀመሪያው የዓመቱ ጾማቸው የሚካኼደው፡ በዚሁ፡ በ"ዘመነ ጽጌ"፡ ከጥቅምት ፲፩ እስከኅዳር ፮ ቀን ድረስ መኾኑ ይታወቃል፤ ይህም የኾነው፡ ስደቱ የተጀመረው፡ ሕፃን ኢየሱስ፡ በተወለደ በ፵ኛው ቀን፡ በእግዚአብሔር ፊት ሊቀርብ፡ ቤተ መቅደስ ከገባበት፡ ከጥቅምት ፲ ቀን በኋላ በመኾኑ ነው።

በግእዝ፡ "ጽጌ" ማለት፡ "አበባ" ነው፡፡ ዘር ኹሉ፡ ከፍሬ በፊት የሚያሳየው የምሥራች ምልክት፡ "አበባ"ን እንደመኾኑ መጠን፡ እግዚአብሔር፡ አዳምንና ሔዋንን፡ በኢትዮጵያ ምድር ፈጥሮ፡ ለመኖሪያቸው በከለለላቸው፡ የዔዶም ገነት መኻከል፡ የተከላት "የሕይወት ዛፍ" ምሳሌዋ የኾነችው፡ "እውነተኛዪቱ ሕያውት ዛፍ"፡ እግዝእተብሔር እም፡ ድንግል ማርያምም፡ እውነተኛውን የዘለዓለም የሕይወት ፍሬ፡ እግዚአብሔር ወልድ፡ ኢየሱስ መሲሕን፡ ከመውለዷ በፊት፡ በዘለዓለማዊት አበባነቷ፡ የፍጹም ድንግልናዋን የወር አበባ እያየች፡ እንደርግበ ኖኅ፡ የዓለሙን የደኅንነትና የሰላም ምሥራች፡ ለፍጥረቱ ኹሉ ማወጇን ለማስረዳት፡ በአበባ ተመስላለች፡፡

## ጾመ ስደት እና ማኅሌተ ጽጌ፡፡

የ"ጾመ ስደት" እና የ"ወርኀ ጽጌ" ምስጢር፡ ኢትዮጵያዊው ሊቅ፡ ገዳማዊ ጽጌ ድንግል፡ "ሰቆቃወ ድንግል" እና "ማኅሌተ ጽጌ" በተባሉት፡ በግእዙ፡ የመልክዓታት ድርሰቶቹ፡ ገላልጦ፡ በሰፊው ተናግሮታል፡፡ "ዮሴፍ፡ የእግዚአብሔር መልአክ፡ ሌሊት፡ በሕልሙ እንደነገረው፡ ከእንቅልፉ ተነሥቶ፡ ሕፃኑን፡ ከእናቱ ከማርያም ጋር ይዞ፡ ወደግብፅ አገር ሸሸ፤ ማርያምም፡ 'የልጄን ደም ሲያፈስሱት ከማይ ይልቅ፡ የእኔን ሞት ያስቀድሙት!' ብላ አለቀሰች፡፡" ተብሎ የሚተረጐመውን፡ የ"ሰቆቃወ ድንግል" ድርሰቱን ይጀምራል፡፡

ይህም፡ “ጐየ ዮሴፍ፡ ብሔረ ግብፅ፡ ተንሢኦ እምንዋሙ፤ መልአከ እግዚአብሔር ሌሊተ፡ በከመ ነገሮ በሕልሙ፤ ነሢኦ ሕፃነ፡ ዘምስለ ማርያም እሙ፤ ይእቲ ትበኪ፥ ወትቤ፡ 'ቀቲሎትየ ይቅድሙ! እምእርአይ ለወልድየ፡ ዘይትከዓው ደሙ!'” የሚለው የግእዙ ቃል ነው፡፡

ገዳማዊ ጽጌ ድንግል፡ የ“ማኅሌተ ጽጌ” ድርሰቱን፡ “ጽጌ አስተርአየ፡ ሠሪፆ እምዓጽሙ!” በሚል መክፈቻ ጀምሮ፡ “እንዘ ተሐቅፊዮ ለሕፃንኪ፡ ጽጌ ፀዓዳ ወቀይሕ፤ አመ ቤተ መቅደስ ቦእኪ፡ በዕለተ ተአምር ወንጽሕ፤ ንዒ ርግብየ፡ ትናዝዝኒ እምላህ፤ ወንዒ ሠናይትየ፡ ምስለ ገብርኤል ፍሡሕ፤ ወሚካኤል፡ ከማኪ ርኅሩኅ፡፡” በሚል ውዳሴ እየተንደረደረ ኼዶ፡ “ተፈጸመ ናሁ፡ ማኅሌተ ጽጌ ሥሙር፤ አስምኪ ቦቱ፡ ንግሥተ ሰማይ ወምድር፤ ከመ በሕፅንኪ ያሰምክ ፍቁር፡፡” በሚል ማሳረጊያ ይደመድመዋል፡፡

የዚህም ትርጉም፡ የመጀመሪያው፡ “ከግንዱ የሠረፀችው ሐረግ፡ አበባነቷን ገልጣ አሳየች!”፥ ከዚያ የቀጠለው፡ “አንቺ፡ የፈካሽ ጽጌረዳ ሆይ! ንጹሕና ተአምረኛ በኾነችው፡ በአርባኛዪቱ ዕለት፡ ሕፃን ልጅሽን ዐቅፈሽ፡ ወደቤተ መቅደስ እንደገባሽ፡ ዛሬም፡ የእኔ መልካሚቱ ርግብ ሆይ! ከኃዘኔ ታጽናኚኝ ዘንድ፡ ከርኅሩኁ መልአክ፡ ከሚካኤልና ከባለምሥራቹ መልአክ፡ ከገብርኤል ጋር ዐብረሽ ነዪልኝ!” ሲኾን፥ የመጨረሻውም፡ “በምስጢር የተከናወነው፡ የአበባዪቱ ማኅሌት፡ እነሆ ተፈጸመ! የሰማይና የምድር ንግሥት ሆይ! ተወዳጁን ሕፃን ልጅሽን፡ በጭንሽ እንደታቀፍሺው ኹሉ፡ ይህን፡ ዝማሬያችንንም፡ እንደርሱ ተቀብለሽ ታቀፊልን!” የሚል ነው፡፡

በዚህ ወራት፡ በየሳምንቱ የሰንበት ሌሊት፡ ካህናቱና መዘምራኑ፡ በየአድባራት፥ በየገዳማት እና በየሰበካ ቤተክርስቲያናቸው እየተገኙ፡ ከዋዜማው ሰንበት ማታ ጀምረው፡ በመቋሚያ፥ በጸናጽልና በከበሮ በመዘመርና በማሸብሸብ፡ ቀደም ብሎ የተጠቀሰውን ማኅሌተ ጽጌ፡ በተመሰጠ መንፈሳዊ ስሜት ሲያደርሱ ያድራሉ፡፡ ምእመናን እና ምእመናትም፡ በብዛት ተገኝተው፡ ሌሊቱን ኹሉ፡ በመንፈሳዊ ደስታ ተመልተው፡ ወንዶቹ፡ በጭብጨባ፥ ሴቶቹም፡ በእልልታ፡ ካህናቱን በማጀብ፡ የምስጋናው ዝማሬ፡ ተካፋዮች ይኾናሉ፡፡

ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት፡ እንዲህ ባለ፡ የተለየ መልክ፡ መንፈሳዊ ደስታቸውን የሚገልጹት፡ ቀደም ብሎ ከተገለጸው፡ ከአበባው ምስጢራዊ ምሳሌነት ጋር፡ ሌሎች ተጨማሪ ምክንያቶችም ስላሏቸው ነው፡፡ እነዚህም፡- ፩ኛ፡- “ልጄን ከግብፅ ጠራሁት፤” የሚለው የነቢዩ ትንቢት ይፈጸም ዘንድ፡ መድኃኒታችን ድንግል ማርያም፡ ሕፃን ልጇን፡ ሰላማችን ኢየሱስ መሲሕን ታቅፋ፡ ከዮሴፍና ከሰሎሜ ጋር፡ ወደምድረ ግብፅ የተሰደደችበትንና በዚያም፡ “ቊስቋም” በተባለችው፡ የኢትዮጵያውያንና የኢትዮጵያውያት ርስትና ገዳም፥ በምድረ ኢትዮጵያም ውስጥ የቆየችበት ጊዜ የሚታወስበት መኾኑ፥

፪ኛ፡- በዚያኑ ወቅትና ከዚያ በኋላ፡ ልጇ፡ ፲፪ኛ ዓመቱን ከጨረሰበት ዕድሜው ጀምሮ ፴ ዓመት ሞልቶት እስኪጠመቅ ድረስ፡ ባለው ዘመን መካከል፡ እናትና ልጇ፡ በሊቀ መላእክት ቅዱስ ዑራኤል ጠባቂነት፡ አገራቸውን ኢትዮጵያን፡ እየተመላለሱ የጐበኙባቸው ጊዜያት የሚዘከርበት ሰሞን መኾኑ ናቸው፡፡

በእነዚህ ምክንያቶች፡ ይህ ወርኀ ጽጌ፡ በተለይ፡ ለእኛ ለኢትዮጵያ ልጆች፡ መታሰቢያነቱ፡ እጥፍ ድርብ ኾኖ ይዘከራል፡፡ ይህም፡ በአንድ ወገን፡ በታላቅ ተመስጦ በሚካኼደው፡ በጽጌ ማኅሌት፥ በሌላ ወገን ደግሞ፡ በፍጹም ፈቃደኝነት በምትጾመው፡ በጽጌ [የስደት]ጾም ገዝፎ ይታያል፡፡

የጽጌ ማኅሌቱ እና የስደቱ ጾም ፍጻሜ፡ ቅድስት እናታችን እና ልጇ፡ ከስደታቸው ባረፉባት፡ በኢትዮጵያውያኑና በኢትዮጵያውያቱ ገዳም፡ በደብረ ቍስቋም ተሰይሞ፡ በዓሉ፡ በኅዳር ፮ ቀን ይከበራል።

## ዘመነ አስተምህሮ።

ከኅዳር ፮ እስከ ፴ ቀን ድረስ፡ "ዘመነ አስተምህሮ" ይባላል። ከመስከረም ፳፮ እስከ ኅዳር ፯ ቀን ድረስ ባለው "ወርኀ ጽጌ"፡ ሰብአዊቷ ነፍስ፡ ስለሥነ ፍጥረት፥ ስለፈጣሪ እና ስለራሷ ሰብአዊ ፍጡርነት፡ በበለጠ ስትረዳ ቆይታለች።

እንደዚያ ኹሉ፥ አኹን ደግሞ፡ ከኅዳር ፮ እስከ ፴ ቀን ድረስ ባሉት ሳምንታት፡ ከምስጢረ ሥላሴ ተነሥታ፡ በምስጢረ ሥጋዌ፥ በምስጢረ ጥምቀትና በምስጢረ ቍርባን ዐልፋ፡ ወደምስጢረ ትንሣኤ ሙታን የምትደርስበትን፡ የዓመቱን፡ ሥጋዊና መንፈሳዊ ጉዞ፡ በትምህርት እየታነጸች፡ የዕውቀት ጉዞዋን፡ በዕድገት ትቀጥላለች። እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ እና እያንዳንዷ ኢትዮጵያዊት፡ በእነዚህ ሳምንታት፡ ሲቻላቸው፡ በቤተ ክርስቲያን፥ ሳይቻላቸው ደግሞ፡ በየቤታቸው እና/ወይም፡ በየሥራ ቦታቸው፥ አለዚያም፡ በየሚመቻቸው ሥፍራ እየተገኙ፡ ከትምህርቱ ጋር የምስጋና ጸሎታቸውን፡ ወደፈጣሪያቸው እያቀረቡ፡ በነቢያት ትንቢት፡ ሲጠበቅ የኖረውን እና በሐዋርያት ተስፋ ተፈጽሞ የታየውን፡ የአዲስ ኪዳን ምሕረቱን ለመቀበል፡ እየራሳቸውን ያዘጋጁበታል።

ሕዝቡ፡ በዚህ፡ የትምህርት እና የምስጋና ጸሎት አካኼዱ፡ እግዚአብሔር፡ በዘመነ ብሉይ፡ ለቀደሙት ወላጆቹ፡ በቃል ኪዳን ሲያደርግላቸው የቆየውን፡ የረድኤትና የበረከት ሥራዎቹን እያስታወሰ፡ እርሱም በፋንታው፡ እነርሱ ለበቁበት የገድል ጸጋና የድል አክሊል፡ እየራሱን ለማብቃት፡ የሚደራጅባቸውን በዓላት እያከበረ፡ ጉዞውን ይቀጥላል። እነዚህም በዓላት፡ ከዚህ የሚከተሉት ናቸው፦

### የኅዳር ሚካኤል።

"የኅዳር ሚካኤል" ተብሎ፡ በኅዳር ፲፪ ቀን የሚከበረው፡ የሊቀ መላእክት ቅዱስ ሚካኤል በዓል ነው። እግዚአብሔር፡ የእስራኤልን ሕዝብ፡ ራሱን፡ ለኢትዮጵያዊነት ባበቃው፡ በሙሴ አማካይነት፡ ከፈርዖን የባርነት አገዛዝና ከምድረ ግብፅ የሥቃይ ኑሮ፡ ነጻ አውጥቶ፡ መዓልቱን፡ በደመና፥ ሌሊቱንም፡ በእሳት ዓምድ ከልሎ እየመራቸው፥ የኢትዮጵያንም ባሕረ ኀጋሽ (ቀይ ባሕርን)፡ በደረቅ ምድር ካሻገራቸው በኋላ፡ እየጠበቃቸው፥ ውኃውን ከዓለት አፍልቆ፥ ኅብስተ መናውን ከሰማይ አውርዶ፥ "ሥጋ አማረን!" ሲሉም፡ ድርጭቱን፡ በነፋስ አውታር ሰብስቦ አምጥቶ እየመገባቸው እንደተንከባከባቸው ይታወቃል፤ በአምላካቸው ቸርነት፡ ይደረግላቸው የነበረውን፡ ያን ኹሉ፡ የተራዳኢነት ተልእኮ ይፈጽምላቸው የነበረው፡ ሊቀ መላእክት ቅዱስ ሚካኤል ነበር።

*ይኹን እንጂ፡ እነርሱ፡ ለዚህ ኹሉ አምላካዊ ቸርነት፡ ውለታቢሶች በመኾን፡ ፈጣሪያቸውን አሳዘኑ፤ ይኸውም፡ ሙሴ፡ ከእግዚአብሔር ጋር ለመገናኘት፡ ወደተራራ ወጥቶ፡ ለጥቂት ቀናት፡ በሱባዔ መቆየቱን ምክንያት አድርገው፡ ካህን ወንድሙን፡ አሮንን፡ **“በፊታችን የምናስቀድመው፡ ጣዖት ካልሠራህልን!”** ብለው አስጨንቀው፡ ጣዖቱን ማስቀረፃቸውና ማምለካቸው ነው።*

*እነርሱ፡ ሊጠፉበት የነበረውን የእግዚአብሔር ቍጣ፡ ሙሴ በባለሟልነቱ አማልዶ ቢያስመልስላቸውም፥ የእነርሱ፡ ማለትም፡ የእስራኤል ልጆች ፍላጎት፡ እንደኢትዮጵያ ልጆች፡ እግዚአብሔርን፡ በእውነት እና በመንፈስ ማምለክን ሳይኾን፡ እንደአሕዛብ፡ በሚታይና በሚዳሰስ ግዙፍ ጣዖት መኾኑን፡ እግዚአብሔር ተመለከተ፤ እንዲህ ከኾነ ብሎም፡ እርሱ፡ እግዚአብሔር፡ <u>ቃሉን፡</u> በጽላት ላይ ቀርፆ፥ ያንንም ጽላት፡ በግእዝ፡ “ታቦት” በሚባለው ሣጥን ውስጥ እንዲያስቀምጡት አዘዞ፡ በዚያ፡ እንዲያመልኩት፡ “ታቦተ ጽዮን” የተባለችውን፡ የቃል ኪዳን ምስክር ሰጣቸው። ከዚህ የተነሣ፡ ጠላቶቻቸውን ድል ይነሡባት ዘንድ፡ እንዲህ አድርጎ በሰጣቸው፥ እርሱ፡ ለእነርሱ በሚገለጽባት፥ እነርሱም፡ እርሱን በሚያመልኩባት፡ በዚችው የጽላተ ሕግ ሃይማኖት እና ምግባር ጸንተው፡ ይኼዱ፥ ወይም አይኼዱ እንደኾነ ሊፈትናቸው፡ አርባ ዓመታት ሙሉ፡ በምድረ በዳ አንከራተታቸው።*

*በዚያን ጊዜ፡ ለእስራኤል ሕዝብ፡ “**ወእፌንዎ ለመልአክየ ቅድሜከ። ...ኢያበውአከ ውስተ ምድር፡ እንተ ትውኅዝ ሐሊበ፥ ወመዓረ፤ ወኢየዓርግ ምስሌከ፡ በእንተ ሕዝብከ፡ እለ ያገዝፉ ክሳዶሙ፡ ከመ ኢያኅልቆሙ በፍኖት። ወተትንና ማርን ወደምታፈስሰው ምድር አላገባህም። እኔ ግን፡ የበደሉኝን በደል አስቤ፡ በጐዳና እንዳላጠፋቸው፡ በፊትህ፡ መልአኬን እሰድዳለሁ እንጂ፡ አንገተ ደንዳና በኾነው፡ በዚህ ሕዝብህ ምክንያት፡ እኔ፡ በአንተ መካከል አልወጣም!**” ብሎ የመደበላቸው መልአክ፡ ቅዱስ ሚካኤል ነበረ። ይህ ኹሉ ዝክረ ነገር፡ በኦሪት ዘጸአት መጽሓፍ ውስጥ ተመዝግቦ፡ ዛሬ ድረስ የሚነበብ ነው። (ዘጸአ. ፴፪፥ ፩-፴፫፤ ፴፫፥ ፩-፫።)*

*እግዚአብሔር፡ ለወዳጆቹ፡ ለአብርሃም፥ ለይስሓቅና ለያዕቆብ፡ የገባውን ቃል ኪዳን በማሰብ፡ በዚያን ዘመን፡ ለእስራኤል ልጆች፡ ያን የመሰለ ታዳጊነቱን፡ በመልአኩ በቅዱስ ሚካኤል አገልጋይነት ያደርግ እንደነበረ፡ ዛሬ፡ “እውነተኞቹ እስራኤል እኛ ስለኾንን፡ ይህንኑ ተራዳኢነቱን ይፈጽምልናል!” ብለው፡ የኢትዮጵያ ልጆች፡ የቅዱስ ሚካኤልን በዓል፡ በዚህ ዕለት ያከብራሉ።*

*በአገራችን፡ በኢትዮጵያ፡ በዚሁ፡ በኅዳር ሚካኤል ዕለት፡ ካህናቱ፡ በየቤተ ክርስቲያኑ፡ ጸሎተ ዕጣን እየደገሙ፡ የማዕጠንት ዕጣንን የሚያሳርጉት፥ ሕዝቡ፡ በከተማ፡ ቍሻሻ የኾነውን ነገር ኹሉ እየሰበሰበ የሚያቃጥለው፥ በገጠርም፡ በየእርሻው፥ በተለይም በቆላ የሚኖረው ወገን፡ ስለወባና ወረርሽኝ፡ በየመሬቱ ላይ እሳት አንድዶ፡ ጢስ የሚያጬሰው፡ “ኅዳር ታጠነ!” የሚባለውን ይትበሃል ለማስታወስ ነው፤ የዚህም ምክንያት፡ በራእየ ዮሓንስ ተጽፎ እንደሚነበበው፡ “ሃያ አራቱ ካህናተ ሰማይ” የሚባሉት መላእክት፡ ስለዓለሙ ኹሉ ደኅንነት፡ በሰማይ፡ በጽርሐ አርያም፡ የምስጋና ጸሎትን፡ ከዕጣን ማዕጠንት ጋር፡ በእግዚአብሔር መንበር ፊት፡ ያለማቋረጥ የሚያቀርቡትን ሥርዓት የተከተለ ነው።*

እንደዚሁ ኹሉ፡ እኛንም፡ እግዚአብሔር፡ በምድር ላይ፡ ካለፈው ዓመት፡ ከማናቸውም ዓይነት፡ ሕማምና ደዌ፥ ቸነፈርና በሽታ ጠብቆ ስላዳነን፥ ከሚመጣውም እንዲጠብቀን በማለት፡ በዚያ ሰማያዊ ሥርዓት፡ እኛም፡ ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት፡ ለፈጣሪያችን፡ ምስጋናችንንና ጸሎታችንን፡ ይኸው እናቀርባለን። በቅርቡ፡ በአጼ ምኒልክ ዘመን ደርሶ የነበረውን፡ "የኅዳር በሽታ" የሚባለውን ከመሰለ፥ በዓመቱ ውስጥ፡ ተላላፊ የሰውና የከብት በሽታ ገብቶ፡ ሊያደርስ ከሚችለው ጥፋትና ዕልቂት "አድነን!" ለማለት።

## የኅዳር ጽዮን።

መድኃኒታችን ድንግል ማርያም እና ሰላማችን ኢየሱስ መሲሕ፡ ዓሥሩ የእግዚአብሔር ቃላት በተጻፉባቸው ጽላት [ኹለት የድንጋይ ሰሌዳዎች] እና እነርሱን በያዘችው ታቦት አድረው የኖሩባት እና "ኪዳነ ሙሴ" የምትባለው "ታቦተ ጽዮን" የምትዘከርበት በዓል፡ "ኅዳር ጽዮን" ወይም "ተዝካረ ማርያም" ተብሎ፡ በኅዳር ፳፩ ቀን ይከበራል።

"ኅዳር ጽዮን" ተብላ፡ በኅዳር ፳፩ ቀን መከበርዋ፡ "እውነተኛዋ ታቦተ ጽዮን" እርሷ፡ እግዝእተብሔር እም፡ ቅድስት ድንግል ማርያም መኾኗን ለማመልከት ብቻ ሳይኾን፡ "አማናዊቷ ቤተ መቅደስ"ም፡ እርሷው መኾኗን ለማሳወቅ ነው። ይህም፡ የቃል ኪዳን ልጆቿ እንደኾኑት፡ እንደኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት የቀን አቈጣጠር፡ በመስከረም ፩ ቀን የተወለደችውን፡ ድንግል ማርያምን፡ ወላጆቿ፡ እንደኦሪቱ ሕግ፡ በ፹ (ሰማንያ) ቀኗ፡ በእግዚአብሔር ፊት ሊያቀርቧት፡ በሕፃንነቷ፡ ወደቤተ መቅደስ የገባችበት ዕለት መታሰቢያ ጭምር በመኾኑ ይረጋገጣል።

ቀደም ብሎ እንደተገለጸው፡ በብሉዩ ኪዳን፡ ለእስራኤል ሕዝብ መመኪያና ለድል አድራጊነታቸው ዋስትና ኾና፡ ስትጠብቃቸው የቆየችው፡ ይህችው "ጽላተ ኪዳን"፡ ከእነርሱ ተወስዳ፡ ለኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት ተሰጥታለች፤ ይህም የኾነው፡ በእርሷ ምስክርነት፡ የእስራኤል ልጆች" የተባሉት አይሁድ፡ ከእግዚአብሔር ጋር ለተጋቡት ቃል ኪዳን፡ እርሷን፡ በባለአደራነት ጠብቀው ለማኖር፡ የበቁና የታመኑ ኾነው ባለመገኘታቸው ነው።

በዚያች፡ አንዲት በኾነችው መንታ ጽሌዎች (ጽላት) ላይ፡ በመለኮት ጣቶች የተጻፈው፡ የእግዚአብሔር ቃል፡ የአዲሱ ኪዳን ሕያውት ጽላት በኾነችው በድንግል ማርያም ማሕፀን ተቀርፆ፡ በሰውነት በተወለደ ጊዜ፡ የዚያች፡ የብሉዩ ኪዳን "ታቦተ ጽዮን"፡ ተልእኮዋን፡ ለመፈጸም በቅታለች።

ስለዚህ፡ እኛ የኢትዮጵያ ልጆች፡ ለምድራዊው ህልውናችን ብቻ ሳይኾን፡ ለሰማያዊው የዘለዓለም ሕይወታችንም፡ አማናዊቷ (እውነተኛዋ) መመኪያችንና የድል አድራጊነት ዋስትናችን የኾነችው፡ ሕያውቷ ታቦተ ጽዮን፡ እርሷ፡ "እግዝእተብሔር እም፡ ቅድስት ድንግል ማርያም ናት!" ብለን አምነን፡ እነሆ፡ በዓሏን፡ በተለየ አንክሮና ተዘክሮ፥ ተመስጦም እናከብረዋለን።

ይህ በዓል፡ ምንም እንኳ፡ በመላዋ የኢትዮጵያ አድባራትና ገዳማት፥ ሰበካም ቤተ ክርስቲያን፡ በከፍተኛ መንፈሳዊ ስሜት የሚከበር ቢኾንም፡ ታቦተ ጽዮን፡ ከኢየሩሳሌም፡ ወደኢትዮጵያ መጥታ፡ እየተዘዋወረች ከቆየችባቸው ቅዱሳት መካናት በኋላ፡ በመጨረሻ፡ ባረፈችባትና "የታቦተ ጽዮን ከተማ" በተባለችው፡ በአኵስም፡ "እምነ ጽዮን"፡ ማለትም፡ "እናታችን ጽዮን" እየተባለች፡ በተለየ ደማቅ ሥርዓት ትከበራለች።